ክርስቲያኖች እንዲህ ናቸው፤ ይበልጡኑ የሚታወቁት በማያደርጓቸው ወይም በሚታቀቡባቸው ነገሮች ነው፤ ስለዚህም ሰዎች እነርሱን ተመልክተው በክርስቶስ አይማረኩም።

ኢየሱስ ግን እንዲህ አልነበረም። ሰዎች በእርሱ ይማረኩ የነበረው ይህን ወይም ያን ከማድረግ ራሱን ስላቀበ ሳይሆን በሚያደርገው ነገር ነበር። ከዚያ ቀደም ያላዩትን የሕይወት ውበት ተመልክተው፤ ይህን በራሳቸውም ማግኘት ፈለጉ። በክርስቶስ ደስታ፤ ሰላምና ርህራሄ ከሁሉም በላይ የእግዚአብሔር ፍቅር ተገልጦ ተመለከቱ።

እግዚአብሔር ይህንኑ ኢየሱስ የገለጠውን ውብ የሆነ ሕይወት ሊሰጠን ይፈልጋል። ኢየሱስ ለደቀመዛሙርቱ እንዲህ ብሏቸዋል፤ "ደስታዬ በእናንተ እንዲሆንና ደስታችሁም ሙሉ እንዲሆን ይህን ነግሬአችኋለሁ" (ዮሐ 15፥11)። የክርስትና ሕይወት ጨፍጋጋ፤ አሰልቺና ፈዛዛ እንደሆነ የምታስቡ ከሆነ ይህን እነግራችኋለሁ፤ ተሳስታችኋል! ልብ በሉ፤ *እግዚአብሔር የተሻለ ምትክ ሳያደርግ፤ ከሕይወታችን የሚያስወግደው ነገር የለም።*

ይህ ለጊዜው እውነትነቱ ላይገለጥልን ቢችልም ውሎ አድሮ ግን እናስተውለዋለን። እውነቱ ሲገባንም በእግዚአብሔር ጥበብና መልካምነት እንደነቃለን። እግዚአብሔር ባሪያ ያደረጋችሁን ከፉ ልማድ ሊነቅልላችሁ የተሻለ የአኗኗር መንገድ ይሰጣችኋል። ሐሜትን፤ መራገምን፤ አሰብልታን ከእናንተ ሊያስወግድ የፍቅርና ሰዎችን የሚደግፍ እንደዚሁም የምስጋና ቃልን በአንደበታችሁ ያኖራል። ራስን ማዕከል ማድረግን ከእናንተ ሊያርቅ የእርሱን ፈቃድ የማድረግን፤ ደስታና ሐሴትን በምትኩ ይሰጣችኋል። እግዚአብሔር እጉል ነገሮችን ከሕይወታችሁ ሊያስወግድ ሥራውን እንዳጠናቀቀ አይቆጥርም፤ ከዚህም ባሻገር በመልካም ነገሮች ሊተካላችሁ ይሻል። *የእርሱ ሀሳብ በመንፈስ ቅዱስ በውስጣችን አዲስ ሰው አድርጐ ሊለውጠን ነው።* መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፤ "መልካም፤ ደስ የሚያሰኝና ፍጹም የሆነው የእግዚአብሔር ፈቃድ ምን እንደሆነ ፈትናችሁ ታውቁ ዘንድ በአእምሮአችሁ መታደስ ተለወጡ እንጂ ይህን ዓለም አትምሰሉ" (ሮሜ 12፥2)።

የእግዚአብሔር ፈቃድ እንዲህ ነው፤ *መልካም፤ ደስ የሚያሰኝ አና ፍጹም።* ታዲያ ወርቅ እያለልን፤ ዓይናችን መዳብ ይቀላውጣልን?

ክፍል ሁለት

ለጉዞአችን ስንቅ መያዝ

ዘጠኝ

ስለዅሙ ጉዞ መዘጋጀት



"ሸክም የሚሆንብንን ሁሉ፣ በቀላሉም ተብትቦ የሚይዘንን ኃጢአት ለሰመገደን

በፊታችን ያለውን ረጂ በጽናት እንሩጥ።"

(ዕብ 12፡ 1)

እግዚአብሔር የጠራን ለአጭር ርቀት ሩጫ ሳይሆን ለማራቶን ነው።

በ1930ዎቹ አባቴ በሠፈራችን ውስጥ መኪናው ውስጥ ሬዲዮ ለማስገባት የመጀመሪያዎቹ ከሆኑት መካከል ነበር። ብዙ ጊዜ መኪና ውስጥ ሆነን በጥራት ባይሰሙንም ከአውሮፓ ይተላለፉ የነበሩትን ፕሮግራሞች በመሰማት እንደሰት ነበር። አንዳንድ ጊዜ የአዶልፍ ሂትለርን አንዳች ኃይል ያለው የሚመስል ድምፅ አንሰማ ነበር፤ የሚናገርበት ቋንቋ ባይገባኝም (ዓለምን የሚያተራምሰ እንደነበረ ሙሉ በሙሉ ለመረዳት ዕድሜዬ ባይፈቅድልኝም አንኳን) በሰማሁት ቁጥር የሆነ ፍርሃት ያድርብኝ ነበር። በ1936 የተካሄደውን የበርሊን ኦሊምፒክ መቼም አልረሳውም። ይህ ትኩረቴን የሳበ የመጀመሪያው ኦሊምፒክ ነበር። የሂትለር ዕቅድ፣ ይህ የስፖርት እንቅስቃሴ በናዚ የሚመራ አትሌቲክስን በሳጭነት ለማሳየት ነበር፤ ሆኖም ባልተጠበቀ ሁኔታ ጀሲ ኦዌንስ የሚባል በትውልድ አፍሪካዊ የሆነ - አሜሪካዊ በወዳድሩ አሸናፊ ሆነ። ኦዌንስ ከዚያ ቀደም ባልታየ ሁኔታ አራት የወርቅ ሜዳሊያ ሊያሸንፍ፡ ለአሜሪካውያን የደስታና የኩራት ወቅት ነበር። ጋዜቦች ሳይ እንዳነበብነው ይህ ጉዳይ ሂትለርን ሲያስቆጣው ለእኛ ግን በድል ስሜት ያስፈነጠዘን ነገር ነበር። ጀሲ ኦዌንስ ከምንኮራባቸው ታላላቅ አትሌቶቻችን አንዱ ነበር።

አጭር ርቀት ወይስ ማራቶን?

የአጭር ርቀት ሩጫ ስሙ እንደሚገልጸው ከማራቶን በጣም ልዩ ነው። አጭር ርቀት የሚወስደው ጊዜ ከጥቂት ሰኮንዶች አይበልጥም፤ ማራቶን ግን በርካታ ማይሎችን የሚሸፍን ሊሆን በርካታ ሰዓታትን ይወስዳል።

ልዩነቱ የርቀትና የጊዜ ብቻ አይደለም፤ ከሯጮቹ የሚጠበቀው ጥንካሬና ጉልበትም ይለያያል። ለምሳሌ 100 ያርድ (91.44 ሜትር) የሚሮጥ ወይም በ200 ሜትር ሩጫ የሚሳተፍ ሰው ያለ የሌለ ጉልበቱን አሰባስቦ በጥቂት ሰኮንዶች መጨረስ ስላለበት የማጠናቀቂያ መስመሩን የሚነካው ጉልበቱ ተዳክሞና ዝሎ ነው። ተጨማሪ 100 ያርድ ወይም 200 ሜትር መሮጥ ካለበት ተዝለፍልፎ ሊወድቅ ወይም ፍጥነቱ በእጅጉ ሊቀንስ ይችላል።

የማራቶን ሯጭ ግን በተመጠነ ሁኔታ በቀሰታ ይሮጣል እንጂ በአንዴ ሩጫውን ሳፍ አድርጉ ጉልበቱን አያደክምም። በ1936 ኦሊምፒክ የተሳተፈው ሌላ አሜሪካዊ ሯጭ ሊዊስ ዛምፔሪኒ በ5000 ሜትር ርቀት የተቀዳጀው ድል በሂትለርም ሳይቀር ከበሬታ ያገኘጸፈው ነበር። ከበርካታ ዓመታት በኋላ ሊዊስ በ1949 በሎስ አንጀለስ ባካሄድነው ሰብሰባ ሕይወቱን ለክርስቶስ ሰጠ፣ በአንድ ወቅት የማራቶን ሯጭ ለረዥም ርቀት እንዴት እንደሚሰለጥንና ጉልበቱን ሁሉ ለዚያ እንዴት እንደሚያውል የነገረኝን አስታውሳለሁ።

በርግጥ ማራቶን ሙሉ በሙሉ ከክርስትና ሕይወት ጋር ተመሳሳይ ነው ማለት አይደለም። ለምሳሌ ያህል፣ የየግል ሩጫችን ምን ያህል ጊዜ እንደሚወስድ አናውቅም፤ ምናልባት አግዚአብሔር የበነገው ዕለት ወደራሱ ሊሰበስባችሁ ይችላል፤ የማራቶን ሯጭ ለዓመታት የሚዘልቅ ለፊ ስልጠና ከወሰደ በኋላ ነው ወደ ውድድር ሜዳ የሚገባው። እኛ ግን አሁንም ሩጫ ውስጥ ስንሆን፣ የውድድሩን ጥበብ የምንማረው እዚያው ሆነን፣ አግዚአብሔር የሚሰጠንን ጉልበትና ብርታት እየተቀበልን ነው። የማራቶን ሯጭ መስመርን ጠብቆ ሊሮጥ እኛ ግን በመንገድ ሳይ የሚጠብቁንን ውጣ ውረዶች አሰቀድመን በአቅጩ አናውቃቸውም - ስለገዘአችን መጨረሻ (ግብ) አንዳች ጥርጥር ባይኖረንም።

ረዥሙ ጉዞ

ይሁንና እኛም እንደማራቶን ሯጭ ከፊታችን ረዥም መንገድ (ጉዞ) ይጠብቀናል። የኛ ጉዞ - የኛ ሩጫ - እግዚአብሔር በሕይወት አስካቆየን ድረስ ይቀጥላል። ፊር ስተን ከተለመረልን መስመር ልናፈነግጥ፣ ወይም ሩጫውን ትተን በመውጣት የተመልካቾቹን ጉራ ልንቀሳቀል ወይም ፍጥነታችንን ቀንሰን ሌሎች ቀድመውን ሊሄዱ ልናይ አይጠበቅብንም። አርአያችን ኢየሱስ ነው፤ እርሱ "በፊቱ ስላለው ደስታ መስቀሉን ታግሦ፣ የመስቀሉንም ውርደት ንቆ፣ በእግዚአብሔር ዙፋን ቀኝ ተቀምጦአል" (ዕብ 12÷2)። ደሙን ማፍሰስ ቢያስጠይቀውም እንኳን እግዚአብሔር ያዘጋጀለትን ሩጫ በታማኝነት አጠናቅቋል።

የጉልበታችን እንጥፍጣፊ እስኪቀር ድረስ ዝለን በሩጫው መሃል ተዝለፍልፈን እንድንወድቅም አይጠበቅብንም። ይህ የሚከሰተው ያለጥበብ የሮጥን ወይም በራሳችን ጉልበት የተማመንን እንደሆነ ነው። በዚህ ሁኔታ ለተወሰነ ርቀት ቢሆንልንም፣ ብዙ ላንርቅ እንገታለን። በራሳችን በጣም ደካማ ነን፣ መንፈሳዊ ስንቃችንም የሚያስተማምን አይደለም። እግዚአብሔር እርሱ በሚሰጠን ብርታት እንጂ በእኛ ብርታት ይህን ጉዞ እንድናደርግ አይጠበቅብንም። ጳውሎስ እንዲህ ሲል ይህን ማመልከቱ ነበር፣ "ኃይልን በሚሰጠኝ በእርሱ ሁሉን ማድረግ እችላለሁ" (ፊል 4÷13)።

በርካታ ክርስቲያኖች በመንፈስ ዝለው ከሚጸከመባቸው ምክንያቶች አንዱ ይህን እውነት ባለመገንዘባቸው እንደሆነ ተረድቼአለሁ። የክርስትናን ሕይወት በራሳቸው በመኖር ሊወጡት እንዳለባቸው ስለሚያስቡ እግዚአብሔር ለጉዞው ብርታት እንዲሆነን ያዘጋጀልንን የተትረፈረፈ ስንቅ ሳይጠቀሙ ይቀራሉ። ለግብግ ተጠርተው ግን ለማዕዱ ሳይቀመጡ እንደቀሩ እንግዶች፣ ከእግዚአብሔር ስንቅ ኃይልን እንዴት መቀበል እንደሚችሉ አልተማሩም። እግዚአብሔር ግን በዚህ ሁኔታ እንድንቀጥል አይሻም። እንድንወድቅ አይፈልግም። እንዲያውም እናንተ ልትሆኑ ከምትችሉት በላይ ለለመንፈሳዊ ጤንነታችሁ ጉዳይ ግድ ይለዋል።

ስሩጫ መዘጋጀት

ጀሊ አዌንስ የበርሊኑን አሊምፒክ ውድድሩን አሸንፎ ሽልማት በመቀበሉ፣ በርካታ አዳጊ ወጣቶች አንድ ቀን የእርሱን

ድል ለመድገም እንዲናፍቁ እንደሚያደርጋቸው ጥርጥር የለውም። ሆኖም ለቀጣዩ አሊምፒክ ለመወዳደር ብቁ የሚሆኑት በጣም ጥቂቶቹ እንደሆኑ ግልጽ ነው (ቀጣዩ አሊምፒክ በጦርነቱ ምክንያት ተሰርዟሎ በ1948 ነበር የተካሄደው)። ለዚህ ምክንያቱ ምንድነው? ባጭሩ ይህ የሚጠይቀው ተፈጥሮአዊ ተሰጥኦ ስለሌላቸው ነው። እንዳንዶቹ ምናልባት ተሰጥኦ ይኖራቸው ይሆናል፤ ሆኖም ከእነርሱ ማናቸውም የጂሊ አዌንስን ሪኮርድ ለመድረስ አልበቁም።

ለምን? ምክንያቱም አንድ ለው የተዋጣለት ሯጭ፣ የእግር ኳስ ተጫዋች፣ የአጅ ኳስ ተጫዋች፣ ዋናተኛ፣ ወይም የብስክሌት ተወዳዳሪ፣ ወይም ሌላ ነገር ለመሆን የሚበቃው ችሎታ ስላለው ብቻ አይደለም። የተፈጥሮ ችሎታ፣ ከሌሎች ሁለት ነገሮች ጋር መጣመር አለበት፤ እነዚህም *ቁርጠኝነትና ትጋት* ናቸው።

ለሯጭ ቁርጠኝነት ማለት መሆን የሚችለውን ሆኖ የላቀ ውጤት ለማግኘት፣ ጠንካራ ፍላጐት፣ ወደፊት የሚገፋ ጽናትና ሁለንተናውን የሚገዛ ግፊት እንዲኖረው ያስፈልጋል ማለት ነው። ዓላማ አድርጎ የያዘው አንድ ነገር ሲሆን ይህም ማሸነፍ ነው። ቁርጠኝነት ማለት ተስፋ፣ ምኞት ወይም ጥልቅ ናፍቆትም አይደለም። ከዚህ እጅጉን የላቀ ነው። ሌላ ነገር ሁሉ በሁለተኛ ደረጃ ይቀመጣል ወይም ካስፈለገም ወደጐን ይተውና ያለውን ጉልበት ሁሉ ተጠቅሞ በመያው የላቀ ደረጃ ለመድረስ ይታገላል ማለት ነው። እንድ አትሌት ከመደው ውጪ ምንም ነገር አያውቅም ለንል ሌት ተቀን ከዓላማው ለመድረስ "መሉ ትኩረቱንና ጊዜውን" ይሰጣል ማለታችን ነው። ቁርጠኝነት ማለት ይህ ነው፤ ለው ካለበው ለመድረስ መሉና ፍጹም የሆነ መሰጠት ይኖረዋል።

ቁርጠኝነት ለሯጭ ወሳኝ ነገር ነው፤ ሆኖም ቁርጠኝነት በራሱ በቂ አይደለም። ሯጩ በውድድር ማሸነፍ እንዲችል ትጋትንም አጣምሮ መያዝ ይኖርበታል። አንዲት ወጣት ሴት የተዋጣለት የቴኒስ ተጫዋች ለመሆን በመሉ ልቧ ልትመኝ ትችላለች፤ ሆኖም ጨዋታውን ከመሠረቱ ጀምራ ለመማርና ራሷን ለማለልጠን ዝግጁ ካልሆነች ሕልሟ ሊሳካ አይችልም። ስለዚህም ትጋት ሊኖራት ያስፈልጋል፤ ይህም ማለት የቴኒስ ጨዋታ የሚጠይቃቸውን ክህሎቶች በየጊዜው ማሻሻልና የአካል ብቃቷን ማዳበር ይጠበቅበታል። ይህም በየጊዜው የአካል እንቅስቃሴ ማድረግና የተመጣጠነ ምግብ መመገብ ያካትታል።

ሰነፍ የቴኒስ ተጫዋች ብትሆን ምንም ያህል ተሰጥኦ ብትታደልም ለሽልማት የሚያበቃ ስኬት መቀዳጀት አትችልም። በአንባሩ እንደሌሎች በተሰጥኦ ባትታደልም ትጋትና ቁርጠኝነትን ያጣመረች ስፖርተኛ ለአንደኛነት ልትበቃ ትችላለች።

በበርሊን ኦሊምፒክስ ድል ከተቀዳጀ ክበርካታ ዓመታት በኋላ ጂሲ ኦዊንስ የ100 ሜትር ሩጫ አሸናፊ መሆን ምን ስሜት እንደፈጠረበት ሲጠየቅ "ዘመንን ሁሉ በሥልጠና ያላለፍኩት ለ0ሥር ሰኮንድ ውድድር ነበር" ብሎ ነበር የመለሰው። የዚህ አጭር ውድድር ድል የዓመታት ቁርጠኝነትና ትጋት የሚጠይቅ ነበር፤ ያ ዋጋ ላያክፈል ሚዳሊያ ማግኘት የማይታሰብ ነበር።

የደቀመዝሙርነት ጥሪ

በእንግሊዝኛ ቋንቋ "ሥነ ሥርዓት" ወይም ራስን ማስገዛት እና "ደቀመዝሙር" መመሳሰላቸው የአጋጣሚ ነገር ላይሆን የሁለቱም ሥረ-መሠረት የላቲን ቋንቋ ስለሆነ ነው። በወንጌላት ለክርስቲያን መጠሪያነት የተዘወተረው ቃል "ደቀመዝሙር" የሚል ነው፤ ደቀመዝሙርነት ከመለጠትና ክሥነ ሥርዓት ሊነጠል አይችልም። *ደቀመዝሙር መሆን ማለት መለጠት ማለት ነው* - ለኢየሱስ ጌትነትና አዳኝነት መለጠት እናም በየዕለቱ እርሱን ለመክተል መለጠት ማለት ነው። *ደቀመዝሙር መሆን ማለት ራስን ማስገዛት ማለት ነው።* በሰውነት፣ በእእምሮ፣ በነፍስ ራስን ማስገዛት ማለት ነው። እኒህን ባህርያት ገንዘብ አድርጋችኋል?

በርግጥ አዲስ ክዳን ክርስቲያንን ለመግለጽ የተለያዩ ቃላትን ይጠቀማል፤ እነዚህ ሁሉ ኢየሱስን መከተል ምን ማለት እንደሆነ እንድንገነዘብ ያረዱናል። ቀደም ሲል እንደተመለከትነው፣ ክርስቲያን በክርስቲያናዊ ጉዞ "ማራቶን ሩጫ" ላይ ሯጭ እንደሆነ መጽሐፍ ቅዱስ ይገልጻል። ጳውሎስ፣ "እንግዲህ በሩጫ ውድድር የሚሮጡ ብዙዎች እንደሆኑ ሽልማቱን የሚቀበለው ግን አንድ ብቻ እንደሆነ አታውቁምን? ስለዚህ ሽልማቱን እንደሚቀበል ሰው ሩጡ" በማለት ጽፏል። ቡጠልማሪም፣ "ለውድድር የሚዘጋጅ ማንኛውም ሰው በሁሉም ነገር ራሱን ይገዛል፤ ስለዚህ እኔ ግብ እንደሌለው ሰው በክንቱ አልሮጥም፤ ሰውነቴን እየጐሰምሁ እንዳገለልኝ እደርገዋለሁ" (1ኞሮ 9፡24-27) ብሏል። እግዚአብሔር ባዘጋጀው ውድድር ሯጭ የነበረው ጳውሎስ ሰግቡ በተሩጠኝነት የተሰጠና

እዚያ ለመድረስ የሚያስፈልገውን ሁሉ ለመክፈልና ራሱን ለማስገዛት የጨከነ ሰው ነበር።

መጽሐፍ ቅዱስ ክርስቲያንን የሚጠራበት ሌላው ምሳሌ "*ወታደር*" ነው። ወታደር የጦር አበጋዙን የመታዘዝ ግዴታ አለበት፤ ጠላቱን ለመግጠምም ተገቢውን ሥልጠናና ትጥቅ ሊቀበል ይገባዋል። ወደ ጦር አውድማ ለመግባት፣ ካለፈለገም ሕይወቱን ለመሠዋት ፈቃደኛ መሆን አለበት። መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፤ "በጌታና ብርቱ በሆነው ኃይሉ ጠንክሩ ... የእግዚአብሔርን ሙሉ የጦር ዕቃ ልበሱ" (ኤፌ 6፡10-11) ይላል። ጳውሎስ ለጢሞቴዎስ እንዲህ ሲል ይመክረዋል፤ "እንደ ክርስቶስ ኢየሱስ በጎ ወታደር፣ ከእኛ ጋር መከራን ተቀበል። በውትድርና የሚያገለግል ሰው አዛዡን ለማስደሰት ይጥራል እንጂ በሌላ ሥራ ራሱን አያጠላልፍም" (2ጢሞ 2፡3-4)።

ክርስቲያንን ለመግለጽ መጽሐፍ ቅዱስ የሚጠቀመው ሌላ ቃል "*ወንድሞች*" የሚል ነው (ይህ ቃል በአንድ ቤተሰብ የሚገኙ ወንድሞችና እህቶችን ለመጥራት የሚውል አጠቃላይ ቃል ነው)። ወንድሞች ግለሰቦች ብቻ አይደሉም፤ እርስ በርስም የተዛመዱ ናቸው። በመጀመሪያ ክፍለ ዘመን ይኖሩ ለነበሩት አይሁዶችና አሕዛብ የቤተሰብ ትስስር ትልቅ ዋጋ የሚሰጠው ጉዳይ ነበር፤ ወንድማማችና እህትማማች መካከል ግጭቶች ሲነሡ (በቤተሰብ አንዳንዴ እንደሚከሰተው) የሚያደርጉት ነገር ችግሩን በሰላም ለመፍታት ቤተዘመድ ዘንድ ሄደው ሽምግልና ማግኘት ነበር። ከዚህ በጠለቀ መንገድ፣ ክርስቲያኖችም እንደዚሁ ለየብቻ ፈንጠር ብለው የቆሙ ግለሰቦች ሳይሆኑ የትልቁ ቤተሰብ ማለትም የእግዚአብሔር ቤተሰብ አባላት ናቸው። ያዕቆብ (የኢየሱስ ግማሽ ወንድም) ወገኖቹ የነበሩትን ክርስቲያኖች "የተወደዳችሁ ወንድሞች ሆይ" (ያዕ 1፡16) ይላቸዋል። ጳውሎስ በቆላስይስ ይኖሩ የነበሩትን ክርስቲያኖች በአካል ባያገኛቸውም "በክርስቶስ ለሆኑ ቅዱሳንና ታማኝ ወንድሞች" (ቆላ 1፡2) ይላቸዋል።

ይሁን እንጂ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በሰፊው የሚዘወተረው የክርስቲያኖች መጠሪያ ቃል "*ደቀመዛሙርት*" ነው። ከኢየሱስ ጋር ይገቡ ይወጡ የነበሩትና ለእርሱ አጅግ ቅርብ የነበሩት ዐሥራ ሁለቱ ተከታዮቹ "ደቀመዛሙርት" ተብለዋል፤ እነርሱ ብቻ ሳይሆኑም ኢየሱስን ይከተሉ የነበሩት ብዙዎች ሴቶችን ጨምሮ ደቀመዛሙርት ተብለው ተጠርተዋል (ሉቃ 8፡2-3)። እንደ

እውነቱ ከሆነ የኢየሱስን ትምህርት ስመከተል የሚሻ ማንኛውም ሰው ደቀመዝሙር ተብሎ ሊጠራ ይችላል።

ለምሳሌ፣ ኢየሱስ የተራራውን ስብከት ሲሰብክ "ከደቀመዛሙርቱ አጅግ ብዙዎች በዚያ ነበሩ" (ሉቃ 6፥17) የሚል ቃል እናነባለን። መጽሐፍ ቅዱስ በተጨማሪም ኢየሱስ አገልግሎቱን ካጠናቀቀ ከተወሰኑ ዓመታት በኋላ "ደቀመዛሙርትም ለመጀመሪያ ጊዜ በአንጾኪያ ክርስቲያን ተብለው ተጠሩ" (የሐዋ ሥራ 11፥26) ይላል። ስለዚህ ክርስቲያን መሆን ደቀመዝሙር መሆን ማለት ነው።

ሠልጣኝ

ኢየሱስ በኖረበት ዘመን ይኖሩ የነበሩ ሰዎች ደቀመዝሙር ምን ማለት እንደሆነ ያውቁ ነበር። የሮማውያን ዓለም በዘሪያቸው ተማሪዎች ወይም ተከታዮች ያስባስቡ በነበሩ ፈላስፎችና አስተማሪዎች የተሞላች ነበረች፤ እነዚህም "ደቀመዛሙርት" ተብለው ይጠሩ ነበር። መጥምቁ ዮሐንስ በዙሪያው ተከታዮች ነበሩት፤ እንደዚሁም ፈሪሳውያን (የሃይማኖት መሪዎች ቡድን) የራሳቸው ደቀመዛሙርት ነበሯቸው። ኢየሱስ የቃሉን ትርጉም በማስፋት በአርሱ የሚያምን ሁሉ ደቀመዝሙር ተብሎ እንደሚጠራ ተናገረ። ኢየሱስም በአርሱ ያመኑትን አይሁድ እንዲህ አላቸው "በትምህርቴ ብትጸኑ እናንተ በእውነት ደቀመዛሙርቴ ናችሁ" (ዮሐ 8፥31)።

ደቀመዝሙር ምንድነው? አንደኛ፣ ደቀመዝሙር ተማሪ ወይም ሠልጣኝ ማለት ነው። ኢየሱስ የቅርብ ወዳጆቹ እንዲሆኑ የጠራቸው ዐሥራሁለቱ ቀንም ሆነ ሌሊት ከአርሱ የማይለዩ ነበሩ። ከኢየሱስ የጠበቀ ወዳጅነት ነበራቸው፣ ከርሱ ጋር የሄደበት የሚሄዱ፣ አብረውት ማዕድ የሚቆርሱ፣ የሚያነጋግሩት፣ የአኗኗር ዘይቤውን የሚያስተውሉ፣ ስተሰበሰበ ሕዝብ ሲሰብክ የሚሰሙት ወዳጆቹ ነበሩ። ይሁንና ኢየሱስን ይከተሉ የነበሩት ከአርሱ ጋር መሆን ስለሚያስደስታቸው ብቻም አልነበረም። የአርሱ ደቀመዛሙርት እንደመሆናቸው ይህ ነው የሚሉት ዓላማ ነበራቸው፤ ይህም ከአርሱ መማር፣ ትምህርቱን መቀበል፣ ከአርአያው መማር፣ በተግሳጹም ራሳቸውን ማቃናት ነበር። ይህን ሁሉም ደቀመዛሙርቱ እንጂ ዐሥራ ሁለቱ ብቻ የሚያደርጉት አልነበረም። ደቀመዝሙር መሆን "ሠልጣኝ" መሆን ማለት ነው።

የዚህ ዓይነት ደቀመዝሙር እንዳንሆን የሚከለክለን ምንድነው? አውነቱን አንነጋገር ከተባለ የመጀመሪያው ምክንያት ሰንፍና ወይም ራስን መግዛት አለመቻል ነው። ትምህርቴን እንደነገሩ ነበር የማየው። የምሰጠው ማማከኛ ዞሮ ዞሮ መጨረሻዬ እንደ አባቴ ገበሬ መሆኔ ካልቀረ የሒሳብ ትምህርት፣ ሥነጽሑፍ እያልኩ ራሴን ሰምን አስጨንቃለሁ የሚል ነበር። ችግሬ ራሴን ገዝቼ ለመትጋት ባለመፈለጌ ነበር፤ ይህ ነገሬ መለወጥ የጀመረው ሕይወቴን ለክርስቶስ ስሰጥ ብቻ ነው።

ሌላው ምክንያት ምን ያህል ማወቅ እንዳለብንና ከእግዚአብሔር እውነት መመራት እንዳለብን ስላልተረዳን ይሆናል። መዝሙረኛው "የቃልህ ፍቺ ያበራል፤ ሕፃናትንም አስተዋዮች ያደርጋል" (መዝ 119፥130) ሲል ትክክል ነበር።

በሕይወት ጉዳና ስንጓዝ በርካታ መሰናክሎችና ፈተናዎች ይገጥሙናል፤ የክርስቶስ እውነት ልባችንን እንዲገዛው ካልፈቀድንለት የተሰያዩ ስህተቶችና አደጋዎች እንደሚገጥሙን ጥርጥር የለውም። ኢየሱስ እንዲህ ብሏል፦ "በትምህርቴ ብትጸኑ እናንተ በእውነት ደቀመዛሙርቴ ናችሁ፤ እውነትንም ታውቃላችሁ፤ እውነትም ነጻ ያወጣችኋል" (ዮሐ 8፥31-32)።

ተከታይ

ሁለተኛ፣ ደቀመዝሙር ሠልጣኝ ብቻ ሳይሆን "ተከታይም" ጭምር ነው። የመጀመሪያዎቹ የኢየሱስ ደቀመዛሙርት እርሱ ሰሄደበት ሁሉ ይከተሉት ነበር፤ ደቀመዝሙርነት ከዚህም የላቀ ትርጉም አለው። *ኢየሱስን መከተል ትምህርቱን መከተልም ነው።* ኢየሱስ እንዲህ ብሏል፣ "የማዛችሁን ብትፈጽሙ ወዳጆቼ ናችሁ" (ዮሐ 15፥14)። በተጨማሪም፣ "እርስ በርሳችሁ ብትዋደዱ ሰዎች ሁሉ የእኔ ደቀመዛሙርት እንደሆናችሁ በዚህ ያውቃሉ" (ዮሐ 13፥35) ብሏል።

በሌላ አባባል፣ *ደቀመዝሙር የኢየሱስን ቃል በተግባር ለመግለጥ ይሻል ማለት ነው።* በአንድ ወቅት አጅግ የተደነቀ ሳይንቲስት ቤቱ ውስጥ ግን የማያንጠባጥብ ቧንቧ መጠገን እንደማይሆንለት የተናገረ ሰው ገጥሞኛል። ይህ ሰው ዓለምና ሰውሰጧ ያሉትን በተመለከተ ስፉ እውቀት ቢኖረውም ዕውቀቱን ወደተግባር በመለወጥ ረገድ ግን ሁልጊዜ የሚሳካለት አልነበረም። ያዕቆብ እንዲህ ሲል ከተግባር የተፋታን እምነት ይተቻል፣

"ወንድሞች ሆይ፣ አንድ ሰው እምነት አለኝ በሏል ሥራ ግን ባይኖረው ምን ይጠቅመዋል? ከመንፈስ የተለየ ሥጋ የሞተ እንደሆነ ከሥራም የተለየ እምነት የሞተ ነው" (ያዕ 2፥14፣26)። ደቀመዝሙር ማለት የኢየሱስ ተከታይ ነው።

አገልጋይ

የደቀመዝሙርነት የመጨረሻው ገፅታ ይህ ነው፣ ደቀመዝሙር መሆን ማለት አገልጋይ - የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አገልጋይ መሆን ማለት ነው። ያዕቆብና ዮሐንስ ኃይለኞች ይመስላሉ፤ ለዚህም ሳይሆን አይቀርም "ወልደ ነጐድጓድ" ብሎ የሚጠራቸው (ማር 3፥17)። አንድ ቀን ኢየሱስ አገልግሎቱን ለማገባደድ ጊዜው ሲቃረብ እንደዚህ አሉት፦ "መምህር ሆይ፣ የምንለምንህን ሁሉ እንድታደርግልን እንፈልጋለን፣ . . . በክብርህ ጊዜ አንዳችን በቀኝህ አንዳችንም በግራህ እንድንቀመጥ ፍቀድልን" (ማር 10፥35፣37)። በሌሎቹ ላይ እንደነገሥታት ለመለልጠን ፈለጉ። ኢየሱስ ግን ገለጻቸውና የደቀመዝሙርነት ትርጉም ገና እንዳልገባቸው ነገራቸው። "ከመካከላችሁ ታላቅ መሆን የሚፈልግ ሁሉ አገልጋይ ይሁን" (ማር 10፥43)። የሚገርመው ደግሞ ከጥቂት ቀናት በፊት ኢየሱስ ለደቀመዛሙርቱ እንዲህ ሲል ነግሯቸው ነበረ፦ "መጀመሪያ ለመሆን የሚፈልግ፣ ከሁሉ መጨረሻና የሁሉም አገልጋይ ይሁን" (ማር 9፥35)። እግዚአብሔር ሊነግረን የሚፈልገውን በተደጋጋሚ መስማት የሚሳነን መሆኑ አያስደንቃችሁም? ደቀመዝሙር መሆን አገልጋይ መሆን ማለት ነው።

በፊታችን ያለው ሩጫ

የክርስቲያን ጉዞ የአጭር ርቀት ሩጫ ሳይሆን ማራቶን ነው። ለዚህ ተዘጋጅታችኋል? ልትዘጋጁ የምትችሉትስ እንዴት ነው? *ጉዞውን የምትጀምሩት ደቀመዛሙርቱ በመሆን ነው - የክርስቶስ ተማሪ፣ የክርስቶስ ተከታይ፣ እና የክርስቶስ አገልጋይ (ባርያ) ለመሆን ቁርጠኛ ውሳኔ ሰጥወሰኑ ነው።* እንዲህ ዓይነት ደቀመዝሙር ናችሁ? ይህን ውሳኔ ወስናችኋል? ከግብ ለመድረስስ ጨክናችኋል? ለጉዞው ተዘጋጅታችኋል የሚባለው ይህን ስታደርጉ ነው።

ደቀመዝሙርነት የሕይወት ዘመን ውሳኔ ነው። ዛሬውኑ ለመጀመር ወስኑ።

ዐሥር

የማያበቃው ተጋድሎ

"ወዳጆች ሆይ፤ እንደ እሳት የሚፈትን ብርቱ መከራ በመቀበላችሁ

እንግዳ ነገር እንደደረሰባችሁ በመቁጠር ትደነቁ።"

1ጴጥ 4፥12

ክርስትና ሕይወት የጦርነት አውድማ እንጂ የመዝናኛ ስፍራ አይደለም።

በ1959 በአገልግሎታችን በስፋቱ ተወዳዳሪ ያልነበረውን በመሳው አውስትራሊያ ያቀድነውን አህጉር አካላይ የስብከት አገልግሎት ለማካሄድ ዝግጅቶች አጠናቅቀን ነበር። በየከተማው ከእያንዳንዱ ቤተእምነት የአገልግሎት ግብገር የደረሰን ሲሆን ለዓመት ያህል ሠራተኞቻችን ለጀማ ስብከት አገልግሎቱ ዝግጅት እብረዋቸው ይሠሩ ነበር። በዐሥር ሺዎች የሚቆጠሩ የበጐ ፈቃደኛ ረዳቶች ተመልምለው ነበር፤ በየከተማው የቤት ውስጥ የጸሎት ቡድኖች ተመድበው ነበር። በሲድኒ ከተማ ብቻ አምስት ሺህ የጸሎት ቡድኖች ተደራጅተው ነበር። በተጨማሪም የስብከት አገልግሎቱን በአውስትራሊያ ለፊ የገጠርና የእርሻ ከተሞች በስልክ መስመር ለማስተላለፍ ዝግጅቶች ተደርገው ነበር። ባለቤቴ ሩት ከዓመት በፊት ኔድን ተገላግላ ስለነበር ከእኛ ጋር መሆን አልቻለችም፤ ለዚያን ያህል ረዥም ጊዜ ተለያይተን ልንቆይ እንደምንችልም አልጠበቅንም ነበር። ይሁንና እግዚአብሔር በአውስትራሊያ የአገልግሎት በር እንደከፈተልን አምነን ነበር፤ ይህን የሚጠብቀኝን አገልግሎት በትልቅ ናፍቆት እጠባበቀው ነበር።

ወደዚያ ለመሄድ ጥቂት ቀናት ሲቀሩኝ ዓይኔ ላይ የሆነ አክል ገጠመኝ። መሬቱን ሳየው እንደማዕበል መሰመር ያለው ሆኖ ነበር የሚታየኝ። ጥቂት ቆይቶም ግራ ዓይኔ ላይ ብርቱ ህመም

ተሰማኝ። ሐሊሙ ዘንድ ሄጀ የሰማሁት ነገር የሚያበረታታ አልነበረም፤ ብዙ ጊዜ የማይከሰት ካልታከመ ግን ወደዓይነሥውርነት ሊመራ የሚችል ችግር እንደሆነና ብቸኛው ህክምና ሙሉ እረፍት እንደሆነ ነገረኝ። ስለዚህም የእውስትራሊያ እገልግሎት ሰሌላ ጊዜ መተላለፍ ነበረበት፣ አገልግሎቱ ሲጀመርም የእኔ የአገልግሎት ድርሻ በእጅጉ ሊቀነስ ግድ ነበር።

ይህ ሰምን ተከሰተ? አግዚአብሔር ራሱ እንዲተንፍል አደረገ ወይስ ሰይጣን ሊያግደን እየሞከረ ነበር? ወይስ ችግሩ እኔ ዘንድ ነበር?

አሁንም ድረስ መልሱን አላውቀውም። በእርግጠኝነት የማውቀው ነገር ቢኖር እግዚአብሔር እነዚያን ያልተጠበቁ የጸጥታና የእርጋታ ሳምንታት በሌላ በምንም ሁኔታ ላገኝ በማልችለው ባልተጠበቀ መንገድ እኔን ሰማዘጋጀት ያደረገው መሆኑን ነው። በተጨማሪም በዕቅዳችን የተከሰተው መተንፍል ሰዎች በበለጠ ትጋት እንዲጸልዩ እደረጋቸው፤ መርሃግብሩ ቢቀየርም በአገልግሎቱ እግዚአብሔር በአስደናቂ ሁኔታ መሥራት ጀመረ። ይሁንና እግዚአብሔር ይህን እንዲከሰት ሰምን እንደፈቀደ ዛሬም ድረስ አላውቅም።

በአገልግሎታችን የዚህ ዓይነቱ ብርቱ እከል ሲገጥመን ይህ የመጀመሪያው ጊዜ አልነበረም፤ ሰነገሩ የመጨረሻም አልነበረም። እንዲያውም በገዛ ራሴ ሕይወትም ሆነ በአገልግሎቴ አንድ ዐይነት ችግር ሳይገጥመኝ ዐቢይ የሆነ የወንጌል አገልግሎት ያካሄድኩበት ጊዜ ትዝ አይለኝም። በአውስትራሊያ ይህ ችግር ሰምን እንደገጠመኝ እንደማላውቅ ሁሉ፣ በሌላ ጊዜም እንዲህ ያሉ እንቅፋቶች ሰምን እንደሚከሰቱ እላውቅም። እናንተም በሕይወታችሁ ተመሳሳይ ችግር ሳይገጥማችሁ አይቀርም፤ በዚህ ሕይወት እስካሰን ድረስ ማናችንም ከችግሮች ልናመልጥ እንችልም።

ግራ የሚያጋባ ነገር

ክርስቶስን ቢከተሉ ችግርና መሰናክል የማባሉ ነገሮች ተጠራርገው እንደሚወገዱ ከልባቸው የሚያምኑ ሰዎች አልፎ አልፎ ይገጥመኛል። ታዲያ "ኢየሱስ ሰላም አሰጣችኋለሁ" ሲል ይህን ማለቱ እይደለም ወይ? ይላሉ። በቂ እምነት ካለን እግዚአብሔር መከራን ከእኛ አርቆ ጤናና ብልዕግና እይሰጠንም? ሊሉም ይጠይቃሉ።

መጽሐፍ ቅዱስ ግን የዚህን ዓይነት ተስፋ አይሰጠንም - እምን፣ ሰላም እንደሚሰጠን ቢገልጽም፣ ፈተናና ግጭትም መምጣታቸው እንደሚይቀር ያስታውቀናል። ይህ እባባል ግራ የሚያጋባ ይመስላል፤ በርግጥ ግራ የሚያጋባበት ሁኔታ አለ። በርግጥስ ሰው ሰላም ሆኖሰት ሳለ ባንድ ጊዜ እንዴት ጦርነት ውስጥ ሊሆን ይችላል?

ኢየሱስ፣ "ሰላምን እተውላችኋለሁ፤ ሰላሚን አሰጣችኋለሁ" (ዮሐ 14÷27) ብሎ የተናገረውን ቃል በምናስተውልበት ጊዜ፣ ይህን መረዳት ቀላል ይሆንልናል። የሰጠን የተስፋ ቃል እውነት ነው፤ ክርስቶስን ስንከተል በእርግጥም ሰላም ይኖረናል፤ ይህም በሰጠን የተስፋ ቃል ላይ የማይናወጥና ጥልቅ መታመን ሊኖረን የምናገኘው የውስጥ ሰላም ነው። የዚህ ዓይነቱ ሰላም ወርድና ስፋቱ ከእግዚአብሔር ጋር ያለን ሰላም መመሰረት ነው። ጦርነት ላይ ያሉ አገሮች የሰላም ስምምነት ሊፈራረሙ ጦርነቱ ያበቃል። እኛም ከእግዚአብሔር ጋር ሰላም ስንመሠርት የሚሆነው ይህ ነው። ቀድሞ ከእግዚአብሔር ጋር ጦርነት ላይ ነበርን፤ አሁን ግን፤ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ከእግዚአብሔር ጋር ሰላም አለን (ሮሜ 5÷1)። በተጨማሪም፣ ከክርስቶስ ጋር ስንራመድ *በልባችን ሰላም ይኖረናል*። የከረረ የጦርነት አውድማ የነበረው ልባችን ሰላም ይሰፍንበታል። ከሌሎች ሰዎች ጋር የሚኖረን ግጭትም ያከትምና *በሰላም ከነርሱ ጋር መኖርን እንማራለን*። ክርስቶስን ስናውቀው አውነተኛ ሰላም ሕይወታችንን ይገዛዋል፤ ከእግዚአብሔር ጋር ሰላም ስንመሠርት በልባችን ሰላም ይነግሣል፤ ከሌሎችም ጋር በሰላም መኖር የምንችል እንሆናለን።

ይህ ሰላም እውነተኛ ነው፤ እግዚአብሔር ራሱ እውነተኛ የሆነውን ያህል ማሰት ነው። *ውስጣዊ* ሰላም ነው። በአስፈሪ ማዕበሎች መካከል ስናልፍ እንኳን በአረፍት የሚሞላን በነፍሳችን፤ በአእምሮአችንና በስሜታችን የሚያድር ሰላም ነው። ግን ይህን ልብ በሉ፤ ይህ ማሰት ሁልጊዜ ከመከራና ከችግር ተከልለን እንኖራለን ማለት አይደለም። እርግጥ ነው ክርስቶስ የውስጥ ሰላም ይሰጠናል፤ ይሁን እንጂ ችግርና መሠናክል የማይገበኘውን ውጫዊ (የሚታይ) ሰላም እንደሚሰጠን ግን ቃል አልገባልንም ምናልባትም ክርስቶስን ስናውቅ የሚገጥመን ችግሮች እየገዘፉ ሊመጡ ይችላሉ፤ ይህ የሚሆነው ለእርሱ ታማኝ ለመሆን መወሰናችን ከማያምነው ዓለም ጋር ጠበኞች ስለሚደርገን ነው። ኢየሱስ እንዲህ ብሏል፤ "በዓለም ሳላችሁ መከራ አለባችሁ" (ዮሐ 16÷33)። በተጨማሪም "አገልጋይ

ከጌታው አይበልጥም፤ ... እኔን አሳደውኝ ከሆነ፣ እናንተንም ያሳድዷችኋል" (ዮሐ 15፥20) በማለት አስጠንቅቋል።

መጠነ ሰፊ መንፈሳዊ ግጭት

የሕይወት ጉዞአችን፣ ለክርስቲያኖችም ሳይቀር በበርካታ ውጣውረድና የልብ ስብራቶች የተሞላው ለምን ይሆን? እንዲህ የሚያንገላቱን ፈተናዎችና መከራዎች መንስኤአቸው ምን ይሆን? ይህን ስለክርስቲያንና ፈተና በሚያወሳው ምዕራፍ በይበልጥ እንመለከተዋለን፤ በቅድሚያ ግን ብዙ ጊዜ የሚዘነጋ አንድ እውነት ልብ እንበል።

በ1985 ሩማንያን የመጐብኘት ዕድል ገጥሞኝ ነበር፤ ይህች አገር በዚያን ወቅት በኮሚኒስት አገዛዝ ሥር ነበረች። ይህን ርእዮተ ዓለም ከመቀበሏ በፊት ግን ከአንድ ሺህ ዓመት በላይ ጠንካራ ክርስቲያናዊ ትውፊት የነበራት አገር ነበረች። አዚያ ከደረስን ጥቂት ሰዓታት በኋላ አንድ የቤተክርስቲያን መሪ በመካከለኛ ዘመን የተገነቡ ካቴድራሎቻቸውን አስጐበኘን። ያሸበረቁ ባለቀለም መስታወቶች ካሏቸው የምዕራብ ካቴድራሎች በተለየ ሁኔታ፣ እነዚህኞቹ ውስጣቸውም ውጫቸውም የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪኮችንና ምስሌዎችን በሚያሳዩ ውብ ስዕሎች የተሰበጠ ነበሩ (በመካከለኛው ዘመን፣ በአውሮፓ መጽሐፍ ቅዱስ በቤታቸው የነበራቸው ወይም ማንበብ የሚችሉ ሰዎች በጣም ጥቂት ሰዎች ስለነበሩ፣ ካህናት የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪኮችን ለማስተማር ይጠቀሙ የነበሩት እነዚህን የጥበብ ሥራዎች ነበር)።

በተሰይ ልዩ ስሜት የፈጠረብኝ አንድ ስዕል ነበር። ይህ ስዕል ጠቅላላውን ግድግዳ የሚሸፍን ሲሆን ወደ መንግሥተ ለማያት በሚያወጣው መሠላል ላይ ሰዎች ወደላይ ለመውጣት ሲታገሉ ያሳያል። በርካታ መላእክት እነዚህን ሰዎች ከብበው ደረጃዎቹን ሲወጡ ሊያበረታቱአቸውና ሊረዱአቸው ይታያሉ፡ ከታች ደግሞ ስፍር ቁጥር የሌሳቸው አጋንንት እግራቸውን እየጐተቱ ከመሰላሉ እውርደው ወደእሳት ሊጥሏቸው ይተናነቁአቸው ነበር።

ይህ ምስል ልበ ወለዳዊነት ቢጐላበትም አንድን አውነት ጥርት አድርጐ ያስተውሰናል፤ ይህም *እኔና እናንተ በዓይናችን በማናየው ሆኖም በዚህች ገሳኔት በሚከለተው ሀሉ ላይ ተዕዕኖ በሚያሳድር መጠነ ሰፊ መንፈሳዊ ግጭት ውስጥ እንዳለን ነው።* ይህም በመልካምና በክፉው፣ በርቱዕና በወላዋዩ፣ በሕይወትና

በሞት፤ በመንግሥተ ለማያትና በገሃነም መካከል የሚካሄደው ትንንቅ ነው። ከሁሉም በላይ ግን በእግዚአብሔርና በሰይጣን መካከል የሚካሄደው የዘመናት ግጭት ነው። የትኛውም የሆሊውድ የፈጠራ ድራማ ሊሆን ከሚችለው በላይ፣ ይህ እውነተኛው የዓለማት ጦርነት ነው። መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ በማለት ይገልጸዋል፤ "ተጋድሎአችን ከሥጋና ከደም ጋር ሳይሆን ከዚህ ከጨለማ ዓለም ገዦች፤ ከሥልጣናትን ከኃይላት እንዲሁም በሰማያዊ ስፍራ ካሉ ከርኩሳን መናፍስት ሠራዊት ጋር ነው" (ኤፌ 6፥12)።

መጽሐፍ ቅዱስ ስለዚህ ተጋድሎ የሚሰጠን የደበዘዘ ስዕል ብቻ ነው፤ በምናባችን ፈጠራ እንዳናከልበትና ከተፈቀደው በላይ እንዳንሄድ መጠንቀቅ ይኖርብናል። ከመጠን በላይ ስለዚህ ነገር እያስላሰልን ልንወስድበት አይገባም። ይሁንና መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚጠቁመን ይህ ምድራዊ ጦርነት ከዚህ የገዘፈ ሰማያዊ ጦርነት ንዕብርቅታ ብቻ ነው። ይህ ጦርነት የመጨረሻው ውጊያ ተጠናቅቆ ሰይጣን ለዲያብሎስና ለመላእክቱ ወደተዘጋጀው የዘላለም እሳት (ማቴ 25፥41) እስኪጣል ድረስ አያቋርጥም።

ይህን የምገልጸው ለምንድነው? ምክንያቱም *እኔና እናንተ በዚህ ተጋድሎ ውስጥ እየተሳተፍን ስለሆነ ነው።* ተጋድሎው ለማያዊ ብቻ ሳይሆን ግለሰባዊም ነው። ሰይጣን እውን ህልውና አለው፤ ከእግዚአብሔር ሊነጥሰን የማይፈነቅለው ድንጋይ የለም። በእውነት ሕይወታችንን ለክርስቶስ ከሰጠን ድነታችን በተደላደለ መሠረት ላይ ይቆማል፤ ምክንያቱም በእኛ ማንነት ላይ ሳይሆን ክርስቶስ በመስቀል ላይ በሠራው ሥራ ላይ ስለሚቆም ነው። ያም ሆኖ ሰይጣን እኛን ለማዳከም፣ በመንፈስ ሽባና የማንጠቅም ሊያደርገን ከመጣር የማያርፍበት አፍታ እንኳን የለውም።

ሦስት ስህተቶች

ሁላችንንም ስለማመለክት ይህን የመንፈሳዊ ተጋድሎ ጉዳይ በቀላሉ ልናየው አይገባም። ስለዚህ ነገር ተገቢ መረዳት ከሌለን በርካታ ስህተቶች ውስጥ እንገባለን፤ እግዚአብሔር ክርስቶስን እንድንመስል የወሰነልን ዕቅድ ሊጨናገፍ ይችላል።

እንዳንድ ሰዎች የሚፈጽሙት የመጀመሪያው ስህተት ይህ ነው፤ ክፉው የለም ይላሉ። ክፉው የሚባል ነገር የተሳሳተ አመለካከት (እምነት) ነው ወይም የበጐ ነገር አለመኖር ነው ብለው

ያምናሉ። ሌሎች ደግሞ ክፉው የሚባለው የሥነ አዕምሮ ወይም የሚሀበራዊ ቀውስ ሌላው ስም ነው ይላሉ። ይሁን እንጂ፣ በክፉው የጭከና ድርጊት ውስጥ በሚያልፉበት ጊዜ ምንም መልስ አይኖራቸውም፣ ምክንያቱም መኖሩንም ሆነ በስው ዘር ላይ የሚያስከትለውን እስቃቂ ተጽዕኖውን መቀበል ስለማይችሉ ነው። የክፉውን የተራቆተ እውነት ብንክድ፣ ለመዋጋት ክቶ የተዘጋጀን አንሆንም። እንድ ወዳጄ እንድ ጊዜ በእባቱ ተንከል በተሞላና ስግብግብ ብቻ ሳይሆን ፍጹም ክፉ በሆነ ባሕርይ ምክንያት እንደተጐዳ እጫውቶኛል። ይህ ወዳጄ ክርስቶስ ከዚህ ሥቃይ ነፃ ስላወጣው ያለው እክብሮትና ምስጋና ወሰን የለውም።

ሁስተኛው ስህተት ደግሞ ከመጀመሪያው ተቃራኒ ነው፣ ክፉ አለ፣ እናም ሉኛ ከቶ ልናሸንፈው አንችልም የሚል ነው። አንዳንዶች እግዚአብሔርና ሰይጣን እኩል ናቸው፣ ሁለቱ ሳይሸናነፉ ማለቂያ በሌለው ትግል ውስጥ ናቸው ብለው ያምናሉ። ምንም በጐ ነገር የለውምና ክፉን መዋጋትስ ለምን እስፈለገ? ይላሉ። እነኚህ ስዎች ማየት የተሳናቸው ነገር ቢኖር፣ ሰይጣን ኃያል ሊሆን እግዚአብሔር ግን ሁሉን ቻይ መሆኑን ነው። ከዚህም በላይ ኢየሱስ በሞቱና በትንሣኤው እስቅነትንና ሥልጣናትን ገፎ፣ ድል እንደነሣቸው (ቆላ 2÷15) ዘንግተዋል። በምዕራፍ ዐራት እንደተመለከትነው፣ ሰይጣን እስ (እውን ነው) - ሆኖም የተሸነፈ ጠላት ነው! ሰይጣን እሁንም በሥራ ላይ ነው - የመጨረሻውም ፍርድ እጠራጣሪ እይደለም። ሕይወት ጀርባዋን ብታዞርባችሁ ተስፋ መቁረጥ የለባችሁም፤ ክርስቶስን ካወቃችሁ በርግጥ ታሸንፋላችሁ!

ሦስተኛው ስህተት ደግሞ ምናልባት በጣም አደገኛው ነው፣ ስግንዛቤ ማነስ የተነሣ ክርስቲያኖች ሳይቀሩ በዚህ ስህተት ወስጥ ሲገቡ ይስተዋላል። እንዲህ ይላሉ፣ ክፉው እውን ነው፣ ግን እራሴ እዋገዋስሁ። እንዲረዳን በእግዚአብሔር በመደገፍ ፋንታ፣ በራሳችን እንመካለን። ከኃጢአት እኳያ ፍጹም ተስፋቢስነታችንንና የመንፈስ ቅዱስ እርዳታ እንደሚያስፈልገን በመገንዘብ ፋንታ በራሳችን ጥንካሬ ድል ለመቀዳጀት መሞከር እንዳለብን እናስባለን። እግዚአብሔር ለድል የሚያስፈልገንን ብቃት ሁሉ እንደለጠን ከመገንዘብ እንስታለን።

እግዚአብሔር ክፈታችን በዘረጋልን በዚህ የሕይወት ጉዞ ላይ የሚያጋጥሙንን እደጋዎች አላንስን እንመልክታቸው። ክፉው እየሠራ ያለው በተለያየ መንገድ ነው - እንዳንዱ በግሃድ፣ ብዙውን ጊዜ ግን በድብቅ እየሠራ ነው። የክፉው ዓላማ ግን ሁሌም አንድ

ነው፣ እኛን ከእግዚአብሔር ለመለየት ይሠራል። ሰይጣን እኛን ማደናገር ከቻለ፣ ወይም ክመንገዳችን ካዘነፈን፣ ወይም ተስፋ ካስቆረጠን፣ ወይም በፈተና ውስጥ ክክተተን - ያኔ ተሳክቶለታል።

ነገር ግን እግዚአብሔር ሊረዳን መፈለጉን ዝቅ እድርገን ልንመለክት እይገባም! እርሱ ይወዳናል፣ ሊረዳንም ይፈልጋል። የነቢዩ ሶፎንያስ መልዕክት፣ "አምላክሽ እግዚአብሔር በመካከልሽ ታዳጊ ኃያል ነው፣ በደስታ በእንቺ ደስ ይለዋል፣ በፍቅሩም ያርፋል፣ በእልልታም በእንቺ ደስ ይለዋል" (ሶፎ 3÷17) የሚለው፣ በነቢዩ ዘመን ለኖሩ ብቻ ሳይሆን ዛሬም ለኛ እውን ነው።

ስተጋድሎ ዋንካሬ

በቅርቡ አንድ ስው፣ "ስህተቴ ምንድነው? ከሁለት ዓመት በፊት ሕይወቴን ስኢየሱስ ስጥቼ ነበር፣ ነገር ግን ትክክል የሆነውን ነገር ለመሥራት የቻልክ አልመስለኝም" ብሎ ጻፈልኝ። ምናልባት እናንተም እንዲሁ ተስምታችሁ ይሆናል።

ስተጋድሎው ጥንካሬ የምናገኘው እንዴት ነው? በጉዞ ላይ ፀንተን የምንቀጥለው እንዴት ነው? ስለዚህ ጉዳይ ሁልጊዜ አስባስሁ፣ የማስበው የራሴን መንፈሳዊ ትግል እያስላስልክ ብቻ ላይሆን የሌሎችንም ጭምር ነው። በየቀኑ በዚህ ዓይነት መንፈሳዊ ትግል ውስጥ እያስፋን ድል የምንቀዳጀውስ እንዴት ነው?

እኔ እንደማምነው፣ *መልሱ ቀላል ነው፣ ለመንፈሳዊ ድል ቁልፉ ከእግዚአብሔር ጋር ተጣብቆ መኖር ወይም አግዚአብሔርን መቅረብ ነው።* መጽሐፍ ቅዱስ ይህን በተመለከተ፣ "እንግዲህ ለእግዚአብሔር ተገዙ፣ ዲያብሎስን ግን ተቃወሙ፣ ከእናንተም ይሸሻል፤ ወደ እግዚአብሔር ቅረቡ ወደ እናንተም ይቀርባል" (ያዕቆብ 4÷7-8) በማለት ይገልጻል። *ተገዙ . . . ተቃወሙ . . . ቅረቡ* - መንፈሳዊ ድል ለመቀዳጀት እነዚህን ማድረግ አለብን።

ስእግዚአብሔር መገዛት ምን ማለት እንደሆነ አስቀድመን ተመልክተናል። መገዛት ማለት ሁለተናችንን ለክርስቶስ ማስረክብ ማለት ነው። መገዛት ማለት ፈቃዳችንን መተውና ራሳችንን ሰርስ ሥልጣን አላልፎ መስጠት ማለት ነው። ሁለተናችሁን ለክርስቶስ ጌትነት አስገዝታችኋል? ይህ መሆን ያለበት ቀዳማ. ርምጃችሁ ነው።

ከዚያ ቀጥሎ *ዲያብሎስን እንድንቃወም* ተነግሮናል። ይህን የምናደርገው እንዴት ነው? "መቃወም" የሚለውን ቃል አንድ ወታደር በሚጠቃበት ጊዜ የሚሰጠውን አፀፋዊ ምላሽ ወይም በጠላት ላይ ያለውን የፀና አቋም ለመግለጽ የምንጠቀምበት ነው። ልክ አንድ ወታደር አጥቂውን እንደሚቃወም፣ እንዲሁም እኛ የዲያብሎስን ጥቃት እንድንቃወም ታዘናል። በምንቃወመው ጊዜ፣ መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚለው፣ ሰይጣን በሸንፈት ከኛ ይሸሻል።

በመጨረሻም፣ *ወደ እግዚአብሔር እንድንቀርብ* ተገልጸልናል። ልብ በሉ፣ ወደ እግዚአብሔር አብዝታችሁ በቀረባችሁ መጠን፣ ከዲያብሎስ እየራቃችሁ ትገኛላችሁ። ይህ ማለት የዲያብሎስ ፈተና ያበቃል ማለት ግን አይደለም። ድል ለማድረግ የሚሞክርበት ዕድል ጨርሶ ተዳክሟል ማለትም አይደለም። መዝሙረኛው፣ "መሐሪዬና መሸሸጊያዬ፣ መጠጊያዬና መድኃኒቴ፣ ረዳቴና መታመኛዬም" (መዝ 144፡2) እንዳለው ለሰሆነ ነው።

ለብቻ ከእግዚአብሔር ጋር

ወደ እግዚአብሔር የምንቀርበው እንዴት ነው? የሚለው ጥያቄ ላይነላ የሚቀርበት ጊዜ የለም። *በመጀመሪያ፣ ሁለት ጠቃሚ እውነቶችን ልብ እንበል። አንደኛው፣ ዘርስቶስን ካመንቅሁ ከእግዚአብሔር ጋር ግላዊ ወዳጅነት መስርታችኋል* ማለት ነው። እግዚአብሔር በሩቅ የተቀመጠ፣ ከእናንተ ጋር ምንም ላለመሥራት በመፈለግ ራሱን የለወረ አካል አይደለም። እርሱ አፍቃሪ ለማያዊ አባታችሁ ነው፣ አናም አሁን አንኳን ልጁ እየፀለየላችሁ ነው። በመሆኑም፣ በመጽሐፍ ቅዱስ እንደተገለጸው፣ "በቅን ልብ ወደ እግዚአብሔር እንቅረብ፣ የተሰፋን ቃል የሰጠው የታመነ ነውና" (ዕብ 10፡22) ነው። ወደ እግዚአብሔር ልትቀርቡ ትችላላችሁ፣ ምክንያቱም እንድታደርጉ እርሱ ይፈልጋልና።

ሁለተኛው እውነት ይህ ነው፦ በክርስቶስ ወንድሞችና እህቶች ከሆኑት ጋር ደግሞ ግላዊ ሕብረት ይኖራችኋል። ወደ እግዚአብሔር ከምንቀርብባቸው መንገዶች አንዱ ከክርስቲያኖች ጋር የምናደርገው ሕብረት ነው - በአንድነት በመፀለይ፣ በአንድነት በማምለክ፣ ቃሉን በሕብረት በማጥናት፣ ሸክሞቻችንን በመሸካከም፣ አንዱ ሌላውን በግበረ-ገታት ማለት ነው።

እነዚህ ሁለቱ እውነቶች በልባችን እንዳሉ ሆነው፣ ወደ እግዚአብሔር የምንቀርበው እንዴት ነው? *ቁልፉ ነገር ከእርሱ ጋር ለብቻ በመቆየት ነው።* ለአዲስ ክርስቲያን መጠነኛ የሆነ ምክር መስጠት ካለብኝ የምመክረው ይህንን ነው፣ "*በየቀኑ ለብቻህ ከእግዚአብሔር ጋር የምትቆይበትን ጊዜ ሥርዓት አዳብር*" አለዋለሁ። እናንተ ይህንን ጊዜ ብትፈልጉ የፀጥታ ጊዜ፣ ወይም የመንፈሳዊ ልምምድ ጊዜ፣ ወይም የፊሊጋችሁትን ሌላ ስም በሉት፣ ግን በየዕለቱ ከእግዚአብሔር ጋር ለብቻ የምናደርገው የግንኙነት ቆይታ ጊዜ ምትክ የሌለው ነገር ነው።

ይህንን ልምምድ እንዴት ልታዳብሩ ትችላላችሁ? አንደኛ፣ ሰዓት መድቡለት። አርግጥ ነው፣ ምናልባት ሥራ በሚበዛባት ቀን ፈታ የምታጡበት ይሆንና ዐሥር ደቂቃ አንኳን ማግኘት አይቻልም ይሆናል። ነገር ግን ትክክለኛው ጥያቄ ይህ ነው፣ ከእግዚአብሔር ጋር የሚኖራችሁ ወዳጅነት ምን ደህል አስፈላጊያችሁ ነው? ለምግብና ለሌሎች አስፈላጊ ናቸው ብላችሁ ለምታስቡአቸው ነገሮች ጊዜ ታገኛላችሁ። በእያንዳንዱ ቀን 1440 ደቂቃዎች አሉ፣ ከሰማያዊ አባታችሁ ጋር ለመሆን ዐሥር ደቂቃ ልታገኙ አትችሉም? ትርፍ ለዓት አስኪኖራችሁ አትጠብቁ፣ ምናልባት ከቶ ላይኖራችሁም ይችላል! ይልቅስ በየቀኑ ለሰዓት መድቡ፣ የምትመድቡበት ሰዓት የማትረበሽበት፣ ባልደከመና በነቃ አእምሮ የምትሆኑበት መሆን አለበት። እንቅልፍ እንቅልፍ በሚላችሁ ጊዜ አይሁን፤ እግዚአብሔር በቀን ውስጥ ከሰጠን ደቂቃዎች ውስጥ ምርጡ ጊዜ አይገባውምን?

ሁለተኛ፣ ዝግጅት ይኑራችሁ። እኔ በየቀኑ ከእግዚአብሔር ጋር በግል ባለኝ የግንኙነት ጊዜ ሦስት ነገሮችን አደርጋለሁ፣ *መጽሐፍ ቅዱስ አነባለሁ፣ እፀልያለሁ፣ እና አለሳስላለሁ* (አገናዝባለሁ)። ቅደም ተከተሉ ሁሌ ተመሳሳይ ላይሆን ይችላል፣ ባንድ ተግባር ላይ ለፊ ጊዜ ልወስድ እችላለሁ፣ ነገር ግን ሦስቱ ነገሮች ለኔ አስፈላጊ ናቸው። መጽሐፍ ቅዱስ በምናነብበት ጊዜ፣ እግዚአብሔር ይናገረናል፣ ድምፁንም ልንለማ ይገባናል። አንድ ጠዋት ከቤታችን አጠገብ ወዳለው የኮንፍራንስ ማዕከል ስጓዝ፣ አንድ አንጋፋ ለባኪ መጽሐፍ ቅዱስ ሲደነብ እየሁት። ተናገርኩት፣ አርሱ ግን አልመለሰልኝም። በኋላ እንዲህ ሰል ጠየቅኩት፣ እናድጀህ ይሆን!? አርሱም፣ "በፀሎት ላይ ብሆን፣ ለእግዚአብሔር እየተናገርኩ ስለማሆን ለተናገርከኝ በወቅቱ መልስ አስጥህ ነበር። መጽሐፍ ቅዱስ በማነብበት ጊዜ ግን እግዚአብሔር እየተናገረኝ ነው" አለኝ። ይህ ለባኪ ጥሩ ነጥብ አለው፣ እግዚአብሔር

በማናገረን ጊዜ መሉ ለመሉ የሆነ መሰጠታችንን (ትኩረታችንን) ይፈልጋል።

ፀሎትና ማለላለል አስፈላጊ ናቸው። በምንፀልይበት ጊዜ፣ ለእግዚአብሔር እንናገራለን - እናም በልባችን ያለውን ደስታና ሸክም እንገልጽለታለን። በምናለላስልት ጊዜ የእግዚአብሔርን ቃል እናመነጭርካለን፣ በሕይወታችንም ተግባራዊ ለማድረግ እንዲረዳን እንጠይቀዋለን። እንዳንድ ሰዎች እግዚአብሔር ምን እንዳስተማራቸው በማሰታወሻቸው መዝገበው ይይዛሉ። ብዙዎች ደግሞ ለማንና ለምን እንደፀለዩ የፀሎት ዝርዝር ይይዛሉ (የእግዚአብሔርን መልስ ደግሞ ይመዘግባሉ)።

በመጨረሻም፣ በየዕለቱ በሞላ ጊዜአችሁ የእግዚአብሔርን መገኘት ልትለማመዱ ይገባል። መዝሙረኛው እንዲህ አለ፣ "እቤቱ ሕግህን እንደምን እጅግ ወደድሁ! ቀኑን ሁሉ እርሱ ትዝታዬ ነው" (መዝ 119፥97)። መጽሐፍ ቅዱስ፣ ያለማቋረጥ ፀልዩ (1ተሰ 5፥17) ይለናል። ሁልጊዜ ከአንድ ሰው ጋር በምንጋገርበት ጊዜ እንኳን፣ በፀጥታ ለሌሎች ስፀልይ ራሴን አገኘዋለሁ። በዕለቱ ማለዳ ያነበብኩትን የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ በአእምሮዬ አሰላስለዋለሁ። ያልተጠበቀ ነገር በሚከሰትበት ጊዜ፣ ወዲያውኑ ለእግዚአብሔር አነግረዋለሁ፣ የርሱንም ጥበብ እሻለሁ። መጽሐፍ ቅዱስ፣ "እግዚአብሔር ለሚጠሩት ሁሉ በእውነት ለሚጠሩት ቅርብ ነው" (መዝ 145፥18) ይላልና። በየቀኑ በያንዳንዱ ለዓት የእግዚአብሔርን መገኘት ተለማመዱ።

ሰላም በመጀብ ውስጥ

ከቶ አትዘንጉ፣ ኢየሱስ ዳግመኛ በሚመጣበት ጊዜ ብቻ የሚያከትመው በጣም ብዙ የማይታዩ መንፈሳዊ ትግሎች (ግጭቶች) በገዛእችን ያጋጥሙናል። ነገር ግን ከቁጥጥራችን በላይ በሆኑ ኃይላት ፍላጐት ተሰፋ በሌለን ሁኔታ ተጠፍረን የተያዝን አይደለንም። ይልቅስ ምርጫ ያለን ነን፣ በየዕለቱ ምርጫ አለን - ምርጫው ወደ እግዚአብሔር መቅረብ ወይም ከእርሱ መራቅ ነው።

ለሰይጣን ዕድል ፋንታ አትስጡት፣ ወደ እግዚአብሔር ለመቅረብ ራሳችሁን አስገዙ። እርሱ ብቻ ዋሰትናችሁ ነው።

ወሥፉ ስንዱ

አስተማማኝ መሪያችን

ሕግህ ለሰንፈ መብራት፣ ለመንገዴ ብርሃን ነው።

(መዝ 119፥105)

እምነት እንደ ለምለም አፈር በሆነው በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ ሊተከል ያድጋል።

የዳንነው ብቻ ሳይሆን የምንኖረውም በእምነት ነው፤ ምክንያቱም በእያንዳንዱ መታጠፊያ ላይ የእግዚአብሔር ጸጋና እርዳታ ያሻናል። መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚነግረን፣ "የምንኖረው በእምነት እንጂ በማየት አይደለም" (2ቆሮ 5፥7)።

ታዲያ እምነታችን የሚያድገው እንዴት ነው?

እምነታችን ሊያድግ ይችላል?

እንድ ሰው በቅርቡ እንዲህ ሊል ጻፈልኝ፣ "እምነቴ ደካማ ነው፤ በእምነት መጠንከር እፈልጋለሁ፤ ግን ይህን ማድረግ የምችለው እንዴት ነው? ይህ የዚህ ሰው ብቻ ሳይሆን ስፍር ቁጥር የሌላቸው ክርስቲያኖች ጥያቄ ነው። እምነት ለተለዩ ሰዎች ብቻ የሚሰጥ ነገር ነው? እምነት ማለት ጥርጣሬን ማዳፈንና የሌለ ማስመሰል ማለት ነው? እምነት ሊያድግና ሊጠነክር ይችላል?

ለመጨረሻው ጥያቄ መልሱ አዎን ሊያድግ ይችላል ነው። ምክንያቱም እግዚአብሔር እምነታችንን እንዲያድግ ሰለሚፈልግ ነው። በተጨማሪም ለእምነታችን ማደግ የሚያሰፈልገንን ሁሉ አቅርቦልናል። እነዚህ ጸጋዎች የተካነ የእንጨት አናፂ እንደሚጠቀማቸው መሣሪያዎች፣ የገረበጡና ቅርጽ የለሽ እንጨቶችንም ያማሩ አድርገው መቅረጽ የሚችሉ ናቸው።

መጽሐፍ ቅዱስ - የእግዚአብሔር መሣሪያ

እምነታችንን ለማጠንከር እንዲረዳን እግዚአብሔር የሰጠን *የመጀመሪያ መሣሪያ መጽሐፍ ቅዱስ* ነው። *መጽሐፍ ቅዱስ* ለመንፈሳዊ እድገት ወሳኝ ነው። በጣም ወሳኝ በመሆኑ ያለእርሱ ዘላቂ መንፈሳዊ ብለለት ልናገኝ እንችልም። *እምነታችን በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ ሥር ሰደ ካልተተከለ፣ ከመሬት እንደተነቀለ ተክል ይጠወልጋል።* ከፈተናና ከጥርጣሬ ሊጠብቀን የሚችለው በእግዚአብሔር ቃል ላይ የተመሠረተ ጠንካራ እምነት ብቻ ነው። አለዚያ ግን "በማዕበል ወደፊትና ወደኋላ እየተነዳን፣ በልዩ ልዩ ዐይነት የትምህርት ነፋስ፣ በሰዎች ረቂቅ ተንኰልና ማታለል ወዲያና ወዲህ እየተንገዋለልን" (ኤፌ. 4፡14) የምንቀር እንሆናለን።

እምነታችሁ እንዲያደግ ተፈልጋላችሁ? እንግዲያውስ *መጽሐፍ ቅዱስ* እለምሮአችሁንና ነፍሳችሁን ሙሉ በሙሉ ይቆጣጠር። በሕይወት ዘመኔ በእለምሮዬ ተቀርጸው ከዘለቁ ትውስታዎቼ አንዱ እናቴ በምትወደው ወንበሯ ላይ በየዕለቱ በፀጥታ መጽሐፍ ቅዱሷን ማንበቧ ነው። *መጽሐፍ ቅዱስ* እንዲህ ይላል፣ "እምነት የሚገኘው መልእክቱን በመስማት ነው፤ መልእክቱም የክርስቶስ ቃል ነው" (ሮሜ 10፡17) እምነት እንዲሁ አይገኝም፤ የሚያደገው ሰም በሆነ በእግዚአብሔር ቃል እፈር ላይ ሲተከል ነው።

ለመጽሐፍ ቅዱስ አክብሮት ሊኖረን ያስፈልጋል! ለበርካታ ክፍለ ዘመናት ተራ ምለመናን መጽሐፍ ቅዱስ አልነበራቸውም ነበር፤ መጽሐፍ ቅዱስ በአጅ ይገለበጥ ስለነበር በጣም ውድ ነበር። ለለዚህም የነበራቸው ብቸኛ አማራጭ ቤተክርስቲያን ሄደው ስብከት መለማት ነበር። ይሁንና የማተሚያ ማሽን መፈልሰፍ ይህን ሁኔታ በመለወጡ ዛሬ መጽሐፍ ቅዱስ በዓለም ዙሪያ በሚገኙ በርካታ ቋንቋዎች (በበይነመረብ ላይቀር) በቀላሉ ይገኛል። ይሁን እንጂ ብዙ መጽሐፍ ቅዱሶች ላይከፈቱና ላይነበቡ የሚቀሩ ይመለከኛል። በእናንተ ሕይወት ግን ይህ መሆን የለበትም!

የእግዚአብሔር ቃል ኃይል

መጽሐፍ ቅዱስ ለመንፈሳዊ ሰድገታችን ይህን ያህል ወሳኝ የሆነው ለምንድነው? አንደኛው ምክንያት ይህ ነው። በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ ሕይወትን የመለወጥ ኀይል አለ። ቃሉ እንደ እሳት፣ ድንጋይንም እንደሚያደቅቅ መዶሻ አይደለምን? (ኤር 23፡29)።

እግዚአብሔር ሲናገር፣ ለማያት ተፈጠሩ። እግዚአብሔር ሲናገር፣ ቀይ ባህር ተከፍሎ እስራኤላውያን ከግብፅ ባርነት አመለጡ። እግዚአብሔር ሲናገር ኢየሱስ ክርስቶስ ከመታን ተነሣ። እግዚአብሔር ሲናገር በጥላቻ ተሞልቶ ክርስቲያኖችን ያለደድ የነበረው ሳውል፣ ሐዋርያው ጳውሎስ ሆኖ ተሰወጠ። በርግጥም በእግዚአብሔር ቃል ኃይል አለ። በስብከቱ ወቅት የመጽሐፍ ቅዱስን ቃል ስጠቅስ፣ መንፈስ ቅዱስ እነኚህን ቃላት ወስዶ በራሱ ኃይል እንደሚጠቀማቸውና ለዎችን ወደ ንስሓ ለውጥ እንደሚመራ አውቃለሁ። መጽሐፍ ቅዱስን በግሌ በጸሎት ላጠናም፣ እግዚአብሔር በእኔ ሕይወት ለውጥን ለማምጣት እንደሚጠቀምበት አውቃለሁ። በእናንተም ሕይወት ይህን ያደርጋል።

መጽሐፍ ቅዱስ ምንድነው?

መጽሐፍ ቅዱስን ከሌሎች *መጽሐፍት* የሚለየው ምንድነው? *መጀመሪያ* ለንመለከተው ከመጠኑ ክብደት ውጪ ከሌሎች መጽሐፍት የሚለየው ነገር ያለ አይመለልም። ብዙ ጊዜ ከበርካታ ዓመታት በፊት ለለተከናወኑ ሁነቶች የሚነግረን በመሆኑ ለዛሬ ዘመን ምን ፋይዳ ሊኖረው ይችላል ልትሉም ትችላለችሁ። ይሁንና ለዎች በየዘመኑ መልእክቱ ምትክየለሽ ዋጋ ያለው ሆኖ እግኝተውታል፤ በዘመናት ሁሉ በግለሰቦችና በማህበረሰቦች ላይ ታላቅ የለውጥ ቀለቃሽ ሆኗል። ይህ ለምን ሆነ? *መጽሐፍ ቅዱስ* ምንድነው?

በመጀመሪያ ደረጃ መጽሐፍ ቅዱስ የመጻሕፍት ስብስብ ሲሆን በመቶ ዓመታት ዘመን በበርካታ ጸሐፍት የተደረሰ ነው። እንዳንዶቹ መጻሕፍት አጭር (ግማሽ ገፅ) ሲሆኑ ሌሎቹ ግን ረዣዥም ናቸው። ይሁንና በዓይነትና በመጠን ቢለያዩም፣ ቀረብ ብላችሁ ስትመረምሩአቸው በጋራ የሚያስተሳስር እንድ ጭብጥ ታገኙባቸዋላችሁ፣ ይህም *እግዚአብሔር ከሰው ዘር ጋር ያለው ግንኙነት ነው።*

የመጽሐፍ ቅዱስ መጻሕፍት ለተጻፉበት ዘመን የነበራቸውን ያህል ለዛሬ ዘመን ለውም ትርጉም እዘል የሚያደርጋቸው እንድ ምክንያት እለ። የመጽሐፍ ቅዱስ ጭብጥ ጊዜ የማይሽራቸው ጥያቄዎች ናቸው፤ እኛ ማን ነን? ከየት መጣን? እዚህ ያለነው ለምንድነው? የት እንሄዳለን? እንዴት መኖር ይገባናል?

ከነዚህ የበለጠ ዋጋ ያለው ጥያቄ ልታለቡ ትችላላችሁ? ታዲያ እንዴት ችላ ልንላቸው እንችላለን?

የእግዚአብሔር ቃል

መጽሐፍ ቅዱስ ግን ከዚህም በበለጠ ምክንያት ዋጋ ሊሰጠው ይገባል፤ *መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል ነው*። እርግጥ ነው የተደረሰው በተለያዩ ሰዎች ነው፤ *ይሁን እንጂ ከሰዎቹ በሰተጀርባ ሌላ ደራሲ ማለትም የእግዚአብሔር መንፈስ አለ*። እነኚህ ሰዎች ለራሳቸው ሳይታወቃቸውም እንኳን እግዚአብሔር ይመራቸው ስለነበር የሚጽፉት የራሳቸውን ቃል ሳይሆን የእግዚአብሔርን ቃል ነበር። ሐዋርያው ጴጥሮስ እንዲህ በማለት ይገልጸዋል፦ "ከሁሉ አስቀድሞ ይህን ልታውቁ ይገባችኋል፤ በመጽሐፍ ያለው የትንቢት ቃል ሁሉ ማንም በገዛ ራሱ መንገድ የሚተረጉመው አይደለም፤ ምክንያቱም ትንቢት ከእግዚአብሔር የተላኩ ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ ተመርተው ተናገሩት እንጂ ከቶ በሰው ፈቃድ የመጣ አይደለም" (2ጴጥ 1፥20-21)። እግዚአብሔር እኛ በምንረዳው ቃል ተናግሮናል፤ እነዚህም ቃላት በመጽሐፍ ቅዱስ ተካትተዋል።

መጽሐፍ ቅዱስ ሰዎች ስለ እግዚአብሔር ያሏቸው አስተሳሰቦች ጥርቅም ወይም ሰዎች በየዘመናቱ ለኑሮ መርህነት የቀረጹት *መመሪያ አይደለም*። ይልቁንም *የእግዚአብሔር ቃል ነው*፤ ልዩነቱም በዚህ ነው። ይህም ማለት መጽሐፍ ቅዱስ በሚያነሳቸው ጉዳዮች ሁሉ ለኛ ባለሥልጣን ነው ማለት ነው። ይህም ማለት መጽሐፍ ቅዱስ እንዴት መኖር እንዳለብን የሚያሳየን መመሪያ ነው ማለት ነው። ከሁሉም በላይ መጽሐፍ ቅዱስ ስለእግዚአብሔርና እግዚአብሔር በክርስቶስ ስላዘጋጀልን መዳን የሚያስተምረን መመሪያችን ነው። ብሉይ ኪዳን ስለክርስቶስ መምጣት ይጠቁመናል፤ አዲስ ኪዳንም ስለመምጣቱ ይነግረናል። ከዘፍጥረት እስከ ራእይ እግዚአብሔር የጠፋውን የሰው ልጅ ወደራሱ የመመለስ ታላቅ ዕቅዱን ይተርክልናል። የመጽሐፍ ቅዱስ ማዕከላዊ ርዕሰ - ጉዳይ ድነት ሲሆን፤ ማዕከላዊ ሰብእ ደግሞ ክርስቶስ ነው።

መጽሐፍ ቅዱስ ለኛ የቀረበልን የእግዚአብሔር ገፀበረከት ነው። ከእግዚአብሔር የመጣ በመሆኑ፤ የሚያመለክተውም ወደ እግዚአብሔር ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ስለራሱ እንዲህ ይላል፦ "ቅዱሳት መጻሕፍት፤ ለማስተማር፤ ለመገሠጽ፤ ለማቅናትና በጽድቅ መንገድ ለመምከር፤ ይጠቅማሉ፤ ይኸውም የእግዚአብሔር

ሰው ሰመልካም ሥራ ሁሉ ብቁ ሆኖ እንዲገኝ ነው" (2ጢሞ 3፥16-17)።

ልንተማመንበት እንችላለን?

መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል በመሆኑ፤ ለይጣን የዚህን ተቃራኒ እንድናምን ሊያደርገን ቢሞክር መደነቅ የለብንም። መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚነግረን ሰይጣን የተናገረው የመጀመሪያው ቃል እግዚአብሔር ለአዳምና ሔዋን የተናገራቸውን ቃል ጥርጣሬ ላይ መጣል ነበር (ዘፍ 3፥1)። በመቀጠልም ከዚህ በበለጠ ድፍረት እግዚአብሔር የተናገረውን በግልጽ ሲቃረን እናያለን (ዘፍ 3፥4)። ከዚያ የዕልመት ቀን ጀምሮ፤ ሰይጣን ያስመታከት ከሚያደርጋቸው ጥረቶች አንዱ የእግዚአብሔርን ቃል እውነተኛነትና ሥልጣን እንድንጠራጠር ማድረግ ነው። በ1949 የቢጋ ወራት እኔና የአገልግሎት አጋሮቼ፤ በአገልግሎታችን በሰፋቱ ትልቁ የሆነውን የወንጌል ስብከት በሎስ አንጀለስ ካሊፎርኒያ ለማካሄድ እየተዘጋጀን ነበር። ይህ ዝግጅት በመገናኛ ብዙሃን ብዙ ትኩረት ባይሰጠውም፤ በመቶዎች የሚቆጠሩ ቤተክርስቲያናት ለታቀደው የሦስት ሳምንት አገልግሎት ለመዘጋጀትና ለመጸለይ በአንድ ላይ ተሰባስበው ነበር። እግዚአብሔር ይህን ስብከት እንድናካሂድ እንደመራን አመንን። ብዙ ሰዎች እግዚአብሔር ይህን አገልግሎት ብዙዎችን ወደ ክርስቶስ ለማምጣት እንዲጠቀምበት በትጋት ይጸልዩ ነበር።

አገልግሎቱ ከመጀመሩ ከጥቂት ሳምንታት ቀደም ብሎ፤ ግን በሕይወቴ ከዚያ ቀደም ገጥሞኝ የማያውቅ ብርቱና ፈታኝ የእምነት ቀውስ ገጠመኝ። ከጥቂት ወራት በፊት እጅግ የማከብረው አብሮኝ በወንጌል የሚያገለግል ሰው በመጽሐፍ ቅዱስ ያለውን ጥርጣሬ ገልጾልኝ፤ እኔም ሀሳቡን በጊዜ ብቀበል እንደሚያዋጣኝ በመንገር፤ መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል ነው ብዬ ማመኔን እንድተው ይወተውተኝ ጀመር። "ቢሊ"፤ አለኝና፤ "ከዘመኑ በሃምሳ ዓመት ያህል ወደኋላ እንደቀረህ ታውቃለህ? እንተ እንደምታምነው ሰዎች መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል ነው ብለው ማመናቸው ዘመን ያለፈበት እየሆነ ነው። እንደ የሞህ ነው የምታምነው" አለኝ። ዘመናዊ የሥነ መለኮት ሊቃውንት ይህን የመሰለ አቂመን እንደሚያቀነቅኑለት እኔም በቅርብ አንብቤአለሁ።

ሰወራት ያህል መጽሐፍ ቅዱስን አስመልክቶ ጥርጣሬ በአእምሮዬ ይገላላ ጀመር፤ በሎስ አንጀለስ አገልግሎት በምሰብክበት ወቅት ጥርጣሬው ልቂቂመው ከምችለው በላይ ሆነብኝ። አንድ

ምሽት በክፍሌ ብቻዬን ሳለሁ፣ መጽሐፍ ቅዱስ የመለኮት የእውነት ቃል መሆኑን የሚናገርበትን ክፍሎች በጥንቃቄ እጠናሁ። ነቢያት የሚናገሩት የእግዚአብሔር ቃል መሆኑን በግልፅ ያምኑ እንደነበር ታወሰኝ፤ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል በማለት ወይም ይህን መሰል ሐረግ ለመቶዎች ጊዜ ያህል ተጠቅመዋል። በተጨማሪም የሥነቁፋሮ ግኝቶች በተደጋጋሚ የመጽሐፍ ቅዱስን ታሪካዊ ትክክለኝነት አንዳረጋገጡ አውቃለሁ።

በተለይ ትርጉም እዘል የሆነልኝ ኢየሱስ ስለ መጽሐፍ ቅዱስ የነበረው እይታ ነበር። መጽሐፍ ቅዱስን እዘውትሮ መጥቀስ ብቻ ሳይሆን የእግዚአብሔር ቃል አድርጎም ይቀበለው ነበር። ለደቀመዛሙርቱ ሲጸልይ እንዲህ ብሏል፣ "ቃልህ እውነት ነው፤ በእውነትህ ቀድሳቸው" (ዮሐ 17፡17)። በተጨማሪም፣ "እውነት እላችኋለሁ፤ ሰማይና ምድር እስኪያልፍ ድረስ ሕግ ሁሉ ይፈጸማል እንጂ ክሕግ አንዲት ፊደል ወይም አንዲት ነጥብ እንኳ አትሻርም" (ማቴ 5፡18)። ታዲያ እኔስ መጽሐፍ ቅዱስን በማመን ጌታዬን መከተል የለብኝም?

በመጨረሻም፣ ጨረቃዋ ቦግ ብላ ታበራ ስለነበር ወደተራራማው ጫነ እየተራመድኩ ወጣሁና አንድ የዛፍ ጉማጅ ላይ መጽሐፍ ቅዱሴን ይገር ለጸሎት ተንበረከክሁ። በትክክል ምን እንዳልክ አላስታውስም፣ ይህን የሚመስል ነገር ነበር የጸለይክት፣ "ጌታ ሆይ፣ በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ብዙ የማይገቡኝ ነገሮች አሉ። መፍትሔ ላገኝላቸው የማልችል በርካታ ሞጋች ጥያቄዎች አሉ። ይሁንና አባት ሆይ፣ ይህ ቃልህ እንደሆነ በእምነት እቀበለዋለሁ።"

ከተንበረከከበት ስነሣ፣ የእግዚአብሔር ህልውት ክዚያ ቀደም ተለምቶኝ በማያውቅ ሁኔታ ተሰማኝ። ጥያቄዎቼ ሁሉ ባይመለሱም፣ የገጠመኝን ብርቱ መንፈሳዊ ውጊያ በድል እንደተወጣሁ አወቅሁ። ክዚያ በኋላ መጽሐፍ ቅዱስ መለኮታዊ እስትንፋስ ያረፈበት መጽሐፍ እንደሆነ ዳግመኛ ተጠራጥሬ አላውቅም፣ ስብከቱም ወዳያውኑ አዲስ ኃይል ተላበሰ። የሎስ አንጀለስ አገልግሎታችን ከታተደለት ሦስት ሳምንት ወደ ስምንት ሳምንት የተራዘመበት አንዱ ምክንያት ይህ ነበር።

መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል የመሆኑን እውነት ማንም እንዲያስጥላችሁ አትፍቀዱለት። ሃሳባችሁ በእምነት ቢነሡም እንኳን፣ ጀርባችሁን በእግዚአብሔር ላይ ለማዞር ሰበብ አታድርጉት። ይልቁንም ጥርጣሬዎቻችሁን ፊት ለፊት በመጋፈጥ መልስ እሹላቸው፣ እንደዚህን ዓይነት ጥያቄዎች ለማንሣት እናንተ የመጀመሪያዎቹ እይደላችሁም (በእካባቢያችሁ በሚገኙ ክርስቲያናዊ መጻሕፍት መደብሮች በዚህ ረገድ የሚያግዙአችሁን መጻሕፍት ታገኛላችሁ።) በተጨማሪም፣ መጽሐፍ ቅዱስን በተከፈተ ልብና አእምሮ አንብቡ። ቃሉ በርግጥ ይህ የርሱ ቃል እንደሆነ እንዲያሳያችሁ ጠይቁት - እርሱ ያሳያችኋል።

መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል እንደሆነ አንዴ ካመናችሁ በኋላ፣ ሕይወታችሁ ከቶም እንደቀድሞ አይሆንም። እግዚአብሔር ቃሉን በመጠቀም ሕይወታችሁን መለወጥ ይጀምራል።

የማይታሰብ መከራ?

አንድ ሰው በቅርቡ እንዲህ ሲል ጻፈልኝ፣ "መጽሐፍ ቅዱስን ማንበብ እንዳለብኝ አውቃለሁ። ግን በጣም ትልቅ መጽሐፍ በመሆኑ ለሰባኪዎችና ለምሑራን እንጂ ለእኔ የሚሆን እያመስለኝም"። ምናልባት እናንተም እንዲህ ተሰምታችሁ ይሆናል።

መጽሐፍ ቅዱስ በርግጥም ትልቅ ነው፤ በጣም ትልቅ በመሆኑም ታላቅ ሊቅ እንኳን በውስጡ የተካተተውን ሀብት መርምሮ ሊጨርስ አይቻለውም። ይሁንና መጽሐፍ ቅዱስ ለባኪያንና ሊቃውንት ብቻ እንዲያነቡት የታቀደ አይደለም! እግዚአብሔር በቃሉ ሊናገራችሁ ይፈልጋል፤ የእናንተ ማንነት ሁኔታ ምንም ቢሆን፣ ቃሉ በሕያውነት ወደእናንተ ይመጣል። በመጽሐፍ ቅዱስ የሰፈረውን በሙሉ ባትረዱም፣ የተወሰነውን ያህል መረዳት ትችላላችሁ። ሳሙኤል ገና ብላቴና ቢሆንም እንዲህ ሲል የጸለየውን ጸሎት እግዚአብሔር ሰምቶታል፣ "እግዚአብሔር ሆይ ባሪያህ ይሰማልና ተናገር" (1ሳሙ 3፡9)። ይህ ጸሎት ለእናንተም ይሁናችሁ።

መጽሐፍ ቅዱስ ለብዙዎች የተዘጋ መጽሐፍ የሆነባቸው ለምንድነው? እንዱ ምክንያት *ምን ያህል እንደሚያስፈልገን ስላልተገነዘብን ነው።* ለጥቂት ወራት ምግብ ብታቆሙስ? የሚላችሁን ለው እንደማትሰሙት ግልጽ ነው። በሕይወት ለመቆየት ምግብ ያስፈልጋችኋል፤ ያለ እህል ብንቆይ ጠውልገን

ውሰ እድሮ ለህልፈት መዳረጋችን እይቀርም። ታዋቂ የሆነ ክርስቲያናዊ የርዳታ ድርጅት አስተዳዳሪ የሆነው ልጄ ፍራንክሊን፣ የረሃብ ለለባ ሆኖ ለማልቀስ እንኳን የጉልበት እንጥፍጣፊ ያልቀረው ህፃን ልጅ በዕቅፍ መያዝ ምንኛ ልብ እንደሚሰብር ነግሮኛል።

ብዙ ክርስቲያኖች እግዚአብሔር በመጽሐፍ ቅዱስ ያቀረበላቸውን መንፈሳዊ ምግብ ችላ ብለው በመንፈሳዊ ረሃብ ደክመዋል። *መጽሐፍ ቅዱስ የአማራጭ ሳይሆን የግድ አስፈላጊ ነው።* ያለ ቃሉ በመንፈስ ልትበረቱ አትችሉም። ኢዮብ እንዲህ ብሏል፦ "የእንደበቱን ቃል ክዕለት እንጀራዬ አብልጬ ይዣለሁ" (ኢዮ 23፥12)። እናንተስ ለመጽሐፍ ቅዱስ ይህን ያህል ዋጋ ሰጥታችሁታል?

ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር ትውውቅ ማድረግ

የመጽሐፍ ቅዱስን መልእክት ልትረዱ የምትችሉት እንዴት ነው? የሕይወታችሁ ድርና ማግ ሊሆን የሚችለው እንዴት ነው?

በቅድሚያ፣ መጽሐፍ ቅዱስን ከሌሎች ተማሩ። እግዚአብሔር ለእንዳንድ ሰዎች መጽሐፍ ቅዱስን የመረዳትና ለሌሎች የማስተማር ልዩ ብቃት ሰጥቷቸዋል። ጳውሎስ እንዲህ ሲል ይናገራል፦ "እግዚአብሔር በቤተክርስቲያን ውስጥ እንዳንዶቹን፣ አስቀድሞ ሐዋርያትን ... ሦስተኛም አስተማሪዎችን ... መድቦአል" (1ቆሮ 12፥28)። የቤተክርስቲያናችሁ መጋቢ መጽሐፍ ቅዱስን ሲሰብክ በጥንቃቄ እደምጡት፤ በተጨማሪም በቤተክርስቲያናችሁ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ሲዘጋጅ ተሳተፉ። በሬዲዮ የሚሰጥ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ለመከታተል ሞክሩ (እንደ ፊላ ሬድዮ ዓይነት)። የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት በሚሰጥበት ኮንፍራንስ ተሳታፊ ሁኑ። በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ የተመሠረቱ የየዕለት የጥሞና መጻሕፍትንም ብዙዎች ጠቃሚ ሆነው እግኝተዋቸዋል። እነዚህ የጥሞና መጻሕፍት ለየዕለቱ እንድ ወይም ሁለት ጥቅስ ብቻ በማብራራት ቢወስኑም እግዚአብሔር እናንተን ለማነጽ ሲጠቀማቸው ይችላል።

ከቅርብ ዓመታት ወዲህ እየታዩ ካሉ መንፈሳዊ እንቅስቃሴዎች ውስጥ ትናንሽ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ቡድኖች በዋነኝነት ይጠቀሳሉ። በመላው ዓለም ክርስቲያኖች እየተሰባሰቡ መጽሐፍ ቅዱስን በእንድነት ማጥናታቸውና ህሰቦች መለዋወጣቸው የተለመደ እየሆነ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፦ "የክርስቶስ

ቃል በመላት ይኑርባችሁ፤ እርስ በርሳችሁ በጥበብ ሁሉ ተማማሩ" (ቆላ 3፥16)። ኢየሱስ እንዲህ ሲል ተስፋ ስጥቶናል፣ "ሁለት ወይም ሦስት በስሜ በማስበሰብት በዚያ በመካከላቸው እሆናለሁና" (ማቴ 18፥20)።

ሁለተኛ፣ መጽሐፍ ቅዱስን በራሳችሁ አጥኑ። መጽሐፍ ቅዱስን እንብባችሁ የማታውቁ ክሆነ ወይም ጀምራችሁ እልዘለቅ ብሏችሁ ክሆነ፣ መጽሐፍ ቅዱስን በራሳችሁ እንድታጠኑ አበረታታችኋለሁ።

ይህን ልታደርጉ የምትችሉት እንዴት ነው?

በመጀመሪያ፣ መጽሐፍ ቅዱስን በደስታ ቅረቡት። መጽሐፍ ቅዱስን ማጥናት ደስታ እንጂ ሽክም መሆን የለበትም! ለዛሬዋ ባለቤቴ ሩት በመጀመሪያ ያቀረብኩላትን የጋብቻ ጥያቄ መቀበሏን በደብዳቤ ስትገልጽልኝ የተሰማኝ ደስታ አሁን ድረስ በግልጽ ይታወሰኛል። ያን ደብዳቤ በዚያ ቀን ብዙ ጊዜ እንብቤዋለሁ። እግዚአብሔርም በቃሉ ሲናገረን ይፈልጋል እንዲያውም ቃሉ ለእኛ የተላከልን የፍቅር ደብዳቤ ነው። ታዲያ ለምን በደስታ እናነበውም?

ቀጥሎም፣ መጽሐፍ ቅዱስን በጸሎትና በመጠባበቅ ልብ ቅረቡት። እግዚአብሔር በቃሉ እንዲናገራችሁ ጠይቁት፤ ይህን እንደሚያደርግ እመኑ። ይህ ማለት መጽሐፍ ቅዱስን በክፈታችሁ ቁጥር አዲስ ነገር ታገኛላችሁ ማለት አይደለም። አዲስ እውነትን መግለጥ ብቻ ሳይሆን የተማርነውንም እውነት ያጸናልናል። የመዝሙረኛው ጸሎት የእናንተም ጸሎት ይሁን፤ "ከሕግህ ድንቅ ነገርን እንዳይ ዐይኖቼን ክፈት" (መዝ 119፥18)።

በተጨማሪም፣ መጽሐፍ ቅዱስን ሥርዓት ባለው መንገድ አጥኑት። እንዳንድ ሰዎች መጽሐፍ ቅዱስን እንዲህ በነሲብ ገልጠው ማንበብ ወይም የሚያውቋቸውን ክፍሎች መደጋገም ይቀናቸዋል። እግዚአብሔር በየትኛውም የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ሊናገረን ችግር ባይሆንበትም መጽሐፍ ቅዱስ በዚያ ብቻ እንድንወስን እንዳልተጻፈ ማስታወስ አለብን። መጽሐፍ ቅዱስን በተጻፈበት መንገድ ዘውትር የማንበብ ልማድ እዳብሩ፤ ይህም በእንድ ጊዜ እንድ መጽሐፍ በማንበብ ማለት ነው። ለሰዎች የምመክረው ክወንጌላቱ የእንዱን (ለምሳሌ የዮሐንስ ወንጌል) ጥቂት እንቀጾች በእንድ ጊዜ በማንበብ ቢጀምሩ መልካም እንደሆነ ነው። በመቀጠልም የሐዋርያት ሥራን (ስለ መጀመሪያዎቹ ክርስቲያኖች

የሚተርከውን ክፍል) ወይም ከአዲስ ኪዳን መልእክቶች እንዳንዶቹን ቢያነቡ ጥሩ ነው። የብሉይ ኪዳን ክፍል የሆነው መዝሙረ ዳዊት ለበርካታ ዘመናት አማኞች የተባረኩበት ሲሆን መጽሐፈ ምሳሌ ደግሞ ስዕለት ተስት ኑሮ የሚበጅ ተግባራዊ መመሪያ ይሰጠናል። መዝሙረ ዳዊት ከእግዚአብሔር ጋር፣ መጽሐፈ ምሳሌ ደግሞ ከሰዎች ጋር እንዴት ህብረት ማድረግ እንደምንችል መመሪያ ይሰጡናል።

በተጨማሪም፣ መጽሐፍ ቅዱስን በማስተዋል ቅረቡት። በሌላ አባባል የምታነቡትን ማስተዋላችሁን ልብ በሉ። ከበርካታ ዓመታት በፊት አንዲት ሴት የሴት አያቷ በየዕለቱ እንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ምእራፍ እንደሚያነቡ ነገረችኝ። ቀጥሎ ግን እንዲህ ስትል አከለች፣ "ግን ምን እንዳነበበች ስጠይቃት፣ አታስታውሰውም። መጽሐፍ ቅዱስን ማንበብ ምንም ለውጥ የማያመጣ የድግግሞሽ ልማድ ሆኖባታል።"

ክፍሉ (ምንባቡ) በሚለው ላይ አትኩሩ። ለለምን ይተርካል? ማዕከላዊ ነጥብ ወይም አንኳር አስተምህሮው ምንድነው? ስለ እግዚአብሔር ወይም ስለ ኢየሱስ ወይም ስው ስለእግዚብሔር ስለሰጠው ምላሽ ምን ያስተምራል?

በመጨረሻም፣ መጽሐፍ ቅዱስን በታዛዥ ልብ ቅረቡት። ያዕቆብ እንዲህ ይላል፣ "ቃሉ የሚናገረውን አድርጉ እንጂ ስሚዎች ብቻ ሆናችሁ ራሳችሁን አታታልሉ" (ያዕ 1፡22)። እግዚአብሔር ልታምኑበት የሚገባ አውነት ወይም ልታደርጉት የሚገባችሁን ነገር እያመለከታችሁ ነው? አስታውሱ፣ እግዚአብሔር *ከቃሉ ተቃራኒ የሆነ ነገር እንድታደርጉ በፍጹም አይመራችሁም።* ይልቁንም *እግዚአብሔር ሁልጊዜ የሚመራን ከቃሉ ጋር የተሰማማ ነገር እንድናደርግ ነው።*

እግዚአብሔር መጽሐፍ ቅዱስን የሰጠን እንድናውቀው፣ እንድንወደውና እንድናገለግለው ስለሚፈልግ ነው። ከሁሉም በላይ፣ *ቃሉን የሰጠን ክርስቶስን በመምሰል ማደግ እንድንችል ነው።* መጽሐፍ ቅዱስን የሕይወታችሁ ሁነኛ አካል አድርጉት፣ ዛሬውኑ ጀምሩ።

በሥሩ ሁለት

የጸሎት አስፈላጊነት



በእግዚአብሔር ፊት ሰመቀረብ ያሰን ድፍረት ደዘ ነው፤ ማንኛውንም ነገር እንደ ፈቃዱ ብንሰምን ስርሱ ደሰማናሰ።

(1ዮሐ 5፥14)

ጸሎት አማራጭ ላይሆን የግድ አስፈላጊ ነገር ነው።

የባለቤቴ አባት ከሆኑት ከዶ/ር ኤል. ኒልሰን ቤል ይልቅ በበለጠ በሥራ የተጠመደ ሰው ገጥሞኝ የማያውቅ አይመስለኝም። ለሃያ አምስት ዓመታት ቻይና ውስጥ በቀዶ ጥገና ህክምና ያገለገሉ ሚስዮናዊ እንደ መሆናቸው፣ በየዓመቱ በሺዎች የሚቆጠሩ ሰዎችን ቀዶ ጥገና አድርገዋል። በእንድ ወቅት በዚያች አገር የአጭር ጊዜ የርስ በርስ ግጭት በተከሰተ ጊዜ፣ ከ600 በላይ ቁስለኞችን አክመዋል። ሁለተኛው የዓለም ጦርነት በተጀመረ ጊዜ ዶክተሩ ከነቤተሰባቸው ወደ አሜሪካ ስመመለስ ሲገደዱ፣ በሥራ የሚወጥራቸውን የህክምና አገልግሎት መቀጠል ብቻ ላይሆን የሁለት ታዋቂ ክርስቲያናዊ መጽሔቶች አርታኢና በቤተክርስቲያናቸውም ትጉህ መሪ በመሆን ያገለግሉ ነበር። እኔና ሩት ከተጋባን በኋላ፣ ዶ/ር ቤል ከቅርብ ወዳጆቼና ሀላባቸውን በአጅጉ ከማከብራቸው አማካሪዎቼ አንዱ ሆኑ። የሳቸውን ያህል ራሱን በሥነ ሥርዓት የሚያስገዛና አያንዳንዷን ደቂቃ በቁም ነገር የሚያውል ሰው ገጥሞኝ የሚያውቅ አይመስለኝም። በዶ/ር ቤል ሕይወት በተለይ የሚታወለኝ ነገር ሳያሳታንጉሉ የሚጸልዩ ስው መሆናቸው ነው። አብዛኛውን ጊዜ ማልደው ተነሥተው በጥናት ክፍላቸው ከጠዋቱ አሥር ተኩል ወይም ዐሥራ አንድ ስዓት ጀምሮ ለረኽም ስዓት ተንበርክከው ይቆያሉ። የሥራዬ ባህርይ ለዚህ አያመችም ብሎ ማማከኛ ቢስጥ የማያስወቅሰው ስው ቢኖር ዶ/ር ቤል ነበሩ። ነገር ግን ከእግዚአብሔር ጋር ብቻቸውን ሆነው

የሚያሳልፉትን ጊዜ ከዕለት ተግባራቸው ዐቢይና ዋነኛው አድርገው ነበር የሚቆጥሩት። በየማለዳው ስለመጸለያቸው ለሰው ሊያሳውቁ (ወይም ሊመኩበት) ማንም ባይለማም፣ አንዳንድ ጊዜ የመዝሙረኛው ቃል ይጠቅሱ ነበር፣ "እግዚአብሔር ሆይ አንተ አምላኬ ነህ፤ አንተን ከልቤ እሻለሁ" (መዝ 63፥1)።

ለዶ/ር ቤል ጸሎት ማለት ዕለታቸውን የሚያሳርጉበት የጥድፊያ ዐረፍተ ነገር ወይም አንዳች ፈተና ሲጋረጥባቸው የሚያደርሱት የደቂቃ ልመና አልነበረም። ይልቁን መላ ሕይወታቸውን የሚገዛ የሠርክና የየቅዕበት ተግባር ነበር። በየዕለቱ በእግዚአብሔር ፊት የሚቀርቡበት ደስታ የለፈነበት ልምምድ ነበር።

የፀሎት ልዩ መብት

እንደ አለመታደል ሆኖ ግን ለብዙዎች ጸሎት ሸክም እንጂ ደስታ አይደለም። መጸለይ ሲሳናቸው፣ የበደለኝነት ስሜት ይጫናቸዋል፤ ለመጸለይ ሊሞክሩ ደግሞ በተገቢው መንገድ እያደረጉት እንደሆነ እርግጠኞች አይሆኑም። ወይም ደግሞ ጸሎታቸው ሕይወት አልባና አለልቲ፣ በልጅነት የተማሩትን እቡነዘበስማያት ከመደጋገም ያላለፈና ልብና እእምሯቸውን የማይዘልቅ ልማድ ይሆንባቸዋል።

ጸሎት ግን እንደዚህ መሆን የለበትም። ጸሎትን ሸክም ላይሆን ልዩ መብት አድርገን ማየት አለብን። እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ኅብረት ማድረግ ስለሚፈልግ በጸጋው የሰጠን ልዩ መብት ነው። እስታውሱ፤ ኢየሱስ ክርስቶስ የሞተው ከእግዚአብሔር የለየንን የኃጢአት ግድግዳ ለማፍረስ ነው፤ ሕይወታችንን ለእርሱ ለንስጥ ከእግዚአብሔር ጋር ግላዊ ግንኙነት መመሥረት እንጀምራለን። እንደ እውነቱ ከሆነ ከእግዚአብሔር ጋር በጸሎት መነጋገር የምንችለው ክርስቶስ በመስቀል ላይ ለእኛ ስለሞተልን ነው።

የማንኛውም ህብረት እንኳር ባህርይ ተግባቦት ነው። በለምኞ ደረጃ (ልኪት) ይህ እውነት መሆኑ አመን ነው፤ እርስ በርሳቸው ቃል ተለዋውጠው የማያውቁ ለምኞ ወዳጃሞች ነን ቢሉ ይታመናሉ? ከዚህ በገዘፈ ሁኔቴ ከእግዚአብሔር ጋር ያለን ህብረት የጠበቀ ተግባቦትን ያጠቃልላል። ይህም አንዳንዴ ከእርሱ ጋር እንዲሁ መነጋገር ብቻ ላይሆን የራሳችንን ውስጥና ነገሬ የምንለውን

ጉዳይ ይዘን ለእርሱ ማካፈልና መግለጽ ማለት ነው። ክርስቶስ የመንግሥቱ ለሚያትን በር ስለከፈተልን "ምሕረትን እንድንቀበልና በሚያስፈልገንም ጊዜ የሚረዳንን ጸጋ እንድናገኝ፣ ወደ ጸጋው ዙፋን በእምነት እንቅረብ" (ዕብ 4፥16)።

ጸሎት ምንድነው?

ከእግዚአብሔር ጋር ወዳጅነታችንንና ተግባቦትን ያጠቃልላል፣ ያም ማለት ጸሎት ከእግዚአብሔር ጋር መነጋገር ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር አኛን ይናገራል፤ በጸሎት ደግሞ እኛ እግዚአብሔርን እናነጋግረዋለን። ሁለቱም የግድ አስፈላጊ ናቸው። ሁለቱም እኛ እርሱን እናውቀው ዘንድ ከእርሱ የተሰጡን ስጦታዎች ናቸው። ጸሎት ልክ እንደ መጽሐፍ ቅዱስ ከእግዚአብሔር የተሰጠን ስጦታ ነው፤ በፀሎት ከእርሱ ጋር የመነጋገር ልዩ መብት የሰጠን ስለሚወደንና ከእኛ ጋር ኅብረት ማድረግ ስለሚፈልግ ነው። ኢየሱስ እንዲህ ብሏል፡- "በእውነት የሚለግዱ ለአብ በመንፈስና በእውነት የሚለግዱበት ጊዜ ይመጣል፤ አሁንም ሆኖአል፤ አብ ሊለግዱለት እንደነዚህ ያሉትን ይሻልና" (ዮሐ 4፥23)። ይህ ነገር ይታሰባችኋል? እግዚአብሔር የኛን ኅብረት ይፈልጋል።

በጸሎት ብርታት ይገኛል

መጸለይ የሚያስፈልገን ለምንድነው? ምክንያቱ ይህ ነው፤ የክርስትና ሕይወት ጉዞ ስለሆነ ነው፤ ስለዚህ የእግዚአብሔር ኃይልና ምሪት ለመንገዳችን እንደ ስንቅ ያስፈልገናል። እኛህን ከምናገኝባቸው መንገዶች አንዱ ጸሎት ነው። እግዚአብሔር በራሳችን ጉልበት እንድንፍጨረጨር አይተውንም። ይልቁንም "በገዛ ክብሩና በበጎነቱ የጠራንን እርሱን በማወቅ ለሕይወትና ለእውነተኛ መንፈሳዊነት የሚያስፈልገንን ሁሉ የመለኮቱ ኃይል ለጥቶናል" (2ጴጥ 1፥3)። እግዚአብሔር ከለጠን እለፈላጊ ነገሮች መካከል ጸሎት አንዱ ነው።

እግዚአብሔርን ትርጉም ባለው መንገድ ያገለገሉ ወንዶችና ሴቶች በሙሉ የጸሎት ለምኞች ነበሩ። ጸሎት የማያውቅ ክርስቲያን ራሱን የሚቃረን ነው፤ ምነው ቢባል ከዋጀን ጌታ ጋር ኅብረት መናፈቅ ለላለብን ነው። በሞላ በመጽሐፍ ቅዱስና በቤተክርስቲያን ታሪክ፣ እግዚአብሔር በኃይል የተጠቀመባቸውና ታላቅ ተዕዕኖ ያመጡ ለምኞች የጸሎት ለምኞች ነበሩ።

ከሁሉም በላይ ኢየሱስ ራሱን ምሳሌ በማድረግ የጸሎትን አስፈላጊነት አሳይቶናል። መላው እገልግሎቱ በጸሎት የተሞላ ነበር። በአንድ ወቅት፣ "ማለዳም ገና ጎሕ ሳይቀድ ኢየሱስ ተነሥቶ ከቤት ወጣ፤ ወደ አንድ ገለልተኛ ስፍራም ሄዶ ይጸልይ ጀመር" (ማር 1፥35)። በሌላ ጊዜ ደግሞ፣ "ኢየሱስ በአንድ ስፍራ ይጸልይ ነበር፤ ፀሎቱንም እንደጨረሰ ከደቀ መዛሙርቱ አንዱ መጸልይን አስተምረን አለው።" (ሉቃ 11፥1)። ቀጥሎም ለዘመናት በርካታ ክርስቲያናት የጸሰዩትን የአቡነዘበለማያት ጸሎት አስተማራቸው። የሞቱ ቀን ሲቃረብ፣ ከኢየሩሳሌም ቅጥሮች ውጪ በሚገኝ የጌቴሴማኒ የአትክልት ስፍራ ሄዶ መጸለይ ጀመረ፤ "እጅግ ተጨንቆም በብርቱ ይጸልይ ነበር፤ ላቡም እንደ ደም ነጠብጣብ ወደ ምድር ይፈስ ነው" (ሉቃ 22፥44)። በመስቀል ላይ ሆኖ የጸለየው የመጨረሻ ጸሎት፣ "አባት ሆይ ነፍሴን በእጅህ አደራ እሰጣለሁ" (ሉቃ 23፥46) የሚል ነበር። የእግዚአብሔር ልጅ በምድር በኖረበት ወቅት ጸሎት እንደ እስትንፋስ የሚያስፈልገው ከነበረ፣ ለኛማ ምንኛ የበለጠ ያስፈልገን ይሆን?

ፍላጐታችንን ለእግዚአብሔር ማቅረብ

አንድ ወጣት በቅርቡ፣ "ጸሎት አስፈላጊ የሆነበት ምክንያት አይታየኝም፤ እግዚአብሔር ምን እንደሚያስፈልገን ያውቃል። ስለዚህ መናገር ምን ያስፈልገኛል?" ሲል ጻፈልኝ።

አስከተወሰነ ደረጃ አባባሉ እውነትነት አለው። እግዚአብሔር ሉዓላዊ በመሆኑ ስለእኛ ሁሉን ያውቃል፤ "አባታችሁ ከመለመናችሁ በፊት ምን እንደሚያስፈልጋችሁ ያውቃልና" (ማቴ 6፥8)። ይሁንና አግዚአብሔር ለፈላጭነንና ለሉሎች እንድንጸልይ አዞናል፤ ወደ እርሱ ስንጸልይ ብቻ ሁል ጊዜ ምላሽ ይሰጠናል። ይህ በምድር ቆይታችን ሙሉ በሙሉ ልንገነዘባቸው ከማንችላቸው ምስጢራት አንዱ ነው።

እግዚአብሔር ከሰጠን እጅግ የሚያጽናኑን የተስፋ ቃሎች አንዱ ፍላጐቶቻችንንና ሸክሞቻችንን ሁሉ ወደ እርሱ ይዘን ብንቀርብ የሚሰማን መሆኑ ነው። የከበደህን ነገር በእግዚአብሔር ላይ ጣል፣ እርሱ ደግፎ ይይዝሃል፤ ለጻድቁም ለዘላለም ሁከትን አይለጠውም" (መዝ 55፥22)። መጽሐፍ ቅዱስ በተጨማሪ፣ "የጻድቅ ለው ጸሎት ኃይል አለው፤ ታላቅ ነገርም ያደርጋል" (ያዕ 5፥16) ይላል። ወደ አፍሪካና ሕንድ ለአገልግሎት በሚድንባቸው ጊዜያት የማይረሳኝ ነገር በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ለምኝ በየማለዳ

በሚያደርጉት የጸሎት ጎብረት መካፈል ነበር። ለምኝ እንዲህ በጋለ ልብ ሲጸልዩ ገጥሞኝ አያውቅም፤ በዚህ ሁኔታ የሚጸልዩት ፀሎት ታላቅ ነገር የማድረግ ኃይል እንዳለው ስለማያውቁ ነው። የእግዚአብሔር ቃል ጸሎታችን እንደሚሰማ በበርካታ ተስፋዎች የተሞላ ነው፤ በተደጋጋሚም ሸክማችንን ይዘን ወደ እርሱ እንድንቀርብ ይነግረናል።

በርግጥ፣ እግዚአብሔር የሚገተገተን የራሳችንን ጉዳዮችና አቤቱታዎች ብቻ ሳይሆን ስለሌሎች የምልጃ ፀሎት ጭምር ወደ እርሱ እንድናመጣ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፤ "በነገር ሁሉ በጸሎትና በምልጃ፣ ከምስጋና ጋር ልመናችሁን በእግዚአብሔር ፊት አቅርቡ እንጂ ስለማንኛውም ነገር አትጨነቁ። ከማስተዋል በላይ የሆነው የእግዚአብሔር ሰላም፣ ልባችሁንና አሳባችሁን በክርስቶስ ኢየሱስ ይጠብቃል" (ፊል 4፥6-7)። ጳውሎስ ብዙ ጊዜ አማኞች እንዲጸልዩለት ይጠይቃቸው ነበር፤ "ወንድሞች ሆይ፤ ስለእኛ ደግሞ ጸልዩ" (1ተሰ 5፥25)። ምድራዊ አባት ልጆቹ ልመናቸውን ይዘው ወደ እርሱ እንዲመጡ እንደሚፈልግ ሁሉ፣ ለማያዊ አባታችንም እንደዚሁ እንድናደርግ ይፈልጋል።

ምስጋናና ውዳሴ

ቀደም ሲል የጠቀስኩት ወጣት እንደጸፈው፣ "እግዚአብሔር እኔ የምፈልገውን ሁሉ ያውቃል" ሆኖም ወደ እግዚአብሔር መቅረብ ያለብን የሚያስፈልገንን ለመጠየቅ ብቻ ከሆነ፣ ጸሎታችን በራስ ወዳድነት ልመና ላይ የተመሠረተ ይሆናል። ሀሳቡ የሚያንቀጠቅጠን ቢሆንም፣ እግዚአብሔርን እንደ ነገር ሲያስፈልገን ብቻ አቤቱታ ከምናቀርብለት ካንድ የከበረ ሰው ትንሽ አስበልጠን ልናስበው እንጀምራለን። አግዚአብሔር ግን ከዚህ በላይ ብዙ በላይ ትልቅ ነው። እስታውስ፤ *እኛ የእግዚአብሔር ለሌሎች ነን እንጂ፣ እርሱ የእኛ ለሌሉ አይደለም*።

እውነተኛ ጸሎት የሚጀምረው እግዚአብሔርን በእውነተኛ ማንነቱ መመልከት ስንጀምር ነው፤ ውዳሴ የጸሎታችን መደበኛ አካል መሆን ያለበትም ለዚህ ነው። እግዚአብሔርን ስናወድስ ትኩረታችን በእርሱ ላይ እንጂ በእኛ ላይ አይሆንም። ብዙዎቹ የመዝሙረ ዳዊት ክፍሎች የውዳሴ ጸሎቶች ናቸው፤ ምስጋና የሚለው ቃል በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ከ200 ጊዜ በላይ ጥቅም ላይ መዋሉ ያለ ምክንያት አይደለም። የጌታ ጸሎት የሚጀምረው

በውዳሴ ነው፣ "በሰማያት የምትኖር አባታችን ሆይ፤ ስምህ ይቀደስ" (ማቴ 6፥9)። ጳውሎስ የኤፌሶንን መልእክት የሚጀምረው እንዲህ በማለት ነው፣ "በሰማያዊ ስፍራ በመንፈሳዊ በረከት ሁሉ በክርስቶስ የባረከን የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አምላክ አባት ይባረክ" (ኤፌ 1፥3)።

በእግዚአብሔር ላይ እንድናተኩር የሚያደርገን ሁለተኛው የጸሎት ደረዝ ምስጋና ነው፤ ይህም ከውዳሴ ጋር በቅርብ የተዛመደ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፤ "በምስጋና ወደ ደጆቹ፣ በውዳሴም ወደ አደባባዮቹ ግቡ" (መዝ 100፥4)።

ምስጋና ማቅረብ ያለብን ለምንድነው? አንዱ ምክንያት ሁሉም ነገር ከእግዚአብሔር ስለሚገኝ ነው። "በጎ ስጦታና ፍጹም በረከት ሁሉ ከላይ ከሰማይ ብርሃናት አባት ይወርዳሉ" (ያዕ 1፥17)። ስኬቶቻችንም እንኳን በእኛ ምክንያት የተገኙ ናቸው ብለን ልንቆጥር አይገባም። ችሎታ የለጠን፣ ሁኔታዎችን ምቹ ያደረገልን ጥረታችንን የባረከ እርሱ ነው። ስለዚህም መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል "ቸር ነውና፣ እግዚአብሔርን አመስግኑ፣ ምሕረቱም ለዘላለም ነውና" (መዝ 106፥1)። በተጨማሪም፣ "በማናቸውም ሁኔታ አመስግኑ፣ የእግዚአብሔር ፈቃድ በኢየሱስ ክርስቶስ ለእናንተ ይህ ነው" (1ተሰ 5፥18)። እግዚአብሔር ስላደረገላችሁ ሁሉ ቆም ብላችሁ ካመሰገናችሁ ምን ያህል ጊዜ ሆኖአችኋል?

ኀጢአታችንን መናዘዝ

ፍላጐቶቻችንን ወደ እርሱ ማቅረብ ... ምስጋናና ውዳሴ ለእግዚአብሔር ማቅረብ ... እነዚህ ዋናኛ የጸሎት አንኳሮች ናቸው። ግን ሌላ አስፈላጊ ነገርም አለ፤ ይህም ኃጢአታችንን መናዘዝ ነው።

ከዚህ ቀደም ልባችሁን ለኢየሱስ ከፍታችሁ የማታውቁ ከሆነ በቅድሚያ ማቅረብ ያለባችሁ ጸሎት የኑዛዜ ጸሎት ነው። ኃጢአተኝነታችሁን ተገንዝባችሁ ከመንገዳችሁ፣ ለመመለስ መወሰናችሁን ለእግዚአብሔር ንገሩት፣ ቀጥሎም ከርስቶስ በእምነት ኃጢአታችሁን እስወግዶ የሕይወታችሁ ጌታና አዳኝ እንዲሆን ጠይቁት፣ እርሱም ጥያቄአችሁን ያከብራል። "በእርሱ የሚያምን ሁሉ በስሙ የኃጢአት ስርየት ይቀበላል" (የሐዋ 10፥43)። ይህ በንስሐና በእምነት ወደእርሱ ለሚመለሱ ሁሉ፣ የእግዚአብሔር

የተስፋ ቃል ነው። ታዲያ ሕይወታችሁን ለክርስቶስ ለመስጠት ለምን ሰባብ አስባብ ታቀርባላችሁ?

ይሁንና ክርስቶስን እውቀንም እንኳን፣ በደል ስለምንፈጽም ራሳችንን ለማንዓትና ለመታደስ ወደእርሱ መምጣት ያስፈልገናል። ኃጢአት እንደሠራችሁ ስታውቁ፣ መለታችሁን ተናዛችሁ ይቅርታውን ከመፈለግ ምንም ነገር ጎፍረት፣ የጥፋተኝነት ስሜት፣ ትዕቢት፣ ፍርሃት ወይም ሌላ ነገር እንዲያቅባችሁ አትፍቀዱለት። መጽሐፍ ቅዱስ ከማያቀርብልን ታላላቅ ተስፋዎች አንዱ በ1ዮሐ 1፥9 የሚገኘው ነው፣ "ኃጢአታችንን ብንናዘዝ ኃጢአታችንን ይቅር ሊለን፣ ከዐመጣ ሁሉ ሊያነጻን እርሱ ታማኝና ጻድቅ ነው።" የእግዚአብሔርን ይቅርታ እሹ፤ ቀጥሎም የመዝሙረኛውን ጸሎት የራሳችሁ አድርጉት፤ አምላኬ ሆይ፦ "ንጹሕ ልብ ፍጠርልኝ፣ ቀና የሆነውንም መንፈስ በውስጤ አድስ" (መዝ 51፥10)።

ጋሬጣዎችን ማስወገድ

የፀሎትን አስፈላጊነት ተገንዝበንም እንኳን መጸለይ ቀላል ላይሆንልን ይችላል። ምክንያቱ ምንድነው? የጸሎት እንቅፋቶችስ ምንድናቸው? የፀሎት እንቅፋቶች ብዙ ሊሆኑ ዋናዎቹ ምክንያቶች የሥርዓት (የራስ መግዛት) አለመኖር፣ ያልተናዘዝነው ኃጢአት፣ የእግዚአብሔር ርዳታ እንደሚያስፈልገን አለመገንዘብ፣ ለሌሎች ሰዎች ደንታ ማጣት፣ ጸሎታችን ስለመሰማቱ መጠራጠርና ወይም ደግሞ በቀጥታ ወደ እግዚአብሔር መቅረብ እንደምንችል ዋስትና ማጣት ናቸው። ምክንያቱ ምንም ይሁን ለእርሱ እና ከእርሱ ጋር የጠበቀ ኅብረት እንዳናደራችሁ ረሃቡንና ናፍቆቱን እግዚአብሔር አንዲሰጣችሁ ጠይቁት። በመቀጠልም፣ ከጸሎት የሚያቅባችሁ ምን እንደሆነ እውነቱን በመጋፈጥ እግዚአብሔር እንዲረዳችሁ ጠይቁት።

ለብዙዎች ግን፣ ውጤታማ የጸሎት ሕይወት እንዳይኖራቸው ያገዳቸው እንደኔ መጸለይ እንዳለባቸው ያለማወቅ ስሜት ነው። አንድ ሰው በቅርቡ እንዲህ ሲል ጻፈልኝ፣ "መጸለይ እንደሚያስፈልገኝ አውቃለሁ፤ ግን ይህን እንዲት ማድረግ እንዳለብኝ አላውቅም፣ ለመጸለይ ብሞክር እግዚአብሔርን የማሳዝነው ይመስለኛል።"

እግዚአብሔር ግን እንደ ሕጻናት የምናደርጋቸው ጥረቶች እንኳን ያስደስቱታል። በጨቅላነታችሁ መናገር አትችሉም ነበር። ያም ሆኖ የመጀመሪያ ቃላችሁን እንዳትማሩና ቱስ በቱስ እጫጫር

ዐረፍተ ነገሮች ከመናገር አልከለከላችሁም። ለእናትም ይሁን ለአባት ልጃቸው ለመናገር ሲንተባተብ ከመስማት የበለጠ አስደሳች ነገር እንደሌለ፣ የናንተ ጥረት ለእግዚአብሔር ደስታ ይፈጥርለታል። ከርስቶስን ስታውቁ የእግዚአብሔር ልጆች ስለምትሆኑ ጸሎታችሁን ይቀበላል። እርሱ ግድ የሚለው ቃል ማለካታችን ሳይሆን የልባችን ሁኔታ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፤ "እግዚአብሔር ሆይ፤ አንተ የተሰበረውንና የተዋረደውን ልብ አትንቅም" (መዝ 51÷17)። አስታውሱ፤ ጸሎት ማለት ከእግዚአብሔር ጋር መነጋገር ነው።

ስመጸልይ መስማመድ

ጸሎትን የዕለት ሕይወታችሁ አካል ልታደርጉ የምትችሉት እንዴት ነው? ለእኔ ትልቅ እገዛ የሆኑኝን ስድስት መመሪያዎች ልጠቁማችሁ።

በቅድሚያ፣ ቀና ልቦና ይኑራችሁ። ጸሎት በእግዚአብሔር ላይ ተደጋፊነታችንን የምናውጅበት ነው። መጸለይ የምንችለው በእግዚአብሔር ላይ መደገፍ እንዳለብን ተረድተን፣ ልመናችንን ስምቶ እንደፈቃዱ እንደሚመልስልን ስንተማመንበት ነው። በቅርቡ በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ወቅት ለንደን በቦምብ ስትደበደብ የሚያሳይ ጥናታዊ ፊልም ተመልክቼ ነበር። በፓሮግራሙ ላይ የቀረበው አንድ ሰው፣ ቦምቦቹ መጣል ሲጀምሩ በሕይወቱ ለመጀመሪያ ጊዜ መጸለይ እንደጀመረ ተናገረ። ብዙ ሰዎች በሕይወት ዘመናቸው ስለእግዚአብሔር አንድም ቀን ሳያስቡ ኖረው ድንገት መወጣት የማይችሉት አጣብቂኝ ውስጥ ሲገቡ የድረሱልኝ ጩኸት ያቀርባሉ። ይሁን ሲያደርጉም በደበዘዘ ሁኔታም ቢሆን በእርሱ ከመደገፍ መውጣት እንደማይችሉ መገንዘባቸው ነው።

በትዕቢት የተሞሉ፣ ለራሱ አላንስም ባይ ሰዎች ከቶም ስለ መጸለይ ማሰብ አይፈልጉም፣ ምክንያቱም የእግዚአብሔር እገዛ እንደሚያስፈልጋቸው ስለማያምኑ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ "እግዚአብሔር ትዕቢተኞችን ይቃወማል፤ ለትሑታን ግን ጸጋን ይሰጣል" በማለት ያስታውሰናል (1ኛጴጥ. 5÷5)።

ሁለተኛ፣ በፀሎታችሁ የእግዚአብሔርን ፈቃድ አሹ። እግዚአብሔር ማናቸውንም ጉዳዮቻችንን በፀሎት ወደርሱ እንድናመጣና ባለማቋረጥ እንድንፀልይ ይፈልጋል። ነገር ግን ስለፈቃዱ የተሟላ ዕይታ (ሥዕል) አይኖረንም፣ እንዳንዱ የማይገቡንን ወይም የተሳሳቱ ነገሮችን እንጠይቃለን። ኢየሱስ አንድ ጊዜ ደቀመዛሙርቱን፣ "የምትለምኑትን አታውቁም" (ማር 10÷38) በማለት ወቅሷቸዋል። ያዕቆብም፣ "ትለምናላችሁ፣ በምኞቶቻችሁም ትከፍሉ ዘንድ በክፉ ትለምናላችሁና አትቀበሉም" (ያዕ 4÷3) በማለት ጽፏል። ከሁሉ በላይ የእግዚአብሔር ፈቃድ እንዲሆን ፀልዩ፤ "ፈቃድህ በሰማይ እንደሆነች እንዲሁ በምድር ትሁን" (ማቴ 6÷10)።

የእግዚአብሔርን ፈቃድ እንዴት እናውቃለን? በዚህ መጽሐፍ በምዕራፍ 24 ይህንን በጥልቀት እናያለን፣ በዚህ ሥፍራ ግን እግዚአብሔር ፈቃዱን እንድናውቅ የሚያደርገውና የሚገልጥልን በቃሉ (በመጽሐፍ ቅዱስ) እና በመንፈስ ቅዱስ ምሪት አማካይነት መሆኑን ልብ እንበል። በምትፀልዩበት ጊዜ የእግዚአብሔርን ፈቃድ አሹ፣ እንድታውቁም ይረዳችኋል።

ሦስተኛ፣ ሁሉን ነገር በጸሎት ለእግዚአብሔር አቅርቡ። እግዚአብሔር ይወደናል፣ እርሱ ስለማንኛውም የሕይወታችን ዝርዝር ጉዳይ፣ ትልቅም ይሁን ትንሽ፣ ያስባል። ስለጥቃትን ነገሮቻቸው የጸለዩ ወጣቶችን እውቃለሁ - ነገር ግን እነዚህ ወጣቶች ስለ ክሌጃቸው ምርጫ ወይም ስለ ሥራቸው፣ ወይም ስለ ወደፊት የትዳር ጓደኛቸው አልፀለዩም። በሌላ በኩል ደግሞ በሕይወታቸው ቀውስ ባጋጠማቸው ጊዜ ብቻ የፀለዩ ሰዎችንም አውቃለሁ። መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፣ "በነገር ሁሉ ... በእግዚአብሔር ዘንድ ልመናችሁን አስታውቁ" (ፊልጵ 4÷6)።

አራተኛ፣ በማንኛውም ጊዜና ሁኔታ ውስጥ መፀለይን ተለማመዱ። በቀን ውስጥ ከእግዚአብሔር ጋር በፀሎት ለምታሳልፉበት ጊዜ ምንም መተኪያ የለውም። በየዕለቱ በመኪና ውስጥ ወይም በወንበር ላይ ስንቀመጥ፣ በምግብ ማብሰያ ክፍል ውስጥ ስንሠራ፣ ከሰዎች ጋር በስልክ ስንነጋገር እንኳን በፀሎት ስሜት ውስጥ ልንሆን እንችላለን። መጽሐፍ ቅዱስ "ባለማቋረጥ ፀልዩ" (1ተስ 5÷17) ይለናል። ነቢዩ ዳንኤል እግዚአብሔርን ከማምለክ ማቋረጥን እምቢ ብሎ ሕይወቱ በአደጋ ውስጥ በነበረ ጊዜ፣ "ወደ ቤቱ ገባ፣ ... ቀድሞም ያደርግ እንደነበረ በየዕለቱ ሦስት ጊዜ በጉልበቱ ተንበርክኮ በአምላኩ ፊት ጸለየ" (ዳን 6÷10)።

አምስተኛ፣ ስለ ውጤቱ በእግዚአብሔር ተማመኑ። ስምች በተደጋጋሚ ከሚጠይቁኝ ጥያቄዎች አንዱ ስለማይመለስ፡ ፀሎቶች ነው። አንድ ሰው ፍርጥ አድርጐ "እግዚአብሔር ደንቆሮ መሆን አለበት" በማለት ጽፎልኛል። ሌላው ሰው ደግሞ "የኔ ፀሎቶች ከቶ ከጣሪያ በላይ የማይወጡ ናቸው" ብሏል። ነገር ግን እግዚአብሔር ለኛ የተሻለው (የሚሻለው) ምን እንደሆነ ያውቃል፣ እናም ስለ ጸሎታችን ውጤት በርሱ መተማመናችንን ልንለማመድ ይገባናል። አንዳንድ ጊዜ እግዚአብሔር ለአንድ ለሆነ ነገር በምንጠይቀው ጊዜ "አዎን" ይላል (ይፈቅዳል)። ነገር ግን አንዳንዴ "ቆይ" ይሆናል መልሱ፣ ወይም "አይሆንም" የሚል ይሆናል። አንዳንዴም ደግሞ መልሱ "ባትረዳኝም እንኳን በኔ ታመን" የሚል ይሆናል።

የባለቤቴ የሩት አባት፣ ዶ/ር ቤል፣ ሁልጊዜ የሚጸልይላቸውን ሰዎች ዝርዝር ይይዛል። ዶ/ር ቤል ከሞተ በኋላ ባለቤቴ ሩት ከአባቲ ከፀሎት ዝርዝሮቹ አንዱን አግኝታ ነበር (በፍፁም የማይነበብ ነው፣ ዶክተሮች እንዴት እንደሚጽፉ ታውቃለህ ብላ ነበር)። ነገር ግን በዝርዝሩ ውስጥ ስለልጆቻችን የነበረውን የፀሎት ሸክም ጽፎ ነበር። ዶ/ር ቤል ለልጆቻችን ወደ አግዚአብሔር ይቀርብ የነበረው ፀሎት መልሱ የመጣው እርሱ ከሞተ ከአምስት ዓመት በኋላ ነበር። ይህ እግዚአብሔር ጸሎትን በታማኝነት እንደሚመልስና በኛ ጊዜ ሳይሆን በራሱ ጊዜ እንደሚሠራ ግልጽ የሆነ ቀስቃሽ ማስረጃ ነው።

በመጨረሻ፣ ማድመጥን ተለማመዱ። መፀለይ ማለት ለእግዚአብሔር መንገር ነው፣ ነገር ግን አንዳንዴ በፀሎት ጊዜአችን በፀጥታ ሆነን እርሱ ይናገረናል። ስለርሱ መገኘት (ህልውት) ውስጣዊ ማረጋገጫ ሊሰጠን ይችላል፣ ወይም በአንድ በተወሰነ አቅጣጫ ይመራናል። መጽሐፍ ቅዱስ፣ "በትዕግሥትህ ጸንተህ እግዚአብሔር የሚያደርገውን ለማየት ተወባበቅ" (መዝ 37፥7) ይላል።

ዛሬ፣ ፀሎትን የሕይወታችሁ ማዕከላዊ በማድረግ ጀምሩ። የኢየሱስን ምላሌነት በመገንዘብ ፀልዩ። የእግዚአብሔር ትእዛዝ ስለሆነ ፀልዩ። ኢየሱስ ወደ እግዚአብሔር አባት እንድንደርስ ስለሞተ ጸልዩ። እግዚአብሔር ምስጋናና ውዳሴአችሁን ስለሚፈልገው ጸልዩ። የርሱ ምህረት፣ ማንፃት፣ ምሪትና ጥበቃ ስለሚያስፈልጋችሁ ፀልዩ። ሌሎች ለሰች ጸሎታችሁን ስለሚፈልጉ ፀልዩ። ከሁሉ በላይ እግዚአብሔር በዘረጋላችሁ በዚህ የሕይወት ጉዞ እርሱ የእናንተን ህብረት ስለሚፈልግ፣ እናንተም የርሱ ህብረት ስለሚያስፈልጋችሁ ፀልዩ።

ዐሥሩ ሦስት

በአንድነት መጓዝ

ሁለት ወይም ሦስት በስሜ በሚሰበሰቡበት በዚያ በመካከላቸው ስሆናለሁና።

(ማቴ 18፥20)

የእኛ አባልነት ለእግዚአብሔር ብቻ ሳይሆን ለእርስ በርሳችንም ነው።

እግዚአብሔር በሰጠን በዚህ የሕይወት ጉዞ የምንጓዘው ብቻችንን አይደለም፣ ሌሎችም ከኛ ጋር እየተጓዙ ናቸው። ነገር ግን ባንድ ውድድር ወይም በማራቶን ሩጫ እንደሚሆነው ለማሸነፍ እርስ በርሳችን እየተወዳደርን አይደለም፣ ወይም ደግሞ ከሌሎች ቀድሞ ለመግባት እየሞከርን አይደለም። በዚህ ጉዞ ደስታዎቻችንን እየተከፋፈልን፣ ሸክሞቻችንንና የልብ ስብራቶቻችንን እየተሸካከምን ባንድነት እየተጓዝን ነው። አንዳንዶች ቢደናቀፉ፣ በእግሮቻቸው እንዲቆሙ እናግዛለን፣ አንዳንዶች አቅጣጫ ቢለውጡ፣ እንዲመለሱ እንጐተጉታለን። በዚህ ጉዞ ላይ ደስን ሀላችን ባንድ ቤተሰብ - የእግዚአብሔር ቤተሰብ - ውስጥ ደስን ወንድሞችና እህቶች ነን።

ይህ ቤተሰብ አዲስ ኪዳን "ቤተክርስቲያን" ብሎ የሚጠራው ነው። ቤተክርስቲያን ሲባል በጭራሽ አንድ የተወሰነ ሕንፃ ወይም ማኅበረ-ምዕመናን ማለት አይደለም፣ ነገር ግን የኢየሱስ ክርስቶስ የሆኑ ሁሉ መንፈሳዊ ህብረት ማለት ነው። የኢየሱስ ክርስቶስ ስንሆን፣ የርስ በርሳችንም እንሆናለን፣ ለክርስቶስ ሕይወታችንን ከሰጠን ለርስ በርሳችንም የተሰጠን ነን። ምክንያቱ ቀላል ነው፣ አንዳችን ለሌላው እናስፈልጋለን። "ቤተክርስቲያን" ብለን የምንለው

ቃል አስፈላጊነቱ ተጠቅሶ በአዲስ ኪዳን ውስጥ ከአንድ መቶ ጊዜ በላይ ተገልጿል።

በዓለም ዙሪያ ሁሉ

በ1959 አንድ ወዳጄ ወደ ሞስኮ በሚያደርገው ጉዞ ላይ አኔና ግራዲ ዊልሰን የተባለ ጓደኛዬ አብረነው አንድንሄድ ጋበዘን። የሶቭየት ኅብረት ባለሥልጣኖች አንድስብከ ስለማይፈቅዱልኝ አኔ የምሄደው በቱሪስት ቪዛ ነበር። ወደ ሞስኮ ደርሰን ከአየር ማረፊያው የኢ.ሚ.ግሬሽን ሠራተኛ ዘንድ ቀርቤ ፓስፖርቴን ስሰጣት ተናድጀ ነበር። ፓስፖርቴን በጥንቃቄ ካየችው በኋላ፣ በአካባቢዋ ማንም እንደሌለ በማረጋገጥ፣ ብሩህ ፈገግታዋን ለገሠችኝና በዝግታ በጣቷ ወደ ሰማይ አመልክታ ክርስቲያን "ባንድ መንገድ" የሚል ምልክት አሳየችኝ። ክህደት በነገሠባት በሶቭየት ኅብረት ውስጥ በክርስቶስ አማኝ ነበረች።

ከብዙ ቀናት በኋላ፣ ዓመታዊ የድል ቀናቸውን ለማክበርና በዓሉን ምክንያት በማድረግ የአበባ ጉንጉኖችን የሚያስቀምጡትን ሰዎች ለመመልከት በክሬምሊን ግንብ አጠገብ ከተሰበሰበው ብዙ ሕዝብ መካከል ቆሜ ነበር። አንድ በውትድርና አገልግሎቱ በደረቱ ላይ ብዙ ሜዳሊያ ያደረገ ሰው በፀጥታ ተጠግቶኝ ቆመ። አንድም ቃል ሳይተነፍስ ከአግሮቻችን በታች በአፈር ላይ ከመጠጫው የቀረውን አንጥፍጣፊ በማንጠባጠብ መስቀል ሣለ። ይህ ሰው በክርስቶስ አማኝ ነበር።

በዚሁ የጉብኝቴ ወቅት ካረፍኩበት ሆቴል ውጭ አንድ አውቶቢስ መንገደኞችን እያወረደ ቆሜ ነበር፣ ገና ብ አያካፉ ነበር። በአውቶቡስ ውስጥ የነበረች አንዲት ሴት በቀጥታ ወደኔ ስትመለከት ምናልባት በአለባበሴ የውጭ ሰው መሆኔን አውቃ ይሆናል ብዬ ነበር። ከዚያም ሆን ብላ በካፊያው ምክንያት በወረዛው በአውቶቡስ መስታወት ላይ የመስቀል ምልክት ነደፈች። አኔም ራሴን ነቀነቅኩና ፈገግ ብዬ ምልክቷን አከበርኩላት። ምንም ባንነጋገርም፣ በክርስቶስ የተነሣ ከርሷ ጋር የጋራ ውል (ስምምነት) አንዳለን ተሰማኝ።

አነዚያ በሞስኮ ያየኋቸው ሦስት ሰዎች ከለሎች አማኞች ጋር ግንኙነት ነበራቸው? ወይስ ብዙዎች በነዚያ በክፉ ቀኖች እንደነበሩ ተሰይተው ለብቻ ለብቻ ናቸው? በርግጥ፣ ይህንን የማውቅበት ምንም መንገድ የለኝም። ነገር ግን ከለሎች

ክርስቲያኖች ጋር ለሚኖራቸው ግንኙነት አንደኃጉ አውቃለሁ፤ ያለበለዚያ አምነታቸውን በተመለከተ ለኔ ምልክት ባላሳዩኝ ነበር።

በሞስኮ ጉብኝቴ ወቅት በከተማው ውስጥ በሚገኝ በሶቭየት ባለሥልጣኖች በተፈቀደለት በባፕቲስት ቤተክርስቲያን ሦስት ፕሮግራሞችን ተሳትፌአለሁ። በሦስቱም ጊዜዎች ከኋላ ተቀምጬ ነበር፣ አያንዳንዱ የስብከት ጊዜ ሁለት ለዓት የፈጀ ከመጽሐፍ ቅዱስ ስብከት (በተንሸከሸከ ትርጉም) በሁለቱ ፕሮግራሞች ሰምቻለሁ። (ከዛሃ አምስት ዓመታት በኋላ ግን በዚህ ቤተክርስቲያን ለመስበክ ልዩ መብት አግኝቻለሁ።) በብዙ መቶዎች የሚቆጠሩ ሰዎች በባለመደገፊያ አግዳሚ ወንበሮች ሞልተው ነበር፣ በሚወብቅ ሙቀት ውስጥ በመተላለፊያ መንገዶች ሁሉ ሰዎች ተጨናንቀው ነበር፣ ከቤቱም ውጭ ብዙዎች ችብችብ ብለው ተሰጥተው ያደምጡ ነበር። በክርስቶስ ያላቸውን የአምነት ጥልቀት መጠንና የአግዚአብሔርን ቃል ለማዳመጥ ያላቸውን ጉጉት በአንድ ዕይታ ከፊታቸው ማንበብ (መረዳት) ይቻላል። መከራዎችና ስጋቶች አለባቸው፣ ቤተክርስቲያን ማለት ለነርሱ ሸክም ሳትሆን ደስታ ነበረች።

ስብቻ አደደለችሁም

በዓመታት ውስጥ በሕይወት ዘመኔ በጣም ከታደልከባቸው ጉዳዮች አንዱ በብዙ ልዩ ልዩ የዓለም ክፍሎች ከክርስቲያኖች ጋር ለመገናኘት የመብቃት ዕድሌ ነው። ልዩ ልዩ ዘር ልንሆን እንችላለን ወይም የተለያየ ቤተ አምነት ወይም ባህል ሊኖረን ይችላል። ነገር ግን ከስዎች ገደብ የሚያልፍ አንድ ነገር የጋራ አንዳለን ባለማወላወል ተገንዝበናል፣ ሁላችንም የክርስቶስ ነን። እኔ እንደተረዳሁት፣ አግዚአብሔር በየቦታው በፍጹም በማይመች ቦታ እንኳን - ለዎች አለት፤ በክርስቶስ ካለን አምነት የተነሣ በመንፈስ ልንድ ሆነናል።

አንደ ግለሰብ ወደ አግዚአብሔር እንመጣለን፤ አያንዳንዳችን በየግል ራሳችንን ለክርስቶስ እንሰጣለን። በወላጆቻችን አምነት ወይም እኛ ወጣቶች በነበርንበት ጊዜ ሌሎች ስለ እኛ በሠሩልን፣ ወይም በቤተክርስቲያን አባልነታችን (እነዚህ ነገሮች ጠቃሚ ቢሆኑም) ልንደገፍ አንችልም። እያንዳንዳችን በየግል ኢየሱስን እንደምንታመነውና ጌታና አዳኝ አድርገነው እንደምንከተለው ሞወሰን አለብን።

ነገር ግን *ለኛ ግለሰብ ለማኞች ብቻ ሊይደለንም።* በእግዚ፡ሔር ዓይን ፊት ሁላችንም ደግሞ የአንድ አካል ብልቶች ነን፤ የክርስቶስ አካል ብልቶች ነን። አካሉም "ቤተክርስቲያን ነች" (ቆላ 1÷24)። ባህታዊ (ብቸኛ) ክርስቲያን መሆን ማለት መቃረን ማለት ነው፣ ምክንያቱም እኛ አያንዳንዳችን የመ·ሉ አካል ብልቶች ስለሆንን ነው። ልክ አንድ ወንድም ወይም አንዲት እህት ከቤተሰብ መካከል በሚነጠለብት ጊዜ አንድ ችግር በመኖሩ ምክንያት አንደሆነ ሁሉ ክርስቲያኖችም ከለማኞች ጋር ስመሆን ወይም ለመሥራት በሚቃወሙበት ጊዜ ችግር አንዳለ ያመለክታል። እና በዚህ የሕይወት ጉዞ በአንድነት ነን፤ እግዚአብሔርም ባንድነት ክርስቲያናዊ ሕይወት አንድንኖር ይፈልገናል።

ቤተክርስቲያን ምንድን ናት?

"ቤተክርስቲያን" የሚል ቃል በምትሰመ·በት ጊዜ በአዕምሮአችሁ ምን እንደምታስቡ እገረማለሁ። ሕንፃ ነው? ቤተእምነት ነው? የተወሰነ ማህበረ ምዕመናን ነው? ወይስ ማህበራዊ ክበብ?

አነኚህ ትርጉሞች የሚናቁ ባይሆንም፣ በመ/ቅዱስ ግን "ቤተክርስቲያን" የሚለው ቃል ሁለት መሠረታዊ ትርጉሞች አለ·ት። *አንደኛ፣ ቤተክርስቲያን ማለት በአጥቢያ ያለ· የክርስቲያኖች ቡድን ማለት ነው፣* ወይም በአንድ በተወሰነ ከተማ ወይም አካባቢ ያለ· ክርስቲያኖች በሞላ ማለት ነው። ለምሳሌ፣ "በኢየሩሳሌም ባለች ቤተክርስቲያን" (የሐዋ ሥራ 8÷1) ወይም "በአንጾኪያ ባለች ቤተክርስቲያን" የሐዋ . ሥራ 13÷1) ወይም "በቆርንቶስ ላለች ለእግዚአብሔር ቤተክርስቲያን" (1ቆሮ 1÷2) ሲል እናነባለን። በአዲስ ኪዳን ውስጥ የትም ቦታ "ቤተክርስቲያን" ሕንፃ እንደሆነች የሚያመለክት አናገኝም። (አብዛኛውን ጊዜ ክርስቲያኖች የሚገናኙት በመኖሪያ ቤቶች ውስጥ ነበረ።) በመጀመሪያው ክፍለ ዘመን የቤተክርስቲያን ሕንፃ ስላልነበረ ከሕንፃ ጋር አይያያዝም።

ሁለተኛ፣ ቤተክርስቲያን የሚለው ቃል በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ለማኞች ሁሉ ጓደኛሞች እንደሆኑ ያመለክታል፣ ከክርስቶስ ጋር ባላቸው ህብረት በመንፈስ የተያያዙ ማለት ነው። ቤተክርስቲያን የአጥቢያ (የአንድ አካባቢ) ማህበረ ምዕመናን አይደለችም፤ በየቦታው ያሉትን ለማኞች የምታቅፍ ነች - የሞቱና አሁን ከመንግሥተ ስማይ ያሉትን ሁሉ ትጨምራለች። እናቴ ልትሞት

በምታጣጥርበት ወቅት፣ ከክርስቶስ ጋር ስመሆን ብቻ ላይሆን ደግሞም በሞት ተወስደው በመንግሥተ ሰማይ ካሉ ወዳጆችና ቤተሰቦች አንድ ላይ ስመሆን ትፈልግ ነበር። የክርስቶስ ከሆናችሁ፣ በዘመናት ሁሉ ወደመንግሥተ ሰማይ የገቡ የማይታየው ትልቅ የለማኞች ህብረት አካል ናችሁ። መጽሐፍ ቅዱስ፣ "ክርስቶስ የቤተክርስቲያን ራስ እንደሆነ አርሱም አካሉን የሚያድን አንደሆነ" (ኤፌ 5÷23) ይነግረናል።

የእያንዳንዱ ስጦታ

መጽሐፍ ቅዱስ ከእግዚአብሔር የተሰጣችሁ ስጦታ ነው፣ እንዲሁም መሰል ክርስቲያኖች ከርሱ የተሰጠ·አችሁ ስጦታዎች ናቸው። እግዚአብሔር አንዳችንን ለሌላው ሰጥቶናል። እግዚአብሔር እኛን ለመቅረጽ (ለማላመር) እና በይበልጥ ክርስቶስን አንድንመስል ከሚጠቀምባቸው ዋና መሣሪያዎች አንዱ የክርስቲያኖች ህብረት ነው። *በርግጥ፣ ከሌሎች ለማኞች ጋር ንቁ የሆነ ግንኙነት ከሌለን፣ የመንፈሳዊ ሕይወታችን ዕደገት ይቀጭጫል።* መጽሐፍ ቅዱስ፣ "ብረት ብረትን እንደሚስል፣ ሰውም ባልንጀራውን ይስላል" (ምሳሌ 27÷17) ይላል። ከሌሎች ለማኞች ጋር የሚኖረን ህብረት ከእግዚአብሔር የተሰጠ ስጦታ ነው።

አንዳንድ ስዎች ከቤተክርስቲያን ጋር ወይም ቢያንስ ቢያንስ የአጥቢያ ቤተክርስቲያን አባል በመሆን ፍላጐት ጉዳይ ችግሮች አሏቸው። በቅርቡ አንድ ሰው፣ "አልፎ አልፎ ወደ ቤተክርስቲያን አሄዳለሁ፣ ነገር ግን በአውነት የምገልጽልህ ጉዳይ ቢኖር ወደ እግዚአብሔር የቀረብኩ የሚመስለኝ ዕሑይ ስትጠልቅ ያላትን ውበት ስመለከት ወይም በጫካ (በዛፎች) መካከል ስንሽራሸር ነው" በማለት ጻፈልኝ። ሌላው ሰው ፍርጥ አድርጐ፣ "የእግዚአብሔር መገኘት የሚለማኝ አየር ክሌላው ከታጨቀ ከአሮጌ ቤተክርስቲያን ውስጥ ይልቅ በጎልፍ ጨዋታ (ትንሽ ሩር በዱላ እየመ·ቱ ጉድጓድ ውስጥ የማስገባት ጨዋታ) ሥፍራ ነው" ብሎ· ጻፈልኝ። በተለይ የአንዲት ሴት ደብዳቤ፣ "ወደቤተክርስቲያን በፍ፡ፀም ሂጀ አላውቅም፣ ባለፈው ሳምንት ለመሄድ ድፍረት ተሰምቶኝ ነበር፣ ነገር ግን ማንም አላነጋገረኝም። ስለ ቤተክርስቲያን ለምን እጥገራለሁ?" በማለት የጻፈችው አላዝኖኛል።

ለምን እቸገራለሁ?

የሴትዮዋ ጥያቄ ብዙዎች፣ ክርስቶስ ጋር ጠንካራ ቃል ኪዳን ያደረጉ እንኳን ሳይቀሩ፣ የሚጠይቁት ዋና ጥያቄ ነው። በአጥቢያ (በአንድ አካባቢ) ማህበረ-ምዕመናን አባላት ሆነን ባንድነት የተሰባሰብነው ለምንድነው? ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ቢያንስ አራት ምክንያቶችን አቀርባለሁ።

አንደኛ፣ አማዚአብሔርን ለማምለክ አንድነት ያስፈልገናል። እግዚአብሔር ለምሥጋናችን ዋጋ ይሰጠዋል፣ በመሆኑም ስናመልከው እናከብረዋለን። በብሉይ ኪዳን ዘመን የእግዚአብሔር ሰዎች፣ "ወደ ደጆቹ በመግዛት ወደ አደባባዮቹም በምሥጋና ግቡ፣ አመስግኑት፣ ስሙንም ባርኩ" (መዝ 100፥4) ተብለው ታዘው ነበር። መጽሐፍ ቅዱስ በህብረት የምንሆነው፣ "በመዝሙርና በዝማሬ በመንፈሳዊም ቅኔ በጸጋው በልባችሁ ለእግዚአብሔር ዘምሩ" (ቆላ 3፥16) ስለተባልን እንደሆነ ይነግረናል።

የተለያዩ ቤተክርስቲያናትን ጉብኝታችሁ ከሆነ፣ የአምልኮአቸው ሥርዓት (መንገድ) እንድ ዓይነት እንዳልሆነ ታውቃላችሁ። አንዳንዶች በእገልግሎታቸው በጣም ግልጽ አይደሉም፣ የአንዳንዶች በጣም የታወቀ ሲሆን የብዙዎች ደግሞ ከሁለቱም ያልሆነ ነው። አንዳንድ ቤተክርስቲያናት (የጌታ እራት አገልግሎትን በተመለከተ) ከሌሎች በበለጠ ሁኔታ ለቅዱስ ቀርባን ሥነ ሥርዓት ትኩረት ይሰጣሉ።

አምልኮን በተመለከተ ካንድ መንገድ በለተቀር ሌሎች ሁሉ ስህተት ናቸው ማለት ነው? በርግጥ አይደለም። የአናንተ የአምልኮአችሁ መንገድ ከሌሎች ይልቅ ለናንተ ምቹ ሊሆን ይችላል፣ ዋናው ነገር በአምልኮና በምስጋና ልባችሁን ወደ እግዚአብሔር መመለስ ላይ ነው። (ይሁን እንጂ፣ ከናንተ በተሰየ መንገድ የሚያመልኩትን አትናቁ። እግዚአብሔር አምልኮአችንን ከምናቀርብበት መንገድ ይልቅ ልባችንን ይመለከታል።) አምልኮ እንደ መዝናኛ ሲታሰብ አይገባም፣ በህብረት የምንሆነው እግዚአብሔርን ለማምለክ እንጂ ራሳችንን ለማዝናናት አይደለም። ኢየሱስ እንዲህ አለ፣ "ነገር ግን በእውነት የሚሰግዱ ለአብ በመንፈስና በእውነት የሚሰግዱበት ጊዜ ይመጣል፣ አሁንም ሆኖአል፣ አብ ሊሰግዱለት እንደ እነዚህ ያሉትን ይሻልና" (ዮሐ 4፥23)። ይህን አስተውሉ፣ እግዚአብሔር በእውነት የሚሰግዱለትን (የሚያመልኩትን) ይሻል።

ሁለተኛ፣ የእግዚአብሔርን ቃል በአንድነት ለመለማመድ ህብረት ያስፈልገናል። እግዚአብሔር መጽሐፍ ቅዱስን በግል በምናጠናበት ጊዜ ይናገረናል፣ ነገር ግን ደግሞ ሌሎች ከመጽሐፍ ቅዱስ እንዲያስተምሩና እንዲቀስቅሱ ወይም እንዲሰብኩን ልዩ ስጦታ ሰጥቷቸዋል፣ በህብረት የምንሆንበትም አንዱ ምክንያት ከነርሱ ለመማር ነው። መጽሐፍ ቅዱስ፣ እግዚአብሔር፣ "አንዳንዶቹ . . . አረኞችና አስተማሪዎች እንዲሆኑ ሰጠ" (ኤፌ 4፥11) ይላል። ጳውሎስ፣ "የእግዚአብሔር ቃል በሙላት ይኑርባችሁ፣ በጥበብ ሁሉ እርስ በርሳችሁ አስተምሩና ገሥፁ" (ቆላ 3፥16) በማለት ጽፏል።

የተለያዩ ሰዎች ከጊዜ ወደ ጊዜ እንዲህ እያሉ ይጽፉልኛል፣ "ከቤተክርስቲያን የማገኘው ነገር የለም"። ብዙውን ጊዜ እነዚህ ሰዎች በሳምንት አንድ ቀን የሚሄዱ እንደሆኑና ቤተክርስቲያን በምትሰጠቸው በሌሎች ዕድሎች - በክፍል ውስጥ የእግዚአብሔርን ቃል መማር፣ በቡድን የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናቶች፣ ልዩ ድርጊቶች፣ በመንፈሳዊ ሽርሽሮችና በመሳሰሉ - ስለማይካፈሉ እንደሆነ ደርሼበታለሁ። አንዳንድ ጊዜ የመጋቢያቸውን ስብከት በማስታወሻ እንዲይዙ እመክራቸዋለሁ። ይህ ዓይነቱ ልምምድ ዋና ነጥቦችን እንዲያስታውሱ የሚያግዛቸው ከመሆኑም በላይ መጋቢያቸው ይህን ሲያውቅ በበለጠ በጥንቃቄ እንዲዘጋጅበት ያበረታተዋል።

ሰስተኛ፣ እርስ በርስ ለመተናነጽ ህብረት ያስፈልገናል። በሕይወቱ ምንም ዓይነት ችግር እጋጥሞት የማያውቅ ሰው ገጥሞኝ አላውቅም። እንደዚሁም ከፈተናዎች ወይም ከተፅዕኖዎች ነፃ የሆነ አማኝ ገጥሞኝ አያውቅም፣ አንዳንድ አማኞች ክርስቲያን የመሆን ፋይዳው ምኑ ላይ ነው እስኪሉ ድረስ ችግር ሲገጥማቸው ይችላል። የእርስ በርስ ማበረታቻና (ምክር) ጥበብ የሚያስፈልገንም ለዚሁ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ እንደዚህ ይላል፣ "አንዳንዶች ማድረጉን እንደተውት መሰባሰባችንን እንተው፣ ይልቁንም ቀኑ (ክርስቶስ የሚመለስበት) እየተቃረበ መምጣቱን ስታዩ እርስ በርሳችን እንበረታታ" (ዕብ 10፥25)።

አንዳንድ ጊዜ ለራሳችን ላይታወቀን ሌሎች ለምችን ልንመክር (ልናበረታታ) እንችላለን። የአንድ ሰባኪ ወይም የመጽሐፍ ቅዱስ አስተማሪ መልእክት ከለማሁ በኋላ "ይህ መልእክት በትክክል እኔን የሚመለከት ነው" ያልከባቸው ጊዜያት በርካታ እንደሆኑ አስታውሳለሁ። እናንተ ራሳችሁ ባታውቁትም አንኳን አዘወትራችሁ ወደ ቤተክርስቲያን መሔዳችሁ አግዚአብሔርን እየፈለገ ላለ ለው መልካም ማበረታቻ ሊሆን ይችላል።

ክአማኞች ጋር በመገናኘትም በግል ሁኔታ አንኳን አንዳችን ሌሎችን ልናበረታታ እንችላለን። በአምነትና በአገልግሎት ዘመኔ፣ ጊዜአቸውን በመስዋ ት ለአኔ ስመፀለይ የፈ ቀዱ የአግዚ አብሔር ሰዎች ታላቅ የብርታት ምንጭ ሆነውኛል። ክሌሎች አማኞች ጋር ስንሆን፣ በመቶ የሚቆጠሩ ሰዎች ጋር በአምልክ አገልግሎት ሥፍራ ሆነን ወይም ካንድ ክርስቲያን ጓደኞችን ጋር ቡና እየጠጣን ስንጨዋወት፣ አግዚአብሔር አነርሱ በሚለጡን አይዞህ ባይነትና ምክር አማካይነት ሊያበረታታንና አምነታችንን ሊያላድግ ይችላል። ባልና ሚስቶች በጋራ በመጸለይና መጽሐፍ ቅዱስን በማንበብ አርስ በርስ ሊበረታቱ ይገባቸዋል።

የዕብራውያን መልእክት ጸሐፊ አንዲህ ይላል፣ "ከመካክላችሁ ማንም በኃጢአት ተታሎ ልቡ አንዳይደነድን ..... በየቀኑ አርስ በርሳችሁ ተመካከሩ (ዕብ 3፥13)። ጳውሎስ ለተሰሎንቄ ክርስቲያኖች፣ "አርስ በርሳችሁ ተመካከሩ፣ አንዱ ሌላውን ያንጽ" (1 ተሰ 5፥11) ብሏል። ጳውሎስ በመጀመሪያው የወንጌል ስብከት ጉዞው አብሮት የነበረው ለው በርናባስ ነበር፣ የስሙ ትርጉም፣ "የመጽናናት ልጅ" (የሐዋ.ሥራ 4፥36) ማለት ነው። በርናባስ የሚታወቅበት መለያ ባህርይው ለምችን ማፅናናት ነበር። ይህ እኛም ልንታወቅበት የሚገባን ነገር ነው።

አራተኛ ሌሎች ሰዎችን በክርስቶስ ፍቅር ለመድረስ ሀብረት ያስፈልገናል። ክበርካታ ዓመታት በፊት በአንዲት የአሜሪካ የገጠር ክተማ ትንሽ ልጃቸው ክቤት ስለጠፋበት ቤተሰብ ታሪክ በጋዜጣ

ላይ አንብቤ ነበር። የመኖሪያ ቤቱ ዙሪያውን በመሉ ለአጨዳ በተቃረበ የስንዴ ማሳ የተከበበና በማሳው መካከል ላይ ያለ ነበር።

በመቶዎች የሚቆጠሩ የቤተሰቡ ወዳጆችና ጎረቤቶች ልጁን ለማግኘት ጥረት ቢያደርጉም አልተሳካላቸውም። ልጁ በአቅራቢያቸው ሊሆን ቢችልም አንኳን ጥቅጥቅ ያለውና ክፍ ያለው የስንዴ ማሳ ስለሚሸፍነው ሊያዩት አይችሉም።

በመጨረሻም ሁለት ቀናት ካለፉ በኋላ አባትዬው የሚያደርገውን ሊያጣ ፈላጊዎች በአንድነት ሆነው ማሳው ውስጥ አሰሳ እንዲያደርጉ ሃሳብ አቀረበ። ሁለት ሺህ ያህል ሰዎች ማሳውን እያለሱ ሩብ ማይል ያህል እንደተጓዙ የልጁን ሀይወት አልባ አካል አገኙ። ልቡ በሀዘን የተሰበረው አባት አሰሳውን ትንሽ ቀደም ብለው ቢያካሄዱ ኖሮ ልጁ በሕይወት ሊገኝ ይችል እንደነበር በቁጭት ተናገረ።

በዙሪያችን ያሉ ብዙ ለምች ከለማያዊ አባታቸው ጠፍተውና ተለይተው ያሉ ናቸው፤ እና ለእነዚህ ለምች ስለ እግዚአብሔር የመናገር ኃላፊነት አለብን። የሚወዳቸውንና ወደ ክርስቶስ የሚያመለክታቸውን ለው ይፈልጋሉ። ከሌሎች ክርስቲያኖች ጋር ሀብረት ብንመሰርት፣ እነዚህን ሰዎች ለመርዳት የበለጠ ማድረግ እንችልም? ጥቂቶቻችን በግል የወንጌል ለባኪን ልንረዳ እንችላለን፣ ወይም ቤት አልባ ለሆኑ ሰዎች መጠለያ ልንሠራ እንችላለን፣ ወይም በረሃብ ለተጠቃ አገር አይሮፕላን መሉ ምግብ መላክ ወይም በለፈራችን የተባበረ የፀሎት እንቅስቃሴ ልንጀምር እንችላለን። በአንድነት ብንሰባሰብ ግን የበለጠ እንችላለን! መጽሐፍ ቅዱስ እረኞችና አስተማሪዎች፣ "ቅዱሳንን ለአገልግሎት ሥራ ለማዘጋጀት" (ኤፌ 4፥12) እንደተጠሩ ይነግረናል።

የሚስማማን ቤተክርስቲያን ማግኘት

ክርስቲያናዊ ጎብረት፣ በቤተክርስቲያን ማጎበረ ምዕመናን ብቻ የተገደበ አይደለም፣ ከአንድ ወይም ሁለት ክርስቲያኖች ጋር ጥልቅ ትስስር በመመሰረት የጎብረትን በረከት ልታገኙ ትችላላችሁ። አየለስ ዐሥራ ሁለት ደቀመዛሙርት ብቻ ነበሩት

(ከመካከላቸው አንዱ ከነጭራሹ እውነተኛ ደቀመዝሙር አልነበረም) ሆኖም ሕይወቱን በእነርሱ ላይ በማፍሰሱ ዓለምን የሚለውጥ ሥራ ለርተዋል። ምናልባትም እግዚአብሔር አንድ ወይም ሁለት ክርስቲያኖችን ንደኛ በማድረግ በእምነት እንዲያድጉ እንድትረዷቸው ጥሪ እያቀረበላችሁ ይሆናል። ጳውሎስ ለወጣት የአገልግሎት አጋሩ ለሆነው ለጢሞቴዎስ እንዲህ ሊል ይመክረዋል "ከእኔ የሰማኸውን ሌሎችን ለማስተማር ብቃት ላላቸው ለታመኑ ለዎች አደራ ስጥ" (2 ጢሞ 2፡2)።

ይሁንና በግለሰብ ደረጃ የምናደርገው ኀብረት ለማኅበረ ምዕመናን ኀብረት ምትክ አይደለም። ክርስቶስ በሚሰበክባትና መጽሐፍ ቅዱስን የምታስተምር ቤተክርስቲያን አባላት ከሆናችሁ ለለዚህ ነገር እግዚአብሔርን አመስግኑ፣ መንፈሳዊ መታነጽ ሊሰጧችሁ የሚችሉ ማንኛቸውንም አጋጣሚዎች ተጠቀሙ። የቤተክርስቲያን አባላት ካልሆናችሁ (ወይም አሁን ባላችሁበት ቤተክርስቲያን በመንፈሳዊ ሕይወት እያደጋችሁ ካልሆነ) እግዚአብሔር ለናንተ ወዳዘጋጀላችሁ ቤተክርስቲያን እንዲመራችሁ ጠይቁት። አዲስ አማኝ ከሆናችሁ ወይም ለቤተክርስቲያን አዲስ ከሆናችሁ መጀመሪያ ላይ ሁሉም ነገር ላይገባችሁ ቢችልም፣ ሐፍረት አይያዛችሁ። መቆም ሊገባችሁ ባትቆሙ ወይም ከመዝሙር መጽሐፍ ላይ የሚዘመረውን መዘመር ገጹን መለየት ካልቻላችሁ፣ ክርስቶስን የሚወዱ ለዎች አይንቁአችሁም፣ ይልቁንም ለናንተ ለለሚጠነቀቁ ሊረዷችሁ ይችላሉ።

ለናንተ የሚሆናችሁን "ትክክለኛ" ቤተክርስቲያን የምታገኙት እንዴት ነው? በአካባቢያችሁ ያሉ የሌሎች ክርስቲያኖችን ምክር ጠይቁ፣ ለለተለያዩ ቤተክርስቲያናት ለማወቅ ሞክሩ፣ የቻላችሁትን ያህል የተለያዩ ቤተክርስቲያናትን በመጎብኘት የሚስማማችሁን ለመምረጥ ወስኑ። በተጨማሪም ይህን ምርጫ ለታደርጉ ያላችሁበትን ሁኔታ ከግምት አስገቡ። ለምሳሌ፦ ልጆች ካሉአችሁ ክርስቶስን ማዕከል ያደረገ የተነቃቃ የወጣቶች ፕሮግራም ያለው ቤተክርስቲያን አባል መሆኑ መልካም ነው። ላምንታዊ የአምልኮ ፕሮግራም አስፈላጊ ቢሆንም ሌሎች ፕሮግራሞች ለምሳሌ፦

የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት፣ የተሃድሶ ፕሮግራም፣ በተለያዩ ዕድሜ ላሉ ለዎች የሚሆኑ ፕሮግራሞች አንዳሉ ማየቱ ጠቃሚ ሊሆን ይችላል። በተጨማሪም፣ የመዘምራን፣ የማኅበራዊ አገልግሎቶች፣ የወንጌል ስብከቶች አገልግሎቶች፣ እና የመሳለሉትን ልትሳተፉ የምትችሉባቸውን ዕድሎች መመልከቱ ጠቃሚ ነው። ጥምቀት ወለዳችሁ የማታውቁ ከሆነም፣ ቤተክርስቲያንን ስትቀላቀሉ ይህን ይፋዊ ውሳኔ የአዲስ ሕይወታችሁ አካል አድርጉት።

ከሁሉም በላይ ግን፣ እግዚአብሔር እንዲመራችሁ ጸልዩ። ምክንያቱም እርሱ ለአናንተ የሚሆናችሁን ቤተክርስቲያን ያውቃል። ፍፁም ቤተክርስቲያን የለም፣ ሆኖም በዚህ ሳቢያ ልባችሁ ሊዝል አይገባም። አንድ ለው እንደተናገረው "ፍፁም የሆነች ቤተክርስቲያን ካገኛችሁ እናንተ በተቀላቀላችኋት ቅጽበት ፍጽምናዋ ያበቃል" ሊል ተናግሯል።

እግዚአብሔር ያዘጋጀላችሁ ይህ ጉዞ ብቻችሁን የምትጓዙት አይደለም። እግዚአብሔር ከናንተ ጋር ነው፣ እንደዚሁም የእርሱ ሕዝብ አብሯችሁ ነው። ለናንተ አንደሚያስፈልጓችሁ ሁሉ፣ እናንተም ለነርሱ ታስፈልጋላችሁ።

ዐሥራ ዐራት

ዘወትር የማይሰየን አጋዣችን

ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ በመረደ ጊዜ ኀይልን ተቀበላላችሁ።

(የሐዋ.ሥራ 1፥8)

በዓለም ውስጥ ክርስቲያንን ከሌላ ሰው የሚለየው ምንድነው?

በርግጥ፣ ይህን ጥያቄ በተለያዩ መንገዶች ልንመልሰው እንችላለን። አንድ ክርስቲያን፣ ክሌሎች ክርስቲያን ካልሆኑ ጓደኞች የሚለየው የቤተክርስቲያን አባል ስለሆነ ነው ሊል ይችላል። ሌላዋ ደግሞ ክሌሎች የሚለየኝ ኃጢአቴ ይቅር ስለተባለና ወደመንግሥተ ሰማያት ስለምሔድ ነው ልትል ትችላለች። ሌላ ሰው ደግሞ ክርስቲያኖችን ክሌሎች የሚለያቸው የሚያምኑት ማስትም መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል መሆኑን፣ ኢየሱስ ስለ ኃጢአታችን የሞተ አምላክ የሆነ የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን ሌሎችንም ሊል ይችላል። ሌላ ሰው ደግሞ ክርስቲያኖች የሚሰዩት በአኗኗራቸው ነው ሊል ይችላል (ታላቢ ተመልካች የሚያውቃቸውን ክርስቲያኖች ግን ይህ ነው የሚባል ልዩነት እንደሌላቸው ሊናገር ይችላል)።

በውስጣችን ያለው መንፈስ

እነዚህ አስተያየቶች ሁሉ እውነት የሆነ ነገር ቢኖራቸውም ምሉዕ ስዕል ግን አይሰጡም። እንዲያውም፣ እግዚአብሔር በተሰመልን በዚህ መንገድ ላይ ለንጓዝ ልናስተውሰው የሚገባንን

አንድ ወሳኝ እውነት ይዘላሱ። ይህም ክርስቲያንን ክሌላ ክማንኛውም ሰው የሚለየው እግዚአብሔር ራሱ በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት በውስጡ የሚያድር መሆኑ ነው። ወደ ክርስቶስ ስንመጣና ሕይወታችንን ለእርሱ ስንሰጥ፣ እግዚአብሔር በልባችን ማደር ይጀምራል። ሁልጊዜ የተሰየ ስሜት ሳይሰማን ወይም ህልሞቱ (መገኘቱ) ላይታወቀን ይችላል። ይሁንና ኢየሱስ ለደቀመዛሙርቱ የሰጣቸው የተስፋ ቃል ተፈጽሟል፣ "እኔ አብን እለምናለሁ፣ እርሱም ከእናንተ ጋር ለዘላለም የሚኖር ሌላ አጽናኝ ይሰጣችኋል፣ እርሱም የእውነት መንፈስ ነው" (ዮሐ 14፥16 - 17)።

በወንጌል ስብከት ፕሮግራም ላይ ክርስቶስን በተቀበልኩበት ምሽት የተሰየ ኃይለኛ ስሜት አልተሰማኝም። ክአጠገቤ የነበረችው ሴት ስታስቅስ ሳያት፣ እኔ የማላስቅሰው አንድ ችግር ቢኖርብኝ ይሆናል ብዬ ማሰቤን አስታውሳለሁ።

ይሁንና በውስጤ አንድ የተሰየ ነገር እንደተከሰተ አውቄ ነበር፣ በኋላ ላይ የዚህ ምክንያቱ መንፈስ ቅዱስ በውስጤ ሰማደር ስለመጣ እንደሆነ አወቅኩ። መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፣ "ማንም የክርስቶስ መንፈስ ከሌለው፣ እርሱ የክርስቶስ አይደለም" (ሮሜ 8፥9)። ሕይወታችሁን ለክርስቶስ ከሰጣችሁ እግዚአብሔር አሁን በመንፈሱ በውስጣችሁ ይኖራል። ክርስቲያን ከሆናችሁ ወደሕይወታችሁ እንዲመጣ ልትለምኑት አያስፈልጋችሁም። አሁንም በውስጣችሁ ነው፣ በውስጣችሁ መኖሩን በመቀበል በእምነት ለእርሱ ኃይል መገዛት ብቻ ነው የሚያስፈልጋችሁ።

የእግዚአብሔር ኀይል ያስፈልጋችኋል

ሰው እንደ መሆናችን ሁለት ታላላቅ መንፈሳዊ መሻቶች አሉን። የመጀመሪያው፣ የኃጢአት ይቅርታ ሲሆን፣ ይህን እግዚአብሔር ልጁን ወደዓለም በመላክ አሟልቶልናል። ሁለተኛው፣ የሚያስፈልገን በጎነት ሲሆን፣ ይህንን እንድናገኝም እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስን በውስጣችን እንዲያድር ልኮልናል።

እግዚአብሔር እንዳቀደልን መኖር እንችል ዘንድ . . . ክርስቶስን በመምሰል እናድግ ዘንድ . . . ጉዞአችንን በጥበብ እንንዝ ዘንድ . . . የእግዚአብሔር ይቅርታና በሳንት ያሰፈልገናል። ወልደ ሰኛ ያደረግልንና መንፈስ ቅዱስ በኛ ውስጥ የሚሠራው ሥራ ያስፈልገናል። *እግዚአብሔር በታላቅ ይቅርታው ላይ የመንፈስ ቅዱስን ታላቅ ስጦታ ጨምሮልናል።* አንድ ጊዜ አንድ ጓደኛዬ፣ "ኢየሱስ ክርስቶስ ለዘላለም ሕይወት ያስፈልገኛል፣ መንፈስ ቅዱስን ደግሞ ለውስጥ ሕይወቴ እፈልጋለሁ" አለ።

መንፈስ ቅዱስ በእውነት ሊለውጠን ይችላል? ከበርካታ ዓመታት በፊት ዝቅተኛ የማንበረበብ ክፍል ሰዎች በሚኖሩበት በስንደን አካባቢ የሚኖር አንድ የቤተክርስቲያን አገልጋይ በደብሩ ለሚኖሩ በመርከብ መቆማያ (በወደብ) የሚሠሩ ኑሮአቸው ሰላሳዘነው አንድ ነገር ሊያደርግላቸው ወሰነ። ሥራቸው ከባድና አስቸጋሪ፣ ምሰጋና የማይቀበሉበትና ደሞዛቸው የማይረባ ነበር። ይህ አገልጋይ እነዚህን ሰዎች በወንጌል ለመድረስ፣ የተሻለው መንገድ እንደነርሱ መሆን እንደሆነ ተገነዘበ። በየቀኑ እንደነርሱ ለብሶ፣ ማንነቱን ለማንም ሳያሳውቅ፣ ሥራ ለማግኘት ከመካከላቸው ወረፋ ይጠብቅ ነበር። በመጨረሻው የክረምት ወራት አንድ ቀን ከዕቃ ተሸካሚ መርከብ ላይ እቃ የማውረድ ሥራ አገኘ፣ ይህም በስንዲት ቀጭን ጠርብ ላይ በእጅ ጋሪ ከጀልባ ወደ ወደብ ዕቃ ማመላለስ ነበር። በመጀመሪያ ጉዞው ጠርቡ በኃይል ሊናቃነቅ እግሩ ላተና ቀዝቃዛ ውሃ ውስጥ ወደቀ። ሰዎቹ በሳቅ አውካኩ፣ ኋላ ላይ ከሰዎቹ መካከል አንደኛው ውሃ ውስጥ እንዲገባ ሆነ ብሎ ጠርቡን (ሳንቃውን) እንደነቀነቀው ተረዳ።

በመጀመሪያ የመጣለት ነገር በቁጣ ሰዎቹን መናገር ነበር (ከዚያ በፊት ብዙ ጊዜ ራሱን ለመቆጣጠር ሞክሯል) - ሆኖም ወዲያውኑ የመንፈስ ቅዱስ ኃይል ቁጣውን በ መግራት ሰላም ሰጠው። እርሱም ፈገግ አለና ከእነርሱ ጋር መሳቅ ጀመረ፣ በዚህ ጊዜ በሚያስገርም ሁኔታ ይህን ተንኮል የሠራው ሰው ሸክሙን አውርዶ ከውሃ ውስጥ እንዲወጣ ረዳው። ከለስቃይነት ወደ ታዳጊነት የተለወጠው ባልደረባው፣ አገልጋዩ ባሳየው ለላማዊ ምላሽ በመደነቅ ከእርሱ ጋር መነጋገር ጀመረ። ኋላ ላይ ተንኮል ሠሪው የተከበረ ሐኪም እንደነበርና ሆኖም ግን በአልኮል ሱሰኝነት ምክንያት ከሥራውና ከቤተሰቡ እንደተለየ በሐፍረት ነገረው። አገልጋዩ ይህን ሰው ወደ ክርስቶስ መራው፣ ከተወሰነ ጊዜ በኋላ ሰውዬው ከቤተሰቡ ጋር ዳግመኛ ተቀላቅሎ ወደቀድሞ ሥራውና ክብሩ ተመለሰ። እዚህ ላይ ዋናው ነገር ይህ ነው፣ የእግዚአብሔር መንፈስ የአገልጋዩን ሰሜት በመግዛት በገርነትና በክርስቶስ መንፈስ ባይሞላው ኖሮ ይህ አሰደናቂ ለውጥ አይከሰትም ነበር። ሰውጡ የተከሰተው በመንፈስ ቅዱስ ነው።

የውስጥ ለውጥ

በርካታ ክርስቲያኖች ይህን እያስተውሉም። የተሻሉ ሰዎች መሆን እንዳለባቸው ያውቃሉ፣ ባለ በሌለ ጉልበታቸው ዐመሳቸውን ለማሻሻል ይሞክራሉ። ይሁንና ራሳቸውን ለመለወጥ በራሳቸው የሚያደርጉት ጥረት ግብ ላይመታ ይቀራል፣ ለለዚህም ልባቸው ይዝልና ተሰፋ ይቆርጣሉ። ሐዋርያው ጳውሎስ የተናገረው ቃል የነዚህን ሰዎች ሁኔታ በትክክል የሚገልጥ ነው፣ "በጎ የሆነውን የማድረግ ምኞት አለኝ፣ ነገር ግን ልፈጽመው አልችልም። የማደርገው ላደርገው የምፈልገውን በጎ ነገር አይደለም፣ ዳሩ ግን ለማድረግ የማልፈልገውን ክፉ ነገር ነው" (ሮሜ 7፣18-19)

ችግሩ ምንድን ነው? ችግሩ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ላይ ላይሆን በራሳችን ኃይል ላይ መደገፋችን ነው። እግዚአብሔር እንዴት ልንኖር እንደሚገባ እንደሚፈልግ ማወቅ ብቻ ላይሆን፣ ይህን ማድረግ የምንችልበት ኃይልም ያሻናል። በመሆኑም እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስን በመስጠት ኃይል ሰጥቶናል። ሊያስተምረን መጽሐፍ ቅዱስን እና እንዲመክሩንና እንዲያበረታቱን ሌሎች ክርስቲያኖችን ሰጥቶናል - ይሁንና ደግሞም ሕይወታችንን እንዲለውጥ መንፈሱንም ሰጥቶናል። በዙሪያችን የሚያግዙን ክርስቲያኖች ከመኖራቸውም ባሻገር በውስጣችንም መንፈስ ቅዱስ አለ። እርሱ ዘወትር የማይተወንና የማይለወጥ የጉዞ ጓደኛችን ነው።

መንፈስ ቅዱስ ማን ነው?

ለዎች ስለመንፈስ ቅዱስ ብዙ ዓይነት አስተሳሰቦች አሏቸው - ከነዚህ አንዳንዶቹ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ሊሆኑ ሌሎቹ ግን አይደሉም። አንዳንዶቹ መንፈስ ቅዱስን ለብዕና (አካል) እንደሌለው ኃይል ይመለከታሉ፣ ለምሳሌ እንደ ኤሌክትሪክ ኃይል ወይም የስበት ኃይል ያስቡታል። ሌሎች ደግሞ መንፈስን የሚያስቡት ከስሜት ጋር በተያያዘ ብቻ ነው፤ የእግዚአብሔር መገኘት በውስጣቸው እንደሚሰማ ቢያስቡ፣ ይህን ስሜት ‹‹መንፈስ ቅዱስ›› ብለው ይሰይሙታል። ሌሎች ደግሞ መንፈስ ቅዱስ ስለሚሰጣቸው ስጦታዎች ያስባሉ። እነዚህ ግን ዋናውን ቁምነገር ይስታሉ።

መጽሐፍ ቅዱስ ስለመንፈስ ቅዱስ *ሶስት ዓቢይ እውነቶችን* ይነግረናል።

አንደኛ፣ መንፈስ ቅዱስ ሰብእ ነው። ስብዕና ያለው አካል ያሉት ባህርያትና መገለጫዎች ሁሉ አሉት። ይናገረናል፣ ያዘናል፣ ለእኛ ይማልዳል፣ ይሰማናል፣ ይመራናል፣ ወዘተ። በተጨማሪም ልናሳዝነው ወይም ልንዋሸው እንችላለን፤ ከዚያም ባሻገር ልንሰድበው ወይም ልናስከፋው እንችላለን። እነዚህ ነገሮች በግዑዝ ኃይል ላይ ልናደርጋቸው የምንችል ነገሮች አይደሉም፤ ይልቁንም እነዚህን ማድረግ የሚችለው እርሱ ሰብእ ስለሆነ ነው። "የእግዚአብሔር ልጆች መሆናችንን ያ መንፈስ ራሱ ከመንፈሳችን ጋር ሆኖ ይመሰክርልናል" (ሮሜ 8፥16)።

ሁለተኛ፣ መንፈስ ቅዱስ ኃይል ነው። መንፈስ ቅዱስ፣ እግዚአብሔር ኃይሉን በዚህ ምድር ላይ ለመግለጥና ፈቃዱን ለማከናወን የሚሠራበት የማይታይ አስተሳላፊ ነው። ዓለማት ከመፈጠራቸው በፊት "የእግዚአብሔር መንፈስ በውሆች ላይ ይለፍፍ ነበር" (ዘፍ 1፥2)። እዮብ እንዲህ ሲል ደመጸል፣ "የእግዚአብሔር መንፈስ ፈጥሮኛል" (እዮብ 33፥4)። ሳምሶን "የእግዚአብሔር መንፈስ በኃይል እንደ ወረደበት" እና ካሠሩት ለዎች ራሱን ነጻ ማውጣት እንደ ቻለ እናነባለን (መሳ 15፥14)። እግዚአብሔር ባስልኤልን ለዎች ለአምልኮ የሚሰበሰቡበትን የመገናኛ ድንኳን እንዲገነባ ኃላፊነት ሲሰጠው እንዲህ ብሎታል፣ "በሁሉም ዓይነት የእጅ ጥበብ ሥራ፣ ብልሃት፣ ችሎታና ዕውቀት እንዲኖረው የእግዚአብሔርን መንፈስ ሞልቼዋለሁ" (ዘፀ 31፥3)

ከዚህም በላቀ ሁኔታ የመንፈስ ቅዱስ ኃይል የእግዚአብሔርን ቃል በመጠቀም ስለኃጢአታችን በመውቀስ አዲስ ልደትን ይለጠናል። በተለያዩ የዓለም ክፍሎች በየምሽቱ ወንጌልን ከሰበኩትና ሰዎች ሕይወታቸውን ለክርስቶስ እንዲሰጡ ጥሪ ካቀረብኩላቸው በኋላ፣ በውስጤ ለእነርሱ ጥልቅ ሸክም ይሰማኛል። አንዳንድ ጊዜ እቅመቢስነትና ብቁ ያለመሆን ስሜት ይጫነኛል፤ ወንጌሉን ግልፅ አድርጌ ለማቅረብ የሚገባኝን ያህል አድርጌ ይሆን? ስል ራሴን እጠይቃለሁ። ይህንና ለዎቹ እውነቱን ማየት እንዲችሉ ዓይናቸውን ሊከፍት የሚችለው መንፈስ ቅዱስ ብቻ እንደሆነም እውቃለሁ፤ ከበርካታ ዓመታት በኋላ ወደዚያው ስፍራ ስንመለስ መንፈሳዊ ጉዞአቸውን በዚያች ቅዕበት የጀመሩ ለዎች ይገጥሙኛል። መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል "ቃሌ በከንቱ ወደ እኔ አይመለስም፤ ነገር ግን የምሻውን ያከናውናል፤ የተላክበትንም ዓላማ ይፈጽማል" (ኢሳ 55፥11)። ኢየሱስም እንደዚህ ብሏል፣ "ከሥጋ የተወለደ ሥጋ ነው፤ ከመንፈስ የተወለደም መንፈስ ነው" (ዮሐ 3፥6)። መጽሐፍ ቅዱስ በተጨማሪ፣ እንደዚህ ይላል፣ "ዳግመኛ የተወለዳችሁት ከሚጠፋ ዘር ላይሆን ሕያው በሆነና ጸንቶ በሚኖር፣ በእግዚአብሔር ቃል አማካይነት ከማይጠፋ ዘር ነው" (ጴጥ 1፥23)። በመንፈስ ዳግም ስንወለድ፣ መንፈስ ቅዱስ በእግዚአብሔር ቤተሰብ አባልነታችን በማቀየት ሕይወታችንን ይለውጣል። እርሱ "የእርሱ ለመሆናችን ማኅተሙን ያተመብን ደግሞም ወደፊት ለምናገኘው ነገር የመንፈሱን ዋስትና በልባችን ያኖረ እርሱ ነው" (2ቆሮ 1፥22)።

ሶስተኛ፣ መንፈስ ቅዱስ እግዚአብሔር ነው። ኢየሱስ ፍጹም እምላክ እንደሆነ ሁሉ፣ መንፈስ ቅዱስም ፍጹም አምላክ ነው። እግዚአብሔር ዘላለማዊ እንደሆነ ሁሉ መንፈስ ቅዱስም ዘላለማዊ እንደሆነ መጽሐፍ ቅዱስ ይነግረናል። እርሱ በሁሉ ሥፍራ የሚገኝ፣ ሁሉን የሚያውቅና ሁሉን የሚችል እንደሆነም መጽሐፍ

ቅዱስ ይነግረናል፤ እነዚህ የእግዚአብሔር ብቻ የሆኑ መለያ ባህርያት ናቸው። (ለይጣን እንደዚህ አይደለም፤ ኃያል ቢሆንም ሁሉን ቻይ ግን አይደለም።)

በተጨማሪም፤ መጽሐፍ ቅዱስ በማያሻማ መንገድ መንፈስ ቅዱስ እግዚአብሔር እንደሆነ ይውጃል "ጌታ መንፈስ ነው" (2ቆሮ 3፥17)። መጽሐፍ ቅዱስ መንፈስ ቅዱስን "የክርስቶስ መንፈስ" ወይም "የእግዚአብሔር መንፈስ" ብሎ የሚጠራበትም ጊዜ አለ፤ ይህም መለኮታዊ ባህርዩን ይገልጻል። መንፈስ ቅዱስ እግዚአብሔር ራሱ ነው። አግዚአብሔር ለብአ እንደሆነ ሁሉ መንፈስ ቅዱስም እንደዚሁ ለብአ ነው፤ እግዚአብሔር ሁሉን ቻይ እንደሆነ ሁሉ መንፈስ ቅዱስም እንደዚሁ ነው። የእግዚአብሔር ባህርይ የሆነ ሁሉ የመንፈስ ቅዱስም ነው፤ ምክንያቱም አርሱ እግዚአብሔር ነው።

ምስጢረ ስላሴ

እዚህ ላይ መንፈስ ቅዱስ እግዚአብሔር ሆኖ ከአግዚአብሔር እንዴት ሊለይ ይችላል? የሚል ጥያቄ ልታ ነሱ ትች ላሳችሁ። በተመሳሳይ ሁኔታ፤ ኢየሱስ ከስግደዊ አባቱ ከእግዚአብሔር ተለይቶ እንዴት ፍፁም አምላክ ሊሆን ይችላል? የሚል ጥያቄ ሊነሳ ይችላል።

ከመጽሐፍ ቅዱስ ጥልቅ እውነቶች አንዱ በሌላ በኩል ለማስተዋል እጅግ አስቸጋሪ ከሆኑት ውስጥ የነገረ መለኮት ሊቃውንት "የሥላሴ ምስጢር" የሚሉት ነው። እግዚአብሔር ወደእኛ የሚመጣው በሶስት የተለያዩ መንገዶች እንደ አብ፤ እንደ ወልድና እንደ መንፈስ ቅዱስ - ሆኖ እንደሆነ መጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ ደስተምረናል። ጳውሎስ ከመልዕክቶቹ አንዱን እንዲህ ሲል ይደመድማል፦ "የጌታ የኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ፤ የእግዚአብሔር ፍቅር፤ የመንፈስ ቅዱስም ኅብረት ከሁላችን ጋር ይሁን" (2ቆሮ 13፥14)። ሶስቱ አካላት አብ፤ ወልደ፤ መንፈስ ቅዱስ በአካል የተለያዩ ቢሆኑም እንደ አንድ ተዋህደዋል። ራሱን በሶስት አካላት የገለጠልንን አንድ አምላክ እንጂ፤ ሶስት አማልክት አናመልክም።

ይህንን እውነት በምናባችን እንዴት ልንቀርጸ እንችላለን? በመጀመሪያ ክርስትናን ወደ አየርላንድ ያመጣው ቅዱስ ፓትሪክ የተባለ ለው፤ ምስጢረ ስላሴን ለአዲስ ክርስቲያኖች ለማብራራት የሣር ዓይነት በምሳሌነት ተጠቅሟል፤ ቅጠሎቹ ሶስት ለየብቻ የሆኑ ቢሆኑም በአንድ ተክል ውስጥ ተዋሀደዋል። ሌሎች ደግሞ ምሥጢረ ሥላሴን ለማብራራት የፀሐይን ምሳሌ ይጠቀማሉ፤ ፀሐይ ቦታ የምትይዝ ነገር ሆና ብርሃንና ሙቀትን ትስጣለች - ሆኖም አንድ ናት። ውሃንም ምሳሌ የሚያደርጉ አሉ፤ ውሃ፤ ጠጠር ወይም ፈሳሽ ወይም ጋዝ ቢሆንም፤ ደው ውሃ ነው።

የአንድ ባልንጀራዬ ወጣት ልጅ አባቱን፤ እንዴት እግዚአብሔር አብ እግዚአብሔር፤ እንዲሁ ደግሞ ወልድ የሆነው ኢየሱስ እግዚአብሔር ሊባሉ ቻሉ ብሎ ጠየቀው። ይህ ማለት ኢየሱስ የራሱ አባት ነው ማለት አይደለም እንዴ? ብሎ ግራ መጋባቱን ገለጸ (ሕፃናት እንደዚህ ዓይነት የተወሳሰበ ሥነ መለኮታዊ ጥያቄዎችን ማንሳት ይችሉበታል)። በወቅቱ መኪና ውስጥ ተቀምጠው ስለነበር አባትዬው ድንገት በመጣለት ሀሳብ እንዲህ ሊል መለሰለት፤ "ይኸውልህ ልጄ የመኪናው ሞተር ውስጥ አንድ ባትሪ አለ፤ ይህን ባትሪ መብራት ለማብራት፤ ክላክ ለ ለመንፋት ወይም መኪናውን ለማንቀሳቀስ ልጠቀምበት እችላለሁ። ይህ እንዴት ሊሆን ቻለ? ለኔ ምስጢር ነው። ግን ይሆናል" ሊል መለሰለት።

እነዚህ ሥዕላዊ መግለጫዎች የሥላሴን እውነት እንድናስተውል ሊረዱን ይችላሉ፤ ሆኖም አንዳቸውም ቢሆኑ ሙሉ በሙሉ ሊያብራሩት አይችሉም። እንደ እውነቱ ከሆነ ይህ በምድር አስካለን ሙሉ በሙሉ ልንረዳው የማንችል ምስጢር ነው። ስለዚህ ጉዳይ ሳስብ የሚመጣልኝ ጳውሎስ እንዲህ ሊል የተናገረው ቃል ነው፤ "አሁን የምናየው በመስተዋት ውስጥ እንደሚታይ በድንግዝግዝ ነው፤ በዚያን ጊዜ ግን ፊት ለፊት እናያለን" (1 ቆሮ 13፥12)። ሙሉ በሙሉ አናስተውለውም ማለት ግን እውነትነቱን ይቀንለዋል ማለት አይደለም። ቅድስት ሥላሴ ስለሆነ

እግዚአብሔርን እንደ አብ፣ ወልድና መንፈስ ቅዱስ እናመልክዋለን።

ወደ ምድር የመጣው ስምንድነው?

ቀደም ሲል እንደተመለከትነው፣ ገና ከማሰዳው (ከፍጥረተ ዓለም ጀምሮ) የሠራው መንፈስ ቅዱስ በመላው የብሉይ ኪዳን ዘመንም ሥራው ቀጥሏል። በአዲስ ኪዳን ጅማሬ ላይም ሰገለጥ እናያለን። መልአኩ ለድንግል ማርያም እንዲህ ሲል ያበስራታል:- "መንፈስ ቅዱስ በአንቺ ላይ ይመጣል፣ የልዑልም ኃይል ይጸልልሻል፣ ስለዚህ የሚወለደው ቅዱስ ሕጻን፣ የእግዚአብሔር ልጅ ይባላል" (ሉቃ 1÷35)።

ይሁን እንጂ፣ ይህ እስከ ጴንጤቆስጤ ቀን ድረስ ባይፈፀምም፣ መንፈስ ቅዱስ በልዩ መንገድ በደቀመዛሙርቱ ላይ የወረደው ኢየሱስ ወደ ሰማይ ካረገ በኋላ ነበር (የሐዋ. ሥራ 2)። ኢየሱስ በአካል ከእነርሱ ጋር ሳሰ አልመጣም ነበር፣ ዳሩ ግን ተሰይታቸው ሲሄድ መንፈሱን እንደሚልክላቸው የተስፋ ቃል ሰጥታቸዋል። (መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚነግረን፣ ኢየሱስ በምድር ላይ አገልግሎቱ ወቅት፣ "ኢየሱስ ገና ስላልከበረ፣ መንፈስ አልተሰጠም ነበር" (ዮሐ 7÷39) የሚሰው ስዚህ ነው።) ኢየሱስ ከነርሱ ጋር መሆኑ እውን የነበረውን ያህል መንፈስ ቅዱስም ከነርሱ ጋር መሆኑ እውን ሆኗል።

ኢየሱስ የመንፈስቅዱስን ሥራ ለመግለፅ የተጠቀማቸውን ቃላት ልብ ልንል ይገባል። ስምሳሌ መንፈስ ስለ ጎጢአታችን እንደሚወቅሰን ነግሮናል:: "በሚመጣበትም ጊዜ ዓለምን ስለ ጎጢአት፣ ስለ ጽድቅና ስለ ፍርድ ይወቅሳል›› (ዮሐ 16÷8):: ወደ ክርስቶስ ከመምጣታችን በፊት መንፈስ ቅዱስ በቅድሚያ ስለ ጎጢአታችን በመውቀስ ዓይናችንን ለወንጌል እውነት ሊገልጥ ያስፈልጋል።

በተጨማሪም፣ መንፈስ ቅዱስ *አስተማሪያችንና መሪያችን* ይሆናል። "የእውነት መንፈስ በመጣ ጊዜ ወደ እውነት ሁሉ ይመራችኋል" (ዮሐ 16÷13)። መጽሐፍ ቅዱስ በጣም አስፈላጊ

የሆነው ለዚህ ነው፣ ቃሉን እንድናስተውል የሚረዳን መጀመሪያውኑ በሐዋርያት አድሮ ያስጻፋቸው መንፈስ ቅዱስ ራሱ ነው - ደሰ እርሱ ትርጉሙን ሙሉ በሙሉ ልናስተውል አንችልም። በተጨማሪም በየዕለቱ ለሕይወታችን በሚያስፈልገን ምሪት የእግዚአብሔርን ፈቃድ ይገልጥልናል።

እንደገናም ኢየሱስ ለሰዎች ስለክርስቶስ እንድንናገር ይረዳናል፣ "ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ በወረደ ጊዜ ኃይልን ትቀበላላችሁ፣ . . . እስከ ምድር ዳርቻ ድረስ ምስክሮቼ ትሆናላችሁ" (የሐዋ. ሥራ 1÷8)። ስክርስቶስ ስንመሰክር መንፈስ ቅዱስ ጥርጊያ በመክፈት፣ ትክክለኛ ቃላት በመስጠትና ልባችንን በድፍረት በመሙላት ከፊታችን ቀድሞ ይወጣል።

በሕይወቱ ከማልረሳቸው ሰዎች ውስጥ አንዱ ክሶብየት ጂዮርጂያ ወደ አሜሪካ ስደተኛ ሆኖ የመጣ አስተማሪ ነው። ሶስት የዶክትሬት ዲግሪዎች ቢኖሩትም፣ በታወቀ ዩኒቨርስቲ ውስጥ ትልቅ ቦታ የነበረው ምሑር ቢሆንም ድብርት የሚጫነውና ደስታ የሸሸው ሰው ነበር። አንድ ቀን፣ ጫማውን እያስጠረገ ሳለ፣ ጫማ ጠራጊውን ሁልጊዜ ፊቱ በደስታ ብሩህ የሆነበትን ምክንያት ጠየቀው። ጫማ ጠራጊው በትህትና ግን በልበሙሉነት ደስታው የመነጨው ኢየሱስ እንደሚወደው በማወቁ፣ በኢየሱስ ምክንያት እንደሆነ ገለጸለት። ፕሮፌሰሩ ጫማ ጠራጊው የተናገረውን ቃል ሊያጣጥለው ቢሞክርም፣ በቀላሉ ክጭንቅላቱ ሊያስወጣው አልቻለም። በዚህ ሰው ቀላል ምስክርነት ሳቢያ፣ እግዚአብሔርን መፈለግ ጀመረ - ይህም ፍለጋ ሕይወቱን ለኢየሱስ ክርስቶስ እንዲሰጥ አደረገው። በኋላ ላይ ያስተምርበት የነበረውን ትልቅ ዩኒቨርስቲ ተሰናብቶ፣ እኔና ባለቤቱ ሩት በተማርንበት ክርስቲያናዊ ኮሌጅ ማስተማር ጀመረ፣ በአስተማሪነቱም በሕይወቱ ላይ ትልቅ አሻራ ከተዉ ሰዎች አንዱ ነው። ይህ ሰውዮ የተከሰተው መንፈስ ቅዱስ ያን ያልተማረ ጫማ ጠራጊ ሰው ለዚህ ልሒቅ አእምሮ ላለው ሰው እንዲመስክር በማድረጉ ነው፣ ልሂቁ ሰው የተራቆተ ልብ (በርግጥ መንፈስ ቅዱስ አስተድሞ ያዘጋጀው ልብ) ስለነበረውና

ሰመስካሪውም የመመስከር ድፍረትን ስለሰጠው ነበር። መንፈስ ቅዱስ በርግጥ እንድንመስክር ይረዳናል።

ክርስቶስን በመምሰል ማደግ

መንፈስ ቅዱስ ሰእኛ የተሰጠበትን ሌሎች በርካታ ምክንያቶችን መጽሐፍ ቅዱስ በዝርዝር ያቀርብልናል። ከነዚህ እንዳንዶቹን በኋላ ዘርዘር አድርገን እንመለከታችዋለን። *መንፈሰ ቅዱስ የተሰጠን ክርስቶስን በመምሰል ማደግ እንድንችል ለመርዳት ነው።* በራሳችን ጥረት ክርስቶስን መምሰል ስለማንችል የአግዚአብሔር እርዳታ ያሻናል። እርሱም መንፈስ ቅዱስን በመሰጠት እርዳታን ሰግሶናል።

የክርስትና ሕይወትን በገዛ ራሳችሁ ጥረት ለመኖር እየሞከራችሁ ነው ወይስ በየቀኑ የሚያስፈልጋችሁን እርዳታ ይስጣችሁ ዘንድ ወደ እርሱ እየተመለከታችሁ ነው? እዚህ ላይ ቆም ብላችሁ አግዚአብሔር በመንፈስ ቅዱስ በውስጣችሁ ሊያድር ስሰመጣ አመስግኑት። እርሱ ከእናንተ ጋር ስላለ፣ ከቶም ቢሆን ብቻችሁን አይደላችሁም።

ወሥዒቱ ትምህርት

የዕለት ለንቅ

ነገር ግን በጊታችንና በክደኛችን በሚየሱስ ክርስቶስ ጸጋና ዕውቀት ስደጉ

(2ጴጥ 3÷18)

ክርስቲያን መሆን የቅጽበት ውሳኔ ሲሆን በክርስትና መቆየት ግን የሕይወት ዘመን ሥራ ነው።

ከበርካታ ዓመታት በፊት፣ (ታሪኩ እንዲህ እደስ ይቀጥላል) መሐንዲሶች በገደልማ የወንዝ ሸለቆ ላይ ተንጠልጣይ ድልድይ ሰመገንባት ይወስናሉ። እዚህ ላይ ትልቁ ችግራቸው የነበረው በጣም ከባድ የሆኑትን የብረት ኬብሎች ከአንድ የሸለቆ ጫፍ ወደ ሌላኛው ጫፍ መዘርጋት ነበር። በወቅቱ ሔሊኮፕተሮች አልተሠሩም ነበርና ኬብሎቹን በጀልባ ሆነው አንዳይዘረጉ ደግሞ በዐለቶች ላይ የሚጋልበው ፈረስኛ ውሃ አደገኛ ነበርና አሳሰቻላቸውም።

ጥያቄአቸው የመፍትሔ ያለሀ? ሆነ። ስችግሩ መላ አየፈለገ ሳለ፣ አንድ ቀን መሐንዲሶቹ በገደልማ ወንዝ ሸለቆ ላይ ወላንዶ (በገመድ ታስሮ በአየር የሚለቀቅ መጫወቻ) ስማብረር ሃሳብ መጣላቸው። ወላንዶዋ በወዲያኛው ጫፍ ላይ ስትደርስ፣ ሆን ብለው መሬት ላይ አሳረፉአትና ሁለቱ የወንዝ ዳርቻዎች በቀጭን የወላንዶ ገመድ ተገናኙ። በመቀጠልም በአንደኛው የወላንዶ ገመድ ጫፍ ላይ ወፈር ያለ ገመድ በማሰር በጥንቃቄ ወደ ሌላኛው ጫፍ አጓጓዙት። ይህንን በርካታ ጊዜ በመደጋገም ቀጭን ገመድ ከዚያም ወፍራም ገመድ በመደራረብ ከባድ የብረት ኬብሎችን በገደልማ ወንዝ ሸለቆ ላይ በማድረግ ድልድዩን ገነቡ።

የወላንዶ ገመድ ብቻ አሻግሪው ቢቀሩ ኖሮ ምን ይከሰት ነበር? ወይም ደግሞ የወላንዶዋን ስኬታማ በረራ ብቻ ምክንያት ስማድረግ ድላቸውን ለማክበር የወር አረፍት ቢወስዱ ኖሮስ? ድልድዩ ላይሰራ ይቀር ነበር፤ ይህ ብቻ ላይሆን የወላንዶዋ ገመድ በንፋስና በፀሐይ ተጎድቶ ይበጠስ ነበር።

ወደ ብስለት ማደግ

መንፈሳዊ ዕድገት ከዚህ ድልድይ ግንባታ ጋር ተመሳሳይ ነው። በመጀመሪያ እምነታችን ትንሽና በቀላሉ የሚጎዳ ስለሚሆን፣ በብርቱ ማዕበሎችና ፈተናዎች የሚናወጥ ሊሆን ይችላል። ይህ ግን የእግዚአብሔር ፈቃድ አይደለም! ሁለቱ የወንዙ ዳርቻዎች ቀስ በቀስ እንደተጋጠሙ ሁሉ፤ እግዚአብሔርም እምነታችን ዕለት ዕለት እንዲጠነክር ይሻል። የእግዚአብሔር ሀሳብ መለወጣችን ብቻ ሳይሆን በመንፈሳዊ ብስለት ማደጋችንም ነው።

አዲስ ክርስቲያን በእምነቱ (በእምነታ) ከቶ ዕድገት ባይኖርና ሁልጊዜ መንፈሳዊ "ሕጻን" ሆኖ (ሆና) ማየት የሚያሳዝን ነገር ነው። እንደዚህ ዓይነት ሰዎች ልክ እንደ ወላንዶዋ ገመድ፣ የመጀመሪያውን ወላኝ እርምጃ ወስደው ከዚያ በኋላ ግን ባሉበት ቀርተዋል። ኢየሱስ የእግዚአብሔርን ቃል በልባችን ከተቀበልን በኋላ፣ በጭንጫና በእሾሃማ መሬት ላይ እንደተዘራ ዘር በዚህ ዓለም ሀሳብ ጠውልጎና ታንቆ እንዳይቀር አስጠንቅቆናል (ሉቃ 8፥1-15)። ይልቁንም ‹‹ቃሉን ቅንና በጎ በሆነ ልብ ሰምተው የሚጠብቁ፣ ታግሰውም በመጽናት ፍሬ የሚያፈሩ›› (ሉቃ 8፥15) እንድንሆን ነግሮናል።

ሰብል በአንድ ጀንበር በቅሎ አይደርስም። ለማሸት ጊዜ ያስፈልገዋል፤ ገበሬውም ብርቱ ትጋት ይጠበቅበታል። በተወለድክበት ዕለት እናቱ ለበርካታ ሰዓታት ያህል ከእርሻ መሬታችን ላይ የባቄላ እህል እየለቀመች ለእሽጋት (እንዲታሸግ) ታዘጋጀው ነበር። ሥራውን ማከናወን እንዳለባት በማመን፣ ለራሷ ፋታ መስጠት አልፈለገችም። ገበሬዎች እርሻቸውን ችላ ቢሉ፣ ወይም ማሳቸውን ማጨድ ቢተው፣ ዓለማችን ምን ትመስል ነበር? ታዲያ በመንፈስ ደካማና ልፍስፍስ ስንሆን፣ ነፍሳችን ይሸው

ዓይነት ዕጣ እንዲገጥማትና እንድትጠወልግ እየፈቀድን ነው። እንግዲያውስ ምን ይበጀናል?

ግባችን ላይ ማነጣጠር

እንደ "ደቀመዛሙርነት" እና "መንፈሳዊ ብስለት" ያሉ ቃላት ለጆሮአችን የሆነ ክብደት አላቸው፤ ግን በትክክል ምን ማለት እንደሆኑ ለአፍታ ቆም ብለን እስበን እናውቃለን?

ሁሉም ቀደም ብለን በተመለከትነው አንኳር እውነት ላይ ያተኩራሉ፤ *እግዚአብሔር ለእኛ ያለው ዓላማ ክርስቶስን በመምሰል እንድናድግ ነው*። ጳውሎስ ከተሰወጡ ብዙም ላልቆዩት የገላትያ ክርስቲያኖች እንዲህ ሲል የልቡን ናፍቆት ይገልጥላቸዋል፦ "የምወዳችሁ ልጆቼ ሆይ፤ ክርስቶስ በውስጣችሁ እስኪቀረጽ ድረስ ስለ እናንተ እንደገና ምጥ ይዞኛል" (ገላ 4፥19)። ሰሌሎች ደግሞ እንዲህ ይላቸዋል፦ "እኛም ሁላችን ባልተሸፈነ ፊት የጌታን ክብር እንደ መስተዋት እያብለጨለጭን መንፈስ ከሚሆን ጌታ እንደሚደረግ ያን መልክ እንድንመስል ከክብር ወደ ክብር እንለወጣለን" (2 ቆሮ 3፥18)። ልጆች የወላጆቻቸውን መልክ ይዘው እንደሚወጡ ሁሉ እኛም የክርስቶስ ቤተሰብ አባላት እንደመሆናችን የእርሱን መልክ እንድንመስል ይጠበቅብናል።

በዚህ ምድር እስካለን ድረስ፣ ሙሉ በሙሉ እርሱን ወደመምሰል ልንደርስ አንችልም። በመንግስተ ሰማያት ግን በምልአት እርሱን እንመስለዋለን "እርሱ በሚገለጥበት ጊዜ እናየዋለንና፣ እርሱን እንደምንመስል እናውቃለን" (1ዮሐ 3፥2)። ይሁንና ያ ቀን እስኪደርስ ድረስ ግልጽ የሆነ ትእዛዝ ተሰጥቶናል፤ ይኸውም "በጠማማና በክፉ ትውልድ መካከል ንውሐንና ያለነቀፋ፣ ነውርም የሌለባቸው የእግዚአብሔር ልጆች ሆናችሁ፤ እንደከዋክብት ታበሩ ዘንድ ነው" ሲል ጳውሎስ ያስታውሰናል (ፊሊጵ 2፥15)። ይህ በሕይወታችሁ እየሆነ ነው?

ክርስቶስን መምሰል

በወጣትነቴ፣ በአንድ ስፍራ ከታወቀ ክርስቲያናዊ መሪ ጋር ተገናኝቼ ነበር። ይህ ሰው ለእውነት ያለው ቅንአትና ለእምነት ተቃዋሚዎች መልስ ለመስጠት የነበረው ትጋት የሚያስደንቅ ነበር። ይሁንና ትንሽ ቆይቼ ይህ ሰው አንድ የሚጎድለው ነገር እንዳለ ተገነዘብኩ፣ ይህም ሌሎችን መውደድ ለእርሱ ቀላል አልነበረም (በተለይም ከእርሱ ጋር የማይስማሙትን ሰዎች)። ከሰውዬው ሁኔታ የተነሣ ኢየሱስ በእንዲህ ዓይነት ነበር የሚታወቀው? ብዬ ራሴን እንድጠይቅ አደረገኝ። የሰውዬውን ጉድለት ካስተዋልኩ በኋላ በእግዚአብሔር እርዳታ ፍቅር አልባ ቅንአትን አስወግጄ፣ በክርስቶስ ፍቅር ለመሞላት እንድጨክን እደረገኝ።

ክርስቶስን መምሰል ማለት ምን ማለት ነው? ቀደም ሲል እንደተመለከትነው፣ ክርስቶስ በሁሉም የሕይወታችን ከልል ጌታ እንዲሆን መፍቀድ ማለት ነው። ለዚህ አብነት የሚሆኑ (ብዙ ሌሎች መዘርዘር ብችልም) ሦስት ምላሌዎችን ልጥቀስ።

አንደኛ፣ ክርስቶስ በባህርያችን ላይ እንዲገዛ መፍቀድ ማለት ነው። አንድ ሰው በለፈሩ ከሚያውቀው ከአንድ ነጋዴ ጋር አንዳችም ግንኙነት ሊኖረው እንደሚይፈልግ ገለጸልኝ። ምክንያቱንም ስገልጽልኝ፣ "ነጋዴው ክርስቲያን ነኝ ቢልም፣ ሁልጊዜ በአቋራጭ መንገድ ማሳበር የሚቀናው፣ ቃል ገብቶ ቃሉን የሚያጥፍና ባገኘትም አጋጣሚ ሁሉ የራሱን ጥቅም የሚያስቀድም ሰው ስለሆነ ነው" አለኝ። በሚያሳዝን ሁኔታ፣ ባህርዩ ክርስቶስን የሚያንፀባርቅ አልነበረም።

ሁለተኛ፣ ክርስቶስን መምሰል ማለት ክርስቶስ በምግባራችን ላይ እንዲገዛ መፍቀድ ማለት ነው። አንድ የኮሌጅ ተማሪ በቅርቡ ክርስትና እምብዛም እንደማይማርከው ጻፈልኝ። እንዲህም ሲል ምክንያቱን ገለጸ፦ "ክርስቲያን መሆን ከማልፈልግባቸው ምክንያቶች አንዱ፣ እውነተኛ ክርስቲያን እስካሁን ስላልገጠመኝ ነው"። ይህ ምንኛ ብርቱ ነቀፌታ ነው! እኔም በምላሹ በጸፀኩለት

ደብዳቤ፣ ክርስቲያኖችን ብቻ ሳይሆን ክርስቶስን እንዲመስከት (ክርስቶስ ብቻ ፍጹም ስለሆነና እርሱ ብቻ ሊያድን ስለሚችል) አበክሬ ብገልጽለትም፣ ክርስቲያኖች የስጡት ስዕል ከክርስቶስ ባሕርይ የራቀ መሆኑ ግን ሳያስከፋኝ አልቀረም። ሕይወታችን ክርስቶስን የማይመስክር ከሆነ፣ ለምች ለስብከታችን ጆሮ እንዲለጡ መጠበቅ የዋህነት አይሆንም? ጳውሎስ ጢሞቴዎስን "ከዚህ ሁሉ (ከክፉው) ሽሽ፣ ጽድቅን፣ እውነተኛ መንፈሳዊ ሕይወትን፣ እምነትን፣ ፍቅርን፣ ትዕግስትንና ገርነትን ተከታተል" (1ጢሞ 6፥11) ሲል ይመክረዋል።

ሶስተኛ፣ ክርስቶስን በመምሰል ማደግ ማለት የልባችን ዝንባሌዎች ላይ ሁሉ እንዲገዛ እንፈቅዳለን ማለት ነው። የልባችን ዝንባሌና ሁኔታ ውጫዊ ምግባራችንን ይወስናል - የሚያሳዝነው ግን ምናልባት ክርስቶስን ማንፀባረቅ ሳይችሉ ሲቀሩ ነው። ክርስቲያኖች አሉታዊና አቃቂር አውጪ መሆን የሚቀናቸው ለምን ይሆን? ሌሎቹስ ነጭናጫ፣ ዕቡይና ትዕግስት አልባ ለምን ይሆናሉ? አንዳንዶቹስ ልባቸው የታወከ፣ የሚጨነቁ ወይም ደግሞ ዳተኞች፣ ራሳቸውን የማይገዙ፣ እምነት የማይጣልባቸውና ኃላፊነት የጎደላቸው የሆኑት ለምን ይሆን? ሌሎቹስ በሰዎች ላይ የሚስለጥኑና የማይመቹ የሚሆኑት ምን ነክታቸው ይሆን? እግዚአብሔር የልባችን ሁኔታ ክርስቶስን የሚያንጸባርቅ እንዲሆን ጥሪ እያቀረበልን ነው።

የክርስቶስ ትህትና

በትውስታዬ ተቀርጸው ከሚኖሩ ገጠመኞች ውስጥ አንዱ ናጋላንድ የሚባል በህንድ አገር ራቅ ብሎ የሚገኝ ተራራማ አካባቢ መጎብኘቴ ነው። ይህ ቦታ በህንድ ውስጥ ክርስቲያኖች በብዛት ከሚገኙባቸው ስፍራዎች አንዱ ቢሆን፣ የተገኘሁት የወንጌል ለባኪያን ወደዚያ ስፍራ የመጡበት መቶኛ ዓመት በሚከበርበት ጊዜ ነበር። በዐሥር ሺህዎች የሚቆጠሩ ሰዎች ለክብረ በዓሉ መጥተዋል- አንዳንዶቹ እዚህ ለመምጣት ለአራት ቀን በጫካ መንገዶች ተጉዘዋል። ሰዎቹ እንደነገሩን፣ በመቶ ሺህ የሚቆጠሩ

ለምች በየማሰዳው ሰመጽሐፍ፡ ቅዱስ ጥናት፣ በየምሽቱ ደግሞ ለወንጌል ስብክት ይሰበስቡ ነበር።

ሰማደሪያ ወደተዘጋጀልን የመንግሥት ቤት ስንደርስ፣ አንድ ሰው ጓዛችንን ከመኪና ካወረደ በኋላ፣ ጫማችን ላይ የነበረው ጭቃ ይጠረግላችኋል አሰን። የሰም ራሳችን እንጠርገዋሰን ብንለውም እሺ ሊሰኝ አልቻሰም። ይህ ስው በማግስቱ የሚካሔደውን የማለዳ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት የሚመራ ሰው አንደሆነ የተገነዘብኩት ኋላ ላይ ነበር። የዚህ ስው ትህትናና ሌሎችን ለማገልገል ያሳየው ፈቃደኝነት፣ በእውነት ክርስቶስን የሚገልጥ ነበር። የዚህ ሰው አርአያ ከቶም ተዘንግቶን አያውቅም።

መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፡- "የመንፈስ ፍሬ ግን ፍቅር፣ ደስታ፣ ሰላም፣ ትዕግስት፣ ቸርነት፣ በጎነት፣ ታማኝነት፣ ገርነት፣ ራስን መግዛት ነው፡ ፡" (ገላ 5÷22-23)። ይህ ዝርዝር ዘጠኝ ባህርያትን ያቀፈ ሲሆን፣ የክርስቶስ የሆነ ሰው ሕይወቱ በነዚህ መሰያዎች ሊያጌጥ ይገባል- ምክንያቱም የክርስቶስ ሕይወት መሰያ ጌጦች ስለሆኑ ነው። ክርስቶስን መምሰል ማለት ምን እንደሆነ ለማወቅ ትፈልጋላችሁ? እግዚአብሔር እነኚህን ዘጠኝ ባህርያት ተገንዝባችሁ፣ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል የሕይወታችሁ አካል ማድረግ እንድትችሉ እግዚአብሔር እንዲረዳችሁ ጠይቁት።

ይሁን እንጂ ይህ ማለት አግዚአብሔር ማንነታችንን ሊሰርዝ ያስባል ማለት አይደለም - በርግጥ ሻካራና ጎርባጣ ጎናችንን ሊያስተካክል ይፈልጋል! ሁላችንም የተሰያየን ነን፣ ምክንያቱም እግዚአብሔር አንደዚያ አደረገን። የጠርሴሱ ላውል ቁርጠኛ፣ የጨከነ፣ ወሰም ዘሰም የማያውቅና የክርስትና እምነትን ከምድረ ገፅ ማጥፋትን ሥራዬ ብሎ በአልህ የያዘ ሰው ነበር። ይሁንና እግዚአብሔር ጣልቃ ገብቶ ሰክርስቶስ የነበረውን ጥላቻ ወደፍቅር ሰወጠሰት። መሠረታዊ ማንነቱ አልተለወጠም፣ ይልቅስ እግዚአብሔር የብርታቱን አቅጣጫ በማስሰወጥ (እንደሐዋርያ ጳውሎስ ሆኖ) የወንጌልን ብርሃን ይዞ የሚገሰግስ ሰው አደረገው። በአንጻሩ የጳውሎስ ረዳት ወጣት ጢሞቴዎስ የተሰየ ስብዕና የነበረው ለው ነበር - ዓይናፋር፣ አዛኝ፣ ከሰው የማይደባለቅ ሰው

ነበር። ሆኖም አግዚአብሔር ዓይናፋርነቱን አስወግዶ ሌሎችን የሚደርስና የሚያገለግል ሰው አደረገው፣ አዛኝ ባህርዩንም ውጤታማና ሰመን፣ጋው የሚራራ፣ መጋቢ እንዲሆን አድርጎ ሰወጠው።

የመሰወጥ ጉዳና

ክርስቶስን በመምሰል ማደግ አንድንችል ከእኛ ምን ይጠበቃል? ቀደም ሲል እንደተመለከትነው፣ የራሳችን ጥንካሬ የትም አደደርሰንም፣ *ሊለውጠን የሚችለው የመንፈስ ቅዱስ ኃይል ብቻ ነው።*

መጽሐፍ ቅዱስ፣ "በመንፈስ ተሞሉ እንጂ በወይን ጠጅ አትስከሩ" (ኤፌ 5÷18) ብሎ የሚያዘን ሰዚህ ነው። አንድ ሰው ሲስክር፣ በአልኮል ተዕፅኖ ስር ነው እንላለን (በዜና እንደምንሰማው፣ ይህ ብዙ ጊዜ ሰኑሮ ጠንቅ ነው)። በሌላ አባባል፣ አልኮል ሰውዬውን እየተቆጣጠረው ነው። በተመሳሳይ ሁኔታ፣ በመንፈስ የተሞላ ሰው በመንፈስ ቅዱስ ቁጥጥር ወይም ተዕፅኖ ሥር ነው። ይህ በሕይወታችን እውን የሚሆነው እንዴት ነው? መንፈስ ቅዱስ ሕይወታችንን ይሰውጥ ዘንድ በውስጣችን መሥራት የሚጀምረው እንዴት ነው?

አንደኛ፣ ንስሐ መግባት ይጠበቅብናል። ይህ ማለት ኃጢአት አስካሁን እየገዛው ያለና የክርስቶስን ጌትነት ያልሾምንበትን የሕይወታችንን ክፍል እግዚአብሔር እንዲያመለክተን መጠየቅ ማለት ነው - ከዚያም በጨከነ ልብ ልባችንን ከነዚህ ኃጢአቶች እንመልሳለን ማለት ነው።

በሰሜን ካሮላይና በሚገኘው ቤታችን የምንጠቀምበት ውሃ የሚመጣው ከፍ ካለ ተራራ ከሚፈልቅ ምንጭ ነው። በዘህ ቤታችን መኖር ስንጀምር የአካባቢው ነባር ነዋሪዎች ይህ ምንጭ በድርቅ ወራት ሳይቀር ሳያቋርጥ እንደሚፈስ ነገሩን - በርግጥም ልክ ነበሩ። ይሁንና በአንድ ወቅት ሰዓመት ያህል ያልተሰመደ ቀዝቃዛ ክረምት ስለነበረ፣ አንድ ቀን ውሃው ተቋረጠ። ክምንጩ በሚያስተላልፈው የውሃ ቧንቧ ላይ ውሃው በረዶ ሠራ፣ በቱር

የተጋገረውን መሬት ቆፍረን መበየጃ በመጠቀም በረዶውን ማቅለጥ ነበረብን። ያኔ ውሃው እንደገና መፍሰስ ጀመረ።

ይህ ምንጭ የመንፈስ ቅዱስን ሥራ ያስታውሰኛል። ምንም ዓይነት ሁኔታ ቢሆን፣ የመንፈስ ቅዱስ መውረድ ልክ እንደ ምንጩ ለኛ ሁልጊዜ ዝግጁ ነው። ሆኖም ኃጢአት እንደተጋገረው በረዶ ቧንቧችንን ዘግቷል። የተቃዋሚው ዓለም መንፈሳዊ ቅዝቃዜ ነፍሳችንን እንዲያቀዘቅዝ ስንፈቅድ፣ የመንፈስ ቅዱስን ሕይወት ስጪ ውሃ ያቋርጣል።

ማነቆውን በማስወገድ ፍሰቱ እንዲቀጥል ማድረግ የሚቻልበት ብቸኛ መንገድ ንስሓ ነው። መንፈሳዊ ሕይወታችን ድርቀት የነገሠበትና ምድረበዳ (የመከነ) ከሆነ፣ የመዝሙረኛውን ጸሎት በመጸለይ ጀምሩ፣ "እግዚአብሔር ሆይ፣ መርምረኝ፤ ልቤንም ዕወቅ . . . የክፋት መንገድ በውስጤ ቢኖር እይ" (መዝ 139፥23-24)። ኃጢአት የስስጠነበት የሕይወታችሁ ክፍል እንዳስ እንዲያሳያችሁ እግዚአብሔርን ጠይቁት፤ ከዚያም ንስሓ ግቡ።

በየዕለቱ ራስን ለእግዚአብሔር ማስገዛት

ሁለተኛ፣ ክርስቶስን በመምሰል ለማደግ ራስን ለእግዚአብሔር ማስገዛት ይጠበቅብናል። በየዕለቱ በልባችን ውስጥ በኛ ፈቃድና በእግዚአብሔር ፈቃድ መካከል የከረረ ትንንቅ ይካሔዳል። እግዚአብሔር አሁን በመንፈስ ቅዱስ በልባችን ይኖራል፤ ሆኖም አሮጌ ባህርያችን አሁንም ሕያው ስለሆነ፣ አሁንም የበላይነት ለማግኘትና እኛን በቁጥጥር ሥር ለማዋል ይታገላል። በሕይወታችን ክርስቶስን በማንፀባረቅ ፈንታ የማያምነውን ዓለም ባህርይ እናንጸባርቃለን።

ኢየሱስ ለደቀመዛሙርቱ እንዲህ ያላቸው ለዚህ ነው፣ "በኋላዬ ሊመጣ የሚፈልግ ማንም ቢኖር ራሱን ይካድ፤ መስቀሉንም በየዕለቱ ተሸክሞ ይከተለኝ" (ሉቃ 9፥23)። ይህ ቃል ደቀመዛሙርቱን እንደሚያስነግጣቸው ዕሙን ነው። በዚያ ዘመን መስቀል የሐፍረትና የሞት ትእምርት (ምልክት) ስለነበረ መስቀል የሚሸከም ሰው ሞት የተፈረደበት ሰው ብቻ ነበር (ኢየሱስ

በመጨረሻ ላይ እንደተሸከመው)። በርግጥም ኢየሱስ ያለው ይህንኑ ነበር። እሮጌ ባህርያችን - ራስ ወዳድነታችን፣ ክፉ መሻታችን፣ አሮጌ ዝንባሌዎቻችንና አኗኗራችን በአንድነት መሞት አለባቸው። መጽሐፍ ቅዱስ እንደዚህ ይላል፣ "ስለዚህ ምድራዊ ምኞቶቻችሁን ግደሉ" (ቆላ 3፥5)። ጳውሎስ ከግል ተሞክሮው ይህ ምን ማለት እንደሆነ ያውቅ ነበር፦ "ከክርስቶስ ጋር ተሰቅያለሁ፤ ከእንግዲህ እኔ አልኖርም፤ ነገር ግን ክርስቶስ በውስጤ ይኖራል" (ገላ 2፥20)።

ራስን ለክርስቶስ ማስገዛት ማለት እያንዳንዱን የሕይወታችንን ክፍል ከእርሱ ሥልጣን በታች ማኖር ማለት ነው፣ እንደዚሁም እንደፈቃዱ እንዲሰውጠን እርሱን መጠየቅ ማለት ነው። ከተሳሳተ መንገድ ተመልሰን፣ መልካምና ንጹሕ በሆነው እንዲሞላን እርሱን መጠየቅ ማለት ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ይህን ልብስ ከመስወጥ ጋር ያመሳስለዋል- አሮጌና እድፋም ልብሱን እውልቆ አዲስና ንጹህ ልብስ እንደ መልበስ፦ "ፊተኛ ኑሮአችሁን እያሰባችሁ እንደማያታልል ምኞት የሚያጠፋውን አሮጌውን ሰው አስወግዱ፣ . . . ለእውነትም በሚሆኑ ጽድቅና ቅድስና እንደ እግዚአብሔር ምሳሌ የተፈጠረውን አዲሱን ሰው ልበሱ" (ኤፌ 4፥22፤ 24)።

በሕይወታችሁ ክርስቶስ የተተወበት የት ጋ ነው? በባህርያችሁ? በዝንባሌያችሁ? በድርጊታችሁ ነው? ወይስ በሌላ አንደ ጊዜያችሁ ወይም ገንዘባችሁ ወይም ከሰዎች ጋር ባላችሁ ግንኙነት ነው? በሥልጣኑ ሥር ያልተገዛ አለ? ሰራላችሁም ለእግዚአብሔርም እውነተኞች ሁኑ። አስታውሱ፤ እግዚአብሔርን ማታለል አትችሉም። መዝሙረኛው እንዲህ ሲል ጸልዮአል፦ "ከተሰወረ በደል እንፃኝ" (መዝ 19፥12)። ይህን ጸሎት የናንተ እድርጉት።

ከዚያም የሕይወታችሁን ሁለንተና ለክርስቶስ ሥልጣን አስገዙ። መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፦ "እንግዲህ ለእግዚአብሔር ተገዙ፣ ዲያብሎስን ተቃወሙት፣ ከእናንተም ይሸሻል። ወደ እግዚአብሔር ቅረቡ፣ እርሱም ወደ እናንተ ይቀርባል" (ያዕ 4፥7-8)።

መታመንና መታዘዝ

በመጨረሻ፣ የመንፈስ ቅዱስ ሕይወት ለዋጭ ኃይል በውስጣችሁ ሊሰቀቅ የሚችለው በንሰሓና በመገዛት ብቻ ሳይሆን፣ በመታዘዝና በመታመን ነው።

አንድ ወታደር ለአዛዡ መኮንን ራሱን በሚያስገዛበት ጊዜ አዛዡ የሚያዝዘውን ለማድረግ ፈቃደኛ ይሆናል። ታማሚ ሰው ወደ ሐኪም ለመታከም ሲሄድ ሐኪሙ እንደሚለው ያደርጋል። የእግር ኳስ ተጫዋች ለአሰልጣኙ እመራር ራሱን ከሰጠ፣ አሰልጣኙ ያዘዘውን ያደርጋል። እናም እኛ ራሳችንን ለክርስቶስ ንጉሥና ለጌቶች ጌታ በምንሰጥበት ጊዜ እርሱ እንድናደርግ የሚነግረንን እናደርጋለን፣ ምክንያቱም የርሱ መንገድ ትክክል እንደሆነ እናውቃለን።

ቀደም ሲል እንደተመለከትነው፣ እግዚአብሔር ከሁሉ በፊት ፈቃዱን የሚገልጥልን በቃሉ፣ በመጽሐፍ ቅዱስ፣ አማካይነት ነው። የእግዚአብሔርን ቃል ብናውቅና ብንታዘዘው ከስንት ችግሮች እናመልጥ ነበር? መጽሐፍ ቅዱስ ለሚገጥመን ሁኔታ ሁሉ መመሪያ ባይሰጠንም እኛ ከምንገምተው በላይ በበርካታ ጉዳዮች ላይ ምሪትን ይሰጠናል። በተጨማሪም ሕይወታችንን ልንመራ የምንችልባቸውን መርሆች ያመላክተናል። የእግዚአብሔር ቃል የተሰጠን እንድንተነትነው ወይም እንድንሚገትበት ሳይሆን እንድንተገብረው ነው። መዝሙረኛው እንዲህ ይላል። "ቃልህን እጠብቅ ዘንድ፣ እግሬን ከክፉ መንገድ ሁሉ ከለከልኩ" (መዝ 119፥101)

እግዚአብሔር በመንፈሱ ደግሞ ይመራናል፣ በተለይም አጣብቂኝ የሆነ ሁኔታ ውስጥ ስንገባ፣ እርሱ በዚህ መንገድ ሊመራን፣ ምንም ያህል ዋጋ ቢያስከፍለን፣ ልንታዘዘው ይገባል። የዚህ ዓይነት ሁኔታ በተደጋጋሚ ገጥሞኛል። አንዳንድ ጊዜ ያለ ብዙ ትግል እታዘዛለሁ፣ በሌሎች ጊዜያት ግን ትክክለኛው ውሳኔ የቱ እንደሆነ ማወቁ ራሱ አስቸጋሪ ይሆንብኛል። አንዳንድ ጊዜ እግዚአብሔር አገልግሎታችን በአንዳንድ መንገዶች ለምሳሌ

በፊልሞችና በቴሌቭዥን በመጠቀም ለማስፋት ስናስብ ወይም ደግሞ ከሚደርሱኝ የወንጌል ስብከት ጥሪዎች የትኞቹን መቀበል እንዳለብኝ ለመወሰን ተስኖኝ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለማወቅ ከአጋሮቼ ጋር ለመወሰን የሞከርንባቸውን ጊዜያት አስታውሳለሁ። በአእምሮ ማገናዘብ ብቻውን በቂ አይደለም፤ ትክክለኛውን ውሳኔ ለማወቅ የቻልነው ስ ንጸልይ፣ ቃሉን ስናጠና ና የሌሎች በሳል የእግዚአብሔር ሰዎችን ምክር ስንጠይቅ ብቻ ነው፤ ውሳኔው ትክክለኛ እንደሆነ እግዚአብሔር በውስጣችን ያጸናልናል። መንፈስ ቅዱስ እንዲህ፤ "መንገዱ ይህ ነው፤ በእርሱ ሑድ" (ኢሳ 30፥21) እያለ ያረጋግጥልናል።

በየዕለቱ እንዳዲስ መጀመር

ንስሓ . . . መገዛት . . . መታዘዝ . . . እነዚህ ክርስቶስን በመምሰል ለማደግ እግዚአብሔር በመንፈሱ ይሞላን ዘንድ ልንወስዳቸው የሚገቡን ሶስት እርምጃዎች ናቸው። እነዚህንም እርምጃዎች በየዕለቱ ልንወስዳቸው ይገባናል፤ ምክንያቱም የእግዚአብሔር እርዳታ በየቀኑ ያሻናል። በመንፈስ ቅዱስ መሞሳት አንዴ ሆኖ የሚያበቃ ሁነት ሳይሆን፣ በሕይወታችን በየዕለቱ መቀጠል ያለበት አውነታ ነው።

በግሌ በየዕለቱ ቀኑን በጸጥታ ለእግዚአብሔር በማስረከብ፣ የእርሱ ወገን ስላደረገኝ በማመስገንና በዕለቱ ምን እንደሚጠብቀኝ ለለማያውቅ በማመስገን እጀምረዋለሁ። በመቀጠልም በዚህ ቀን ለክብሩ እንዲጠቀምብኝና ይህ እንዳይሆን ከሚከለክል ኃጢአት ሁሉ እንዲያነጻኝ አጠይቀዋለሁ።

ከዚያም በእምነት፣ ቃሉን ስታዘዝና በእርሱ ስተማመን፣ መንፈሱን እንደሚሞላኝ በማመን አራመዳለሁ። ሁልጊዜ ህልሙ (መገኘቱ) ባይታወቀኝም፣ በዕለቱ ፍጻሜ ላይ ግን ውሳኔዎን ተመልሼ ላስብ ከእኔ ጋር ሆኖ ስለመራኝ አመስግነዋለሁ። በዚያን ዕለት ከእኔ ጋር እንደሚሆን በስጠኝ ተስፋ መሰረት፣ በርግጥም ቃሉን አክብሯል።

ይህ የእናንተም ልምምድ ሊሆን ይችላል፣ በየዕለቱ ሕይወታችሁን ለክርስቶስ ጌትነት ስታስገዙ፣ በእናንተም ሕይወት የሚሆን ነገር ነው። ውሎአችሁን ተመልሳችሁ ስታስቡት ተስፋ እንደሰጠው ከናንተ ጋር ስለነበር ልታመሰግኑት እንድትችሉ፣ ቀኖቻችሁን ሁሉ ለእርሱ አስረክቡ።

ክፍል ሦስት

በመንገድ ላይ የሚደቀኑብን ተግዳሮቶች

ዐሥራ ስድስት

የመንቀሞሰል (የመንከራተት) ዘንባሌ

መደፈተና እንዳተገሙ ተጉና ጸበየ፤ መንፈስ ዝግጁ ነዉ፤ ሥጋ ግን ደካማ ነዉ

(ማቴ 25÷41)::

እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ከሆነ፣ የተለያዩ ችግሮች የሚከቡን ለምንድነው? ክርስቲያኖች ከችግር ነፃ አይሆኑም፤ እኛም እንታመማለን፣ እንፈተናለን፣ ሀዘን፣ ስብራትና ሌሎች በርካታ ችግሮች ያጋጥሙናል። በሕይወት ዘመናችን በምናደርገው ጉዞ መንግስተ ሰማያት እስክንገባ ድረስ በመንገዳችን ላይ የተለያየ አባጣና ጎርባጣ ሁኔታዎች ይገጥሙናል። በዕድሜ ስንገፋ፣ የሚገጥሙን ችግሮች የተለዩ ሊሆኑ ይችላሉ፤ ሆኖም ሙሉ በሙሉ ከእኛ አይወገዱም።

በዙድቀት አደጋ ውስጥ

ከቤታችን በተወሰነ ርቀት ላይ አነስተኛ ሐይቅ ይገኛል። ሐይቁ ውሃ የሚያገኘው በአቅራቢያ ከሚገኙ ተራሮች እየተወረወረ በሸለቆው በሚመጣ የተራራ ምንጭ ነው። ልጆቻችን ወጣቶች በነበሩበት ወቅት በዚያ ተጫውተዋል፤ ከዚያም አልፈው በሐይቁ ቀዝቃዛ ውሃ ውስጥ ይዋኙ ነበር። (አንዲያውም በቤታችን ሳሎን ከአሳት መሞቂያው (ከምድጃው) አናት ያለ መደርደሪያ የተሠራው ባንድ ወቅት በሐይቁ ውስጥ ለመጥለቅ እንደ መዝለያ ከሚያገለግል ሳንቃ ነው)። ሐይቁ የተበጀው ከብዙ ዓመታት በፊት ከምንጩ ዙሪያ ከጠንካራ ሊሚንቶ ግድብ ተገንብቶ ነው።

በአካባቢያችን ያሉት ተራሮች ለአየር ንብረት ጥቃት ተፈጥሮአዊ መከላከያ ስለሚሆኑ፣ ብዙ ጊዜ በቂ ዝናብ እናገኛለን። ይሁን እንጂ፣ ከጥቂት ዓመታት በፊት ባልተለመደ ሁኔታ ለተከታታይ ቀናት ከባድ ዝናብ ስለጣለ፣ ለወትሮ በቀስታ ይወርድ የነበረው ጅረት ኃይለኛና ያገኘውን የሚጠራርግ ፈረሰኛ ውሃ ሆነ። ከሞላው ወንዝ ዳርቻ የቆመ ሰዎች፣ ውሃው ትላልቅ ቋጥኞችን ሲያንከባልል ያዩ ነበር።

የአካባቢው ሰዎች ግድቡ ሊወድቅ ይችላል ብለው መስጋት ጀመሩ። ውሃ ወደ ወለሉ ንጣፍ መስረግ ስለጀመረ፣ በጥቃቅን ስንጥቆች መካከል ውሃ መፍሰቅ ጀመረ። ፖሊሶች ግድቡ በድንገት ሊወድቅ ይችላል በማለት ከግድቡ በታች የሚኖሩትን ሰዎች ለቀው እንዲወጡ አዘዙ። ደግነቱ ዝናቡ ጋብ በማለቱ ግድቡ እንደተፈራው ሳይፈርስ ቀረ (ምንም እንኳን በጎላ ላይ በከፍተኛ ወጪ ጥገና ቢደረግለትም)።

ይህ ክስተት ችግሮችና ፈተናዎች እኛን የሚያናውጡበትን ሁኔታ ያስታውስኛል። ልክ ግድቡ በሚሠርገው ውሃ እንደተነቀነቀ ሁሉ እኛም ብዙ ጊዜ ከግብረገባዊና መንፈሳዊ አቋማችን እስክንናወጥ ድረስ ግፊቶች ሊበራከቱብን ይችላሉ። የምንኖረው ዘወትር ከእግዚአብሔር ሊነጥለን በሚተናነቅ ተቃዋሚ ዓለም ሲሆን፣ አንዳንዴ ውጥረቶቹ ጠንካራ ሊሆኑ ይችላሉ። በሌላ አባባል፣ በሕይወት እንግልቶችና ፈተናዎች ተጠቂ ከምንሆንባቸው ምክንያቶች አንዱ በየዕለቱ በዙሪያችን በሚሆኑት (በሚገጥሙን) ሁኔታዎች ሳቢያ ነው።

ልክ ደራሽ ውሃው የግድቡን ደካማ ቦታዎች አንዳጠቃ ሁሉ፣ ችግሮችና ፈተናዎችም ደካማ ጎናችንን እየፈለጉ ያጠቁናል። ግድቡ ምናልባት ዘጠና ዘጠኝ በመቶ ጠጣርና ጠንካራ ሊሆን ይችላል፣ ግን አንድ በመቶው ብቻ ደካማ ሆኖ ውሃ የሚያሳልፍ ከሆነ ከመሠረቱ ሊናጋና ሊርስ ይችላል። ይህ ነገር በሕይወታችንም እውነት ነው። ችግሮችና ፈተናዎች ሁልጊዜ የሚያጠቁን ደካማ በሆንንባቸው አቅጣጫዎች ነው። በሌላ አባባል፣ በውስጣችን (በራሳችን) ድክመት ምክንያት ለሕይወት ግፊቶችና ፈተናዎች

ተጋላጮች አንሆናለን። ልክ በጋይለኛው ውሃ አንደተሸረሸረው ግድብ ጥገና፣ ዳግመኛ መጠገኑ ከፍ ያለ ወጪ የሚጠይቀን ሊሆን ይችላል።

ችግሮቻችንን መጋፈጥ

ክርስቲያኖች ከሆንን በኋላም አንኳን፣ በርካታ ችግሮች የሚገጥሙን ለምንድነው? አንዱ ምክንያት (እንደተመለከትነው)፣ በዘመን ፍጻሜ ሰይጣን ለመጨረሻ ጊዜ እስከሚሸነፍ ድረስ፣ በማያባራ ሰፊ መንፈሳዊ ተጋድሎ ውስጥ ተካፋዮች በመሆናችን ነው። በተጨማሪም፣ አሮጌው የኃጢአት ባህርያችን አሁንም ገና ስላልሞተ፣ አግዚአብሔር ከሰጠን አዲስ ባህርይ ጋር ትግል ላይ ናቸው። መንፈስ ቅዱስ አሁን በውስጣችን ቢያድርም፣ ይህ ማለት ከችግሮች ነፃ አንወጣለን ወይም ዳግመኛ ኃጢአት አንሠራም ማለት አይደለም። እንዲያውም መንፈስ ቅዱስ ለእኛ የተሰጠበት ምክንያት አግዚአብሔር ምን ያህል ደካሞች እንደሆንን ስለሚያውቅ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፣ "እንዲሁም መንፈስ በድካማችን ያግዘናል" (ሮሜ 8÷26)

ይሁን እንጂ፣ ዋናው አከራካሪ ጉዳይ ችግሮችና ፈተናዎች ለምን ይገጥሙናል ሳይሆን በእንዴት ደስ አኳኋን ምላሽ እንሰጣለን ነው። በቀጣዮቹ ጥቂት ምዕራፎች፣ መጽሐፍ ቅዱስ ስለዚህ ጉዳይ ምን እንደሚናገር እንመለከታለን። መጽሐፍ ቅዱስ በጣም ተግባራዊ መጽሐፍ ሲሆን አግዚአብሔር በዚህ መልኩ የሚናገረን ለሕይወት ፈተናዎችና ችግሮች የበለጠ የተዘጋጀን እንሆን ዘንድ ነው። አንደ አለመታደል ሆኖ ግን፣ ብዙ ጊዜ ፈተና ሲገጥመን የምንሰጠው ምላሽ ክርስቶስን በማያላይ መንገድ ነው፣ አደራረጋችን ለእኛም ላይታወቀን ይችላል። ይህን ዓይነት ምላሽ ስንሰጥ፣ ሰይጣን ባለድል ይሆንና የክርስቶስ ስም ይነቀፋል።

በዚህ ምዕራፍ የምንመለከተው ርዕሰ ጉዳይ ስለፈተና ይሆናል። ፈተና በምድር ያሉ ሰዎች ሁሉ የሚገጥማቸው ነገር ስለሆነ፣ የተለያዩ ዓይነት ፈተናዎች በመንገዳችን ይጋረጣሉ። ግን ፈተና የሚመጣው ከየት ነው? ለመቋቋም የሚያስቸግረንስ

ለምንድነው? ፈተናን መቋቋም ይለብን አንዴት ነው? እጅ ስንሰጥስ ምን ማድረግ አለብን? ሰቀጣይስ ከመውደቅ ልንጠበቅ የምንችለው እንዴት ነው?

ፈተና ምንድነው?

የፈተናን ፍቺ ለመስጠት ሞክራችሁ ታውቃላችሁ? በቀላል አነጋገር፣ መፈተን ማለት ልክ ይልሆነን ነገር ለማድረግ መገፋፋት ወይም መማለል ማለት ነው።

ፈተና ማለት ኃጢአት ማለት እይደለም፣ መፈተንም ኃጢአት ማለት አይደለም። መፈተን ማለት ልክ ይልሆነን ነገር ለማድረግ መማለል (መላብ) ማለት ነው፣ ኃጢአት ግን ሰፈተና ተሸንፎ ልክ ያልሆነን ነገር ማድረግ ማለት ነው። መፈተን ኃጢአት አይደለም፣ ለፈተና እጅ መስጠት ግን ኃጢአት ነው። በአገልግሎቱ መጀመሪያ ላይ፣ "መንፈስ ቅዱስ ኢየሱስን በዲያብሎስ ይፈተን ዘንድ ወደ ምድረበዳ ወሰደው" (ማቴ 4÷1)። ኢየሱስ ግን ለሰይጣን ፈተናዎች (ፈተናዎቹና ማባባያዎቹ እጅግ ማራኪና አጓጊ ቢሆኑም) እጅ አልሰጠም። መጽሐፍ ቅዱስ አንደሚነግረን፣ ኢየሱስ "ከኃጢአት በቀር በነገር ሁሉ እንደ እኛ የተፈተነ ነው" (ዕብ 4÷15)።

ልክ ያልሆነን ነገር ለማድረግ በምፈተንበት ጊዜ፣ የኢየሱስን ምሳሌ በማየት ብርታት አገኛለሁ። በነገር ሁሉ ስለተፈተነ፣ እርሱ ሊረዳው የማይችል ፈተና፣ እናንተንና እኔን ሊገጥመን አይችልም። እርሱ ራሱ በዚህ መንገድ ስላለፈ፣ ስንፈተን የምናልፍበትን መንገድ ያውቀዋል። አንደዚሁም እርሱ ፈተናን ተቋቁሞ ስላሸነፈ፣ የድልን ጎዳና ያመለከተናል። እኛም እናሸንፋለን።

ዓሰም፣ ሥጋና ሰይጣን

ፈተና የሚመጣው ከየት ነው? የክፋት ሁሉ ሥረ - መሠረት (የፈተናም ጭምር) ባለጋራችን የሆነው ሰይጣን ነው። መጽሐፍ ቅዱስ አንዲህ ይላል፦ "ጠላታችሁ ዲያብሎስ የሚውጠውን በመፈለግ አንደሚያገሳ አንበሳ ወዲያና ወዲህ ይዞራል" (1 ጴጥ 5÷8)። አንበሳ ከአንስሳት መንጋ ውስጥ

ደካማውንና ስማጥቃት የሚያመቸውን ፈልጎ እንደሚዞር ሁሉ፣ ሰይጣንም እንደዚሁ ደካማ የምንሆንበትን አጋጣሚ እየፈለገ ያደባል።

ይሁንና ሰይጣን በጣም የረቀቀ ስልት ስለሚጠቀም፣ በቀጥታ ወይም በገሃድ አያጠቃንም። "መጣሁብህ እኔ ባሰጋራህ፣ ላጠፋህ ነው" የሚል ጽሑፍ ያለበት ምልክት አንግቦ አይመጣም። ከበርካታ ዓመታት በፊት በአውስትራሊያ አደላይድ በተባለ ዩኒቨርስቲ ውስጥ በምናገርበት ወቅት፣ የተወለኑ ተማሪዎች "እኔ ሰይጣን ነኝ! እኔ ሰይጣን ነኝ" የሚል ጽሑፍ አንግበው ወደ ተሰበሰበው ሕዝብ በመምጣት መረበሻቸው ትዝ ይለኛል። ሰይጣን ራሱን በይፋ እየገለጸ አይመጣም፣ በጣም የረቀቀ በመሆኑ ራሱን ይሰውራል፣ መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚነግረን ሰይጣን "የብርሃን መልአክ ለመምሰል ራሱን ይለዋውጣል" (2ቆሮ 11፥14)። ብዙ ጊዜ ራሱን ለውሮ፣ ከመጋረጃ በስተጀርባ ይሠራል።

ሰይጣን የሚ ፈትነን እንዴ ት ነው ? ይህን የ ሚያደርገው በሁለት መንገድ እንደሆነ መጽሐፍ ቅዱስ ይነግረናል። *አንደኛ፣ ውጫዊ ግፊት ያበረታብናል፣* ይህም ማለት በዙሪያችን ካለው ዓለም ማለት ነው። ቀደም ሲል የገለጽኩት ግድብ፣ የዘነበው ዝናብ በቶሎ ቢያበራ ኖሮ፣ የመፍረስ (የመለነጣጠቅ) አደጋ አይገጥመውም ነበር። ይሁን እንጂ በገነቡ የተባበሰው ምንጭ ወደ ግድቡ እየገባ ግፊቱን አጠነከረበት - በእኛም ሕይወት የሚሆነው እንደዚህ ነው።

መጽሐፍ ቅዱስ ይህን ግፊት "ዓለም" ይለዋል። ዓለም ሲባል በዙሪያችን የምናየው አካላዊ ዓለም ላይሆን፣ የሚያምነው ዓለም ራሱን የሚያስተዳድርበት የእሴት ሥርዓት - የአስተሳሰብና የድርጊት ዘይቤ ማለት ነው። ይህ ከእግዚአብሔር የተለየውን፣ በፈጣሪው ላይ እያመጸ ያለውን ዓለም መለኪያዎችና ባሕርያትን ያመለክታል።

ይህን ከቶ አትዘንጉ፣ የምንኖረው ምስቅልቅል ባለ ዓለም ውስጥ ነው፣ ሰዎች ሲወዱ የሚገባቸውን ሲጠሉ፣ ሊጠሉ

የሚገባቸውን ሲወዱ በሚገኙበት ዓለም ውስጥ ነው። ለዚህም ነው መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ በማለት የሚያስጠነቅቀን፣ "ዓለምን ወይም በዓለም ያለውን ማናቸውም ነገር አትውደዱ"። ይህን ካለ በኋላም ዓለማዊ ዝንባሌን የሚገልጡ ባህርያትን ይዘ ረዝራል፣ "በዓለም ያለው ሁሉ፣ የሥጋ ምኞት፣ የዐይን አምሮትና የኑሮ ትምክህት ከዓለም እንጂ ከአብ የማመጣ አይደለም" (1 ዮሐ 2፥15-18)።

ዓለማዊነት እግዚአብሔርን ሳይሆን እኔነትን ማዕከል የሚያደርግ ውለጣዊ ዝንባሌ ነው። ትኩረቱ በአሁን ጊዜ ላይ የታሰረ ሲሆን፣ የእሴቶቹ መነሻዎችም የትዕቢትና የራስ ወዳድነት መሻቶች ናቸው። ጳውሎስ የቆሮንቶስን አማኞች በክርስቶስ በኢየሱስ መንፈሳዊ ብስለት ስላልነበራቸውና እንደ ኢ-አማንያን ይመላለሱ ስለነበር እንዲህ ሲል ይገስፃቸዋል "በመካከላችሁ ቅናትና ክርክር አለ፣ ታዲያ ሥጋውያን መሆናችሁ አይደለምን?" (1ቆሮ 3፥3)።

የሥጋ ፈተና

ሰይጣን እኛን የሚፈትንበት ሁለተኛው መንገድ ከራሳችን ውስጥ ነው - በመጽ ሐፍ ቅዱስ እጠራር "ሥጋ" የተባለውን በመጠቀም ነው። እዚህ ላይ "ሥጋ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው አካላዊ ሥጋችንን ብቻ ላይሆን፣ እኛን ሊገዙን የሚሞክሩ ምኞቶቻችንና ፍላጎቶቻችንን ጭምር ነው። ሥጋ ማለት ከሥጋ ፍትወት ምኞት (እርስን በጨምርም) የገዘፈ ነው። ሥጋ ማለት እግዚአብሔርን ደስ ለማሰኘት ከመፈለግ ይልቅ የራሳችንን ምኞቶችና ፍላጎቶች ማርካትን ዋነኛ ዓላማ ማድረግ ማለት ነው። መጽሐፍ ቅዱስ እንደዚህ ይላል፦ "እንደ ሥጋ የሚኖሩ ልባቸውን በሥጋ ፍላጎት ላይ ያሳርፋሉ" (ሮሜ 8፥5)። ያዕቆብም እንዲህ ይላል፦ "ነገር ግን እያንዳንዱ የሚፈተነው በራሱ ምኞት ሲሳብና ሲታለል ነው" (ያዕ1፥4)።

አካላችንን የሰጠን እግዚአብሔር እንደ መሆኑ፣ ተገቢ እንክብካቤ ልናደርግለትና ለክብሩ ልናውለው ይገባል። ብዙ ጊዜ ግን ስውነታችንን ከመግዛት ይልቅ፣ እንዲገዛን እንፈቅድለታለን።

አንዳንዶች ራሳቸውን ለመጠጥ ወይም ለአደንዛዥ ዕፆች ወይም ለምኞት ወይም ለሱስ ባርነት ያስገዛሉ፣ ሌሎችን ደግሞ ልማዶች ይለዋጥኑባቸዋል። ሌሎች ደግሞ አንዳንድ ነገሮችን ከሚገባው በላይ የሕይወታቸው ማዕከል በማድረግ ጣዖት አንዲሆንባቸው ፈቅደዋል።

ለዚህም ነው መጽሐፍ ቅዱስ "ለውነታችሁን ቅዱስና እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝ ሕያው መሥዋዕት አድርጋችሁ አቅርቡ፤ ይህም መሥዋዕት እንደ ባለ አዕምሮ የምታቀርቡት አምልኮአችሁ ነው" (ሮሜ 12፥1) ሲል የሚያዘን። በተጨማሪም "ጌታ ኢየሱስ ከ ርስቶስን ልበስት ፤ ምኞቱ ንም ይፈጽም ዘ ንድ ሰሥጋ በሐሳባችሁ አትመቻቹለት" (ሮሜ 13፥14) ሲል ይመክረናል። ለውነታችሁን ለክርስቶስ ሕያው መሥዋዕት አድርጋችሁ አቅርባችኋል?

የማምለጫ መንገድ

ይሁን እንጂ፣ ዋነኛው ጥያቄ፣ ይህ ነው፤ *ፈተናን መቋቋም የምንችለው እንዴት ነው?* የሚለው ነው። አ ንዱት ልንቋቋም እንችላለን? በቅርቡ አንድ ወጣት እንዲህ ሲል ጻፈልኝ፦ "እንዲህ ደካማ ባልሆንኩ ምንኛ ጥሩ ነበር! ሁልጊዜ ቁርጠኛ ውሳኔዎች ባደርግም፣ ከንደኞቼ ጋር ስሆን አነርሱ የሚያደርጉትን መከተሌ የማይቀር ይሆናል። ፈተናን የመቋቋም ብቃቱ ያለኝ መስሎ አይሰማኝም።" ምናልባት አናንተም አንደርስ ይሰማችሁ ይሆናል። ከባዱ ዝናብ ቤታችን አቅራቢያ የተገነባውን ግድብ ስንጥቆችና ድክመቶችን እንዳሳበቀ ሁሉ፣ ፈተናም በሕይወታችን የተደበቁ ድክመቶችን ይገልጣል።

ፈተናን መቋቋምና ድል መንሣት የምትችሉባቸውን ዐራት እርምጃዎች ልጠቁማችሁ፣ *አንደኛ፣ ፈተናውን ለይታችሁ አውቁት።* ለሥች በተደጋጋሚ የነገሩኝ ነገር፣ "ይህን ነገር ያደረከት እኔው ራሴው መሆኔን ማመን ይከብደኛል። እያደረግሁት መሆኔን አንኳን የተረዳሁት የማልመስለበት ርቀት ከሔድኩ በኋላ

ነው" የሚል ነው። ለይጣን ይህ ነገር ኃጢአት አለመሆኑን ወይም እንደማይጎዳቸው እንዲያስቡ በማድረግ አታሎአቸዋል።

አንዳንዶች ስህተትና ትክክል የሚባሉ ነገሮች የሉም እያሉ ስለ ፈተና እምብዛም መጨነቅ እንደሌለብን ይነግሩናል። እግዚአብሔር ግን እንደዚህ አይነግረንም። ይህን ልብ በሉ፣ *መፈተን ማለት በእግዚአብሔር ዓይን ልክ ያልሆነን ነገር ለማድረግ የሚደርስብን ግፊት ነው፣ ኃጢአት ማለት ደግሞ ያው ነው።- ኃጢአት።*

ለዚህም ነው መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ስህተትና ትክክል ምን እንደሚያስተምር ማወ ቅ ያለብን። በየዕለቱ ከመገናኛ ብዙሃ ን፣ ከማስታወቂያዎች፣ ከመዝናኛዎች፣ ከታዋቂ ሰዎች፣ ከወዳጆቻችን ሳይቀር "ለራስህ ኑር" የሚል መልዕክት በተለያዩ መንገዶች ይቀርብልናል። ዓለም እኛን በራሱ መልክ ለመቅረጽና ንጹሕት በእውነት ኃጢአት እንዳልሆነ ሊያሳምነን በመሞከር አርሱን እንድንከተል ደስ አረፍት ይወተውተናል። ደግሞስ ዓለም ሁሉ የሚያደርገውን አላደርግም የምትል አንተ ማነህ? በማለት ይሞግተናል። እግዚአብሔር ግን በተቃራኒ እንዲህ ይሰናል፦ "በአእምሮአችሁ መታደስ ተለወጡ እንጂ ይህን ዓለም አትምሰሉ›› (ሮሜ 12፥2)።

ፈተና በራችሁን ሲያንኳኳ ለይታችሁ ለማወቅ እንዲረዳችሁ እግዚአብሔርን ጠይቁት። በዚህ ወቅት በነፍሳችሁ የማስጠንቀቂያ ደወል መሰማት አለበት። ትኩረታችሁ በግልጽ በሚታወቁ ፈተናዎች ላይ ብቻ አይሁን። ስውር የሆኑ የአንደበት ወይም የስሜቶች ወይም፣ የሀሳብ ወይም የመሻት ፈተናዎችንም ልብ ብላችሁ ተመልከቱ። መዝሙረኛው እንደዚህ ሲል ጸልዮአል፦ "እግዚአብሔር ሆይ፣ መርምረኝ፣ ልቤንም ዕወቅ" (መዝ 139፥23)።

አንዳንድ ጊዜ፣ "ግራጫ ነገሮች" (ትክክል ወይም ስህተት ያልታወቀ) ማለትም መጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ ባይከለክላቸውም፣ በሕይወታችን ሥፍራ ላይኖራቸው የሚችሉ ነገሮች ይገጥሙናል።

እንድ ነገር ስሀተት ይሁን ወይም ትክክል ይሁን ለማወቅ አዳጋች ሆኖ ስታገኙት፣ የሚከተሉትን ጥያቄዎች ለራሳችሁ አቅርቡ፤ ይህ እግዚአብሔርን ያስከብራል? ይህን ባደርግ ለእግዚአብሔር የምስጋና ጸሎት ላደርስ እችላለሁ? ወደ ክርስቶስ ያቀርበኛል? ወይስ በዚህ ዓለም እንድጠመድ ያደርገኛል? ጤናዬን ይጐዳዋል? ወይም በሌላ መልኩ የሚጎዳ ነገር እሰውን? ሌሎች ሰዎች (በተሰይም ያልበሰሉ ክርስቲያኖች) በመንፈሳዊ ወይም በግብረገባዊ ሕይወታቸው የሚሰናከሉበት ይሆን? አንድ አስተዋይ ክርስቲያን ከበርካታ ዓመታት በፊት፣ "ስለ እንድ ነገር ጥርጣሬ ካለህ - አታድርገው!!" ሲል የመከረኝን ቃል መቼም አልዘነጋውም።

ከፈተና ሸሹ

ሁለተኛ፣ ፈተና በራችሁን ሲያንኳኳ፣ ተቃወሙት። ማርቲን ሉተር እንዲል ሲል ተናግሯል "ወፎች ከጭንቅላታችሁ በላይ እንዳይበሩ ማድረግ አትችሉም ነገር ግን በጸጉራችሁ ላይ ጎጆ እንዳይሠሩ መከልከል ትችላላችሁ!!" እናንተና እኔ ፈተናን ማስወገድ ባንችልም፣ እንዳይለሰጥንብን ማድረግ ግን እንችላለን።

ፈተናዎችን አታጣጥሙ፣ አትኑሩባቸው ወይም ከነርሱ ጋር እትጫወቱ፤ ወይም በአእምሮአችሁ በመከለስና በማመላለስ እንዲለጥነባችሁ እትፍቀዱላቸው። ስለ እንድ ፈተና ይበልጥ ባስባችሁ መጠን የበሰጠ የሚስብና የሚማርክ መሆን ይጀምራል። በልጅነታችሁ በማግኔት ተጫውታችሁ ታውቃላችሁ? ማግኔቶቹ በተቀራረቡ መጠን፣ መለያየቱ አስቸጋሪ ይሆናል። ፈተናም እንደዚህ ነው። ወደ እኛ እንዲቀርብ በፈቀድንለት መጠን፣ እኛን የመሳብ ኃይሉ እያየለ ይመጣል። በርግጥ፣ አስቀድማችሁ ካልነቃችሁበት፣ እስክነጭራሹ ለመቋቋም እስቸጋሪ ይሆናል።

ይህ እንዲሆን እትፍቀዱ! *ፈተናን ማየትና መያዝ ያለባችሁ እንደ መርዘኛ አባብ ወይም በመርዝ እንደተሞላ ብልቃጥ ነው። እንዲህ ስለሆነ መሆን ያለበትም እንዲሁ ነው።* ፈተናን ለመቋቋም ብቸኛው መንገድ ወዲያውኑ እና በቁርጠኝነት መቃወም ነው። ጳውሎስ ለጢሞቴዎስ፣ "ከወጣትነት ከፋ ምኞት ሽሽ" (2 ጢሞ

2፥22) ይለዋል። የቆሮንቶስ ሰዎችም "ከጣዖት አምልኮ ሽሹ" (1 ቆሮ 10፥14) ተብለዋል። በተጨማሪም መጽሐፍ ቅዱስ፣ "ከዝሙት ሽሹ" (1 ቆሮ 6፥18) ይለናል። በራሳችን ጥንካሬ ከፈተና መሸሽ አንችልም፤ በፍፁም። እግዚአብሔር ግን እርሱን ስንጠይቀው የሚያስፈልገንን ጥንካሬ ይሰጠናል። አንድ ጓደኛዬ እንዲህ ብሏል፦ "ዲያብሎስ በሩን ሲያንኳኳ፣ በሩን እንዲከፍትሰት ለኢየሱስ እነግረዋለሁ!"

የግማሽ መንገድ እርምጃ አያዋጣም። ቁርጠኛና የማያዳግም ውሳኔ ማድረግ ይጠበቅብናል። ሰምሳሌ ኮምፒውተርን ወይም ቴሌቪዥንን እንደ መዝጋት ማለት ነው . . . ከአንድ ሰው ጋር ጓደኝነት እንደ መመሥረት . . . ወይም ሊያበረታታችሁና ኃላፊነት እንዲሰማችሁ ከሚያደርጋችሁ በላል ክርስቲያን ጋር ተጋድሎአችሁን እንደ መከፋፈል ሊሆን ይችላል። አልፎ አልፎ ሥራቸውን የለቀቁ (የለወጡ) ሰዎች ደብዳቤ ይደርሰኛል፣ ሥራቸውን ለመልቀቅ ምክንያታቸው በሥራ ቦታ ያለ አንድ ሰው ወይም ሁኔታ ስህተት እንዲሠሩ ስላደረጋቸው ነው።

ፈተናን በተመለከተ መጽሐፍ ቅዱስ ከሚናገራቸው ዐቢይ ጥቅሶች መካከል አንዱ በ1ኛ ቆሮ 10፥13 የሚገኘው ነው። ይህን ክፍል በቃል እንድትይዙት አበረታታችኋለሁ። "በሰዎች ሁሉ ላይ ከደረሰው የተሰየ ፈተና አልደረሰባችሁም፣ እግዚአብሔር ታማኝ ነው፤ ስለዚህ ከምትችሉት በላይ እንድትፈተኑ አይተዋችሁም፤ ነገር ግን በምትፈተኑበት ጊዜ ፈተናውን እንድትችሉ፣ መውጫ መንገዱን ያዘጋጅላችኋል።" በርግጥም፣ እግዚአብሔር "መውጫን ይሰጠናል" መውጫውን እንዲያሳያችሁ ጠይቁት - በእርሱም ሐዱ።

ከፈተና ተማሩ

ሶስተኛ፣ መፈተናችሁን ለትምህርት አድርጉት። በሌላ አባባል፣ ወደፊት ፈተና ስገጥማችሁ በተሻለ መንገድ ልትቋቋሙት ትችሉ ዘንድ፣ ስለፈተናው አስላስሱ። በተለይ ከአንዳንድ ሰዎች ጋር ስትሆኑ፣ ለመወደድ ስትሉ እነርሱ የሚያደርጉትን የሚያስደርግ ያነጣ ጉን አላችሁ? በአንዳንድ ሁኔታዎች ውስጥ ወይም ቦታዎች

ስትሆኑ ትፈተናላችሁ? ስይጣን ሲጠቀምበት የሚሞክርበት ድክመት በሕይወታችሁ አለ? ለምሳሌ፡- ስይጣን የምትመኩበትን ነገር አያመሰከታችሁ ይሆን? አንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ት/ቤት ፕሮፌሰር የሆነ ጓደኛዬ፣ በወሲብ ኃጢአት የወደቁ ክርስቲያን መሪዎችን አንድ በአንድ ከዘረዘረልኝ በኋላ፣ እነዚህ ሁሉ ስዎች ሊወድቁ የበቁት በትዕቢት ምክንያት እንደሆነ ተናገረ። አግዚአብሔር ድካማችንን እንድንረዳና መቋቋም የምንችልበትን ብርታት ከአርሱ እንድንጠብቅ ሊፈልግ እንደንፈተን የሚፈቅድበት ጊዜ አለ። ፈተናን መቋቋም ብቻ ሳይሆን ልንማርበትም ያስፈልጋል።

ለፈተና ሊያጋልጧችሁ የሚችሉ ሁኔታዎችን መራቅ ተማሩ። አንዲት ሴት ከመጠን በላይ የመብላት ፈተና ስለነበራት ትግል ጽፋልኝ ነበር። ይህንን ስመቋቋም የወሰደችው ብቸኛው ርምጃ፣ የምታዘወትራቸውን የምግብ ሽቀጦችን የተወሰኑትን ዓይነቶች ማስወገድ ነበር። ማራቅ የሚገባትን ምግብ ገዝታ በማቀዝቀዣዋ ካስገባችው ፈተናውን መቋቋም የማይታሰብ ይሆናል።

ስንወድቅ

ዐራተኛ፣ ስትወድቁ ንስሃ በመግባት፣ የእግዚአብሔርን ይቅርታና ኢድሳት አሸ። ኃጢአት ከእግዚአብሔር ጋር ያለንን ሀብረት ያፈርሳል - ይሁን እንጂ ግንኙነቱን አያከትመውም። ባንታዘዘውም እንኳን አሁንም ልጆቹ ነን። ሐፍረትና የበደለኝነት ስሜት ስለሚጫነን አንዳንዴ መደበቅ እንፈልጋለን። ይሁንና አግዚአብሔር አሁንም ይወደናል፣ ይቅር ሊለንና መልሶ ሊቀበለን ይሻል። ስትወድቁ፣ ንስሃ በመግባት የእግዚአብሔርን የይቅርታና የመታደስ የተስፋ ቃሉን በመተማመን ጠይቁ።

አንዲት ሴት፣ ለፈተና እጅ በመስጠት ቤተሰቧ እንደፈረሰ ነግራኛለች። ጨምራ የነገረችኝ ነበር፣ "ከሁሉ በላይ ልቤን የሚስብረው ነገር አግዚአብሔር ከቶም ይቅር የማይለኝ መሆኑን አውቃለሁ።" ለይጣንም የሚፈልገው ይህን እንድናምን ነው - ግን

አውነት አይደለም። መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ሲል የተስፋ ቃል ይሰጠናል፣ "ኃጢአታችንን ብንናዘዝ ኃጢአታችንን ይቅር ሊለን፣ ከዐመፃ ሁሉ ሊያነጻን እርሱ ታማኝና ጻድቅ ነው" (1 ዮሐ 1፡9)። አግዚአብሔር የስጣችሁ ተስፋ ይህ ነው። በዚህ ቃል አመኑ።

አግዚአብሔር ይቅር ሊለው የማይችለው ብቸኛ ኃጢአት ይቅርታውን የመግፋት ኃጢአት ብቻ ነው። ኃጢአት ስታደርጉ፣ ለበብ አስባብ አትስጡ ወይም ስማድበስበስ አትሞክሩ ወይም ችላ አትበሉት፣ ወይም ሌላን ስው አትወንጅሉ። አውነቱን ተቀበሉ . . . ንስሃ ግቡ . . . ከዚያም አግዚአብሔር ሙሉ በሙሉ ይቅር ስላላችሁ ደስ ይበላችሁ።